ተሰማርተው ኖሩ። በመሆኑም በኅብረተሰቡ ዘንድ ጠይብ፣ ቡዳና አስማተኛ ተብለው በስድብ ስም የሚጠሩ የኢትዮጵያ አንድ ልዩ የሃይማኖትና የዕደጥበብ ካስት ማኅበረሰብ ሆኑ።

በመጨረሻ በ1980ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ የኢትዮጵያ ቤተ እሥራኤል/ፈላሾች በሥርዓትና በሃይማኖት ግፊት የጥንቱ አገራችን ወደ ሚሉት ወደ እሥራኤል ፈለሱ።

ይህ ከዚህ በላይ ባጭርና በጥቅል የቀረበው የሰሜን/ፈላሻ ሕዝብ ረጅም የቁጡዙዙ ዓመታት የመከራና የጦርነት ታሪክ በኢትዮጵያ ዘውዳዊ የሥርዓት የሕዝቦች መከራ አንድ ምሳልና መገለጫ ብቻ ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር የቅርቡ በ60000 የሚቆጠሩ ቤተ እሥራኤሎች የአገረ እሥራኤል ፍለሳ የኢትዮጵያ የሰሜን/ፈላሻ ረጅም ታሪክ ፍጻሜ አይደለም። ምክንያቱም በኢትዮጵያ ልዩ የሕዝቦች፣ የቋንቋዎች፣ የባህሎችና የሃይማኖቶች መስተጋብርና መወራረስ ልምድና ታሪክ መሠረት በተጠቀሰው ረጅም ዘመን ሰሜን/ፈላሾች በመሬት፣ በጊዜ፣ በቋንቋ፣ በደም፣ በባህልና በእምነት በአካባቢው የአገው፣ የአማራና የትግሬ ነባርና ተዛማጅ ሕዝቦች አካል ሆኗልና። እቴጌ ምንትዋብ፣ ዳጃች ውቤ፣ አጼ ቴዎድሮስና እቴጌ ጣይቱ የመሳሰሉ የኢትዮጵያ ታላላቅ የአገርና የመንግሥት መሪዎች የወለደ አንድ የአገሪቱ ነባር ዘርና ሕዝብ ነውና።





# 4. የእስልምና ሃይማኖት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት

## ከእስልምና በፊት የኢትዮጵያና የአረቦች ታሪካዊ ግንኙነት

### *የኢትዮጵያና የሮማውያን የፖሊሲ ስምምነት በአረቢያ*

በ610-632 በአረቢያ በነቢዩ ሙሐመድ አብደላ የተመራው ታላቁ የአረቦች እስላማዊ አብዮት ታሪካዊ መነሻዎችና ዓለማቀፋዊ ውጤቶች በአካባቢው በሦስቱ የሮማውያን፣ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት መካከል ለረጅም ዘመን ከተካሄዱ ጂኦ-ፖለቲካዊ ግንኙነቶች ጋር በቅርብና በጥብቅ የተያያዙ ናቸው።

ከታሪክ እንደሚታወቀው፣ ሮማውያን በ30 ዓመተ ዓለም ግብፅን ለሦስት ምዕተ ዓመታት (332-30) ከገዙት ግሪኮች ያዙ። በዚህ የግሪኮ-ሮማውያን ዓለማቀፋዊ የሽግግር ዘመን በላይኛው ዓባይ ሸለቆ ጥንታዊ የኑቢያ-ሚሮዌ መንግሥት እንዲሁም በአኅራባቹ አረቢያ ሚናን፣ ሳባ፣ ቀጣባን፣ ሃድራማዊ፣ ሂሚያሪትና ሃምዳና የተሰኙ አናሳ የአረብ መንግሥታት በየበኩላቸው በራሳቸው ውስጣዊና አካባቢያዊ ምክንያቶችና ግፊቶች ሁሉም በፈጣን የውድቀት ሁኔታዎችና ሂደቶች ላይ ነበሩ።[1]

እነዚህ የዘመኑ ታላላቅ አካባቢያዊና ዓለማቀፋዊ ክስተቶች፣ ሁኔታዎችና ሂደቶች የዓባይ ሸለቆ፣ የቀይ ባሕር፣ የአረቢያና የመካከለኛው ምስራቅ እስትራቴጂያዊ አገሮችን ለሦስቱ የሮም፣ የፋርስና የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥታት ክፍት የግዛትና የተፅዕኖ አካባቢዎች አደረጉ።[2]

ይሁን እንጂ በአካባቢው ከሦስቱ ተጠቃሽ መንግሥታት፣ በእስትራቴጂያዊ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በደጋማው ክልል የሚገኘው የኢትዮጵያውያኑ መንግሥት በተጠቀሱት ሁኔታዎችና ሂደቶች ላይ ለዓባይ ሸለቆ፣ ለቀይ ባሕርና ለኤደን ባሕረሰላጤ ጠረፍ ንግድ፣ ሰላምና ፀጥታ ዋስትና ለመስጠት ብቃት ያለው ኃይል

[1] Kobishchanov, Axum, p. 36.
[2] Ibid., p.37.

መሆኑን አረጋገጠ።[3] ይህም ሁኔታ በኢትዮጵያና በሮማውያን መንግሥታት መካከል የጂኦፖለቲካና የፖሊሲ ስምምነት ለመፍጠር ምቹ መንገድና ምክንያት ሆነ። ባንፃሩ፥ ሁለቱም በኋላ በአረቦቹ እስላማዊ አብዮት እስኪደመሰሱ ድረስ የሮማውያንና የፋርሳውያን መንግሥታት በአካባቢው ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የንግድና የኃይል ሚዛን ባላንጣ ኃይሎች ሆኑ።

### *ኢትዮጵያ በአረቢያ ላይ የነበራት ፖሊሲ ታሪካዊ መነሻና ዕድገት*

በ24 ዓመተ ዓለም ሮማውያን ከግብፅ ተነስተው በአረቢያ ላይ የመጀመሪያ ወረራ አካሄዱ።[4] በዘመነ ክርስትና በ105-108 ደግሞ የሮማውያኑ የአረቢያ አውራጃ ተመሠረተ።[5] በመሆኑም አረቢያ በአፍሪካ፥ በአውሮፓና በሩቅ እስያ አገሮች መካከል እስትራትጂያዊ የዓለም ንግድ መንገድና ድልድይ ሆነ። ስለሆነም ከላይ እንደተባለው ሁለቱ ኃያላን የሮምና የፋርስ መንግሥታት በአካባቢው በንግድ፥ በእስትራቴጂና በኃይል ሚዛን ጉዳዮች ላይ ለረጅም ዘመን ባላንጣ ኃይሎች ሆኑ።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ሁለት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የዘመኑ አረቦች በአኅራባቹ ሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር «ሀበሻት» እና «አክሱማውያን» በማለት በሁለት ተወራራሽ ስሞች የሚጠሩዋቸው ኢትዮጵያውያን ቀይ ባሕርን ተሻግረው በምዕራብ፥ በማዕከላዊና በደቡብ አረቢያ ምድር በግምት በሰሜን ምዕራቡ ጫፍ ከዛሬው የሳውዲ አረቢያ የሂጃዝና የአሲር ክፍላተ ሀገር አንስቶ በደቡብ ምስራቅ እስከ የመን ድረስ በሚገኘው ረጅም የቀይ ባሕር ምሥራቃዊ ጠረፍ ክልል በጥንታዊ ሰነዶች ቲሃማት፥ ሚና፥ ሃምዳን፥ ሳባ፥ ሂሚያሪት፥ አራብቴ፥ ኪናይዶኮልፕቴ፥ ሀበሻ፥ ረይዳን፥ የመን፥ ቀጣባንና ሃድራማዊ ተብለው በልዩ ልዩ የጎሳና የአካባቢ ስሞች ከሚታወቁ ብዙ የአረብ አገሮችና አናሳ የጠረፍ መንግሥታት ጋር ረጅም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግንኙነቶችን መቼና እንዴት እንደጀመሩ እስከ ዛሬ ድረስ ከተገኙ የጽሑፍና የአርኪኦሎጂ መረጃዎች በትክክል ለማወቅ ገና አልተቻለም።[6]

---

[3] Ibid., p. 41.

[4] G. W. B. Huntingford (tr. & ed.,) The Periplus of the Erythrean Sea (1980), pp. 3-4.

[5] Sergew Hablesellassie, History, p.72.

[6] Conti Rossini, "Expeditions et Posssessions en Arabie", Journal Asiatique, Ser. 18 (1921), pp. 5-36.





ይህን የኢትዮ-አረብ ግንኙነት ታሪካዊ መነሻና ዕድገት አስመልክቶ ኢጣልያዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ ኮንቲ ሮሲኒ (1872-1949) እንደዘገበው፥ በዘመነ ክርስትና በ130 አንድ ረቢ አቂባ የተባለ ይሁዳዊ ጸሐፊ ደቡብ አረቢያን ጎብኝቶ ታልሙድ በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፍ ከጎባሩ የአረብ ሕዝቦች በመልክ፥ በቀለምና በባህል ልዩ የሆነና ኢትዮጵያዊ ነኝ ያለ አንድ ጥቁር ንጉሥ የአገሩ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ሆኖ እንደእሱም ጥቁር ከሆንች እቴጌዪቱ ጋር አረቢያን ያስተዳድር ነበር።[7]

ከዚህ በ130 ዓመተ ምህረት በአረቢያ በረቢ አቂባ ከተጠቀሰው ጥቁር ኢትዮጵያዊ ንጉሥ በኋላ በግምት ከ2ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ እስከ 3ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ማለትም ከ175 እስከ 225 ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ በሳባ ቋንቋና ፊደል በድንጋይ ላይ ተጽፈው በየመን አገር ከማሪብ ጥንታዊ የሳባ ከተማ በተገኙ ብዙ የአረብ ነገሥታት ዜና መዋዕሎች «የሀበሾችና የአክሱማውያን» ነገሥታት ገደረት፥ ዋዜባና አድባ የተባሉና ደቡብ አረቢያን ይገዙ የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ አሁን በዘመናችን በአርኪኦሎጂ ጥናትና ምርምር ታውቋል።[8]

በተጨማሪም፥ በሦስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ኢጋማሽ አካባቢ በኢትዮጵያ በመዳብ ዘንግ ላይ በግዕዝ ቋንቋና ፊደል የተጻፈና «የአክሱማውያን ንጉሥ ገደር» የሚል አንድ ታሪካዊ ጽሑፍ በቅርቡ በሰሜን ምስራቅ ትግራይ ከአንድ ጥንታዊ ሥፍራ ተገኝቷል።[9]

አሁን ዋናው ነገር፥ በደቡብ አረቢያ በሳባ ጽሑፍ «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» እና በኢትዮጵያ በግዕዝ ጽሑፍ ደግሞ «የአክሱማውያን ንጉሥ ገደር» ተብለው የቀረቡ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ሳይሆኑ በአንድ ወቅት በሁለት በተለያዩ ሥፍራዎች፥ ቋንቋዎችና ፊደላት በሁለት በተለያዩ የስም አጠራር ዘዴዎች የቀረቡ የአንድ የኢትዮጵያ ንጉሥ ሁለት የተለያዩ ስሞች እንደሆኑ በዘመኑ ቋንቋና ታሪክ ታዋቂ የሆኑ ምሁራን አስረድተዋል።[10]

ከዚህ የታሪክ ትንተና ሂደት፥ የአረቦቹ «ሀበሻ» የሚለው የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ስም በታሪክ ሰነድ ለመጀመሪያ ጊዜ

---

[7] Ibid., "Expeditions et Possessions", p. 18.

[8] Ibid., pp. 18-36; Kobishchanov, Axum, pp. 48-54; Sergew Hablesellassie, History, pp. 75-80; W. F. Jamme (tr., and ed.,), Sabaean Inscriptions from Mahram Bilqis (Marih), Baltimore, 1962.

[9] A Caquot et A. J. Drewes, "Les Momuments Recueillis A Maqalle", Annales D' Ethiopie, Vol. 1 (1955), pp. 35-39.

[10] Ibid., p. 39.

ተጽፎ የተገኘው ከዚህ «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» ተብሎ በተጠቀሰውና ለመጀመሪያው ጊዜ በ183 ዓመተ ምሕረት[11] በአረቢያ በሳባ ቋንቋና ፊደል በተጻፈ በአንድ የሃምዳኑ አረብ መስፍን ዜና መዋዕል ነው። ባጭሩ ሀበሻ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የአረቦች ስያሜ ነው።

በግምት ከ175 እስከ 225 ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ በአረቢያ እርስ በርሳቸው የግዛትና የሥልጣን ጠላት በሆኑ የሃምዳና፣ የሳባ፣ የሂሚያሪት፣ የቀጣባንና የሃድራማዊ አረብ መንግሥታትና የጦር አበጋዞች መካከል በተካሄደው ረጅም ጦርነት አገሮቹ በኃሳና በሥልጣን አንጃዎች ተለያይተው እየተዋጉ ብዙ ጊዜ በየግምባራቸው «የሀበሻት እና የአክሱማውያን ነገሥታት» ከሚሉዋቸው ገደረት፣ ዋዜባና አድባ አንድ ጊዜ የፖለቲካና የመገለጫ እርዳታ ሲፈልጉ በሌላ ጊዜ ደግሞ ጊዜያዊ የአረብ ኅብረት ፈጥረው ከኢትዮጵያውያኑ ጋር ሲዋጉ ይታያሉ።[12]

በመጨረሻ በ220ዎቹ የሂሚያሪት አናሳ መንግሥት የተቀሩ የአረብ ባላንጣ መንግሥታትን በውልም በውጊያም ተቆጣጥሮ ከዛፋር መዲናው በኢትዮጵያውያኑ የግዛትና የተፅዕኖ ሥር አንድ ጠንካራ የሂሚያሪት-ሳባ ጥምር የአረብ ኃይል መሠረተ።

በሌላ በኩል «የሀበሻትና የአክሱማውያን» መንግሥት በአረቢያ የቀይ ባሕርን ምሥራቃዊ ጠርፍ ክልል በሰሜን ምዕራብ ከሂጃዝ፣ ከአሲር እና ከቲሃማት ክልል ጀምሮ በደቡብ ምስራቅ እስከ የኤደን ወደብ ድረስ ማለትም የሂጃዝ-የመን ጠረፎችን በሙሉ በመቆጣጠር በምድርም በባሕርም ለሚቀጥሉት ብዙ ምዕተ ዓመታት የደቡብ አረቢያ የበላይ ኃይልና ሥርዓት ሆነ።[13]

በተጠቀሰው ዘመን የአክሱሙ የአጼ መንግሥት የአራቱ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ የዓባይ ሸለቆ፣ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አጎራባች ሕዝቦችና አገሮች የበላይ ኃይል ሆኖ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም ታሪክ ላይ የታወቀው በታላቁ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ ነው። ከላይ እንደተገለፀው፣ የዚህ የአዱሊስ ሐውልት ጽሑፍ የጻፈው ንጉሥ ስም ሆነ የተጻፈበት ዘመን እስከ ዛሬ ድረስ በትክክል አልተረጋገጠም።

ይሁን እንጂ ጽሑፉ የተጻፈበት ዘመን በ2ኛው ምዕተ ዓመት «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» አረቢያን ከገዛበት ጊዜ

[11] Conti Rossini, "Expedition et Possessions", p. 11; Kobishchanov, Axum, p. 50.

[12] Ibid., Axum, pp. 52-54.

[13] Ibid., 54.





በኋላና በ4ኛው ምዕተ ዓመት በ330 ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዘመን በፊት (በ300ዎቹ?) እንደሚሆን በኢትዮጵያ የዘመኑ ታሪክ ታዋቂ የሆኑ ምሁራን ይገምታሉ።[14]

የዚህ የአዱሊስ ጽሑፍ ግኝትና ቅጅ አስመልክቶ የግሪኮ-ግብፅ ጸሐፊ ኮስማስ ከ525 የአዱሊስና የአክሱም ከተሞች ጉብኝቱ መልስ እንደጻፈው፣ በተጠቀሰው ዓመት ከአክሱሙ አጼ ካሌብ የጽሑፉን ቅጅ አስገልብጦ እንዲልክለት አባስ ለተባለ የአዱሊስ ገዥ ትእዛዝ ይሰጣል። በታሪክ አጋጣሚ በዚህ ጊዜ ጸሐፊ መንገደኛው ኮስማስ ሚናስ ከተሰኘ ጓደኛው ጋር በንግድ ሥራ ምክንያት በአዱሊስ ከተማ ነበር።

በመሆኑም አገረ ገዥው አባስ የግሪኮ-ግብፅ ጸሐፊዎቹን ከሐውልቱ ጽሑፍ ለአጼ ካሌብ የሚልከውን ቅጅ እንዲያዘጋጁለት ጠየቃቸው። ጸሐፊዎቹም የጽሑፉን ሦስት ቅጆች አዘጋጅተው አንዱን ለአገረገዥው ሰጡ። የተቀሩ ሁለቱን ቅጅዎች ለራሳቸው አንዳንድ ወሰዱ። ኮስማስ የራሱን ቅጅ *የኮስማስ የክርስቲያን ቶፖግራፍ* በተሰኘ መጽሐፉ ገልብጦ ለትውልድና ለታሪክ መረጃ አስተላለፈ።[15] ነገር ግን ኮስማስ የጽሑፉን ደራሲ ሆነ የተጻፈበትን ዘመን ባለመጻፉ ሰነዱ መቼና በማን ተጻፈ የሚለው ቁልፍ የታሪክና የጊዜ ጥያቄ እስከ ዛሬ ድረስ አልተመለሰም።

ባጭሩ የታላቁ የአዱሊስ ጽሑፍ ርዕሰ ነገሮች ከጽሑፉ ገፅ ሆነ ይዘት በትክክል በማይታወቅ ዘመን በአንድ ስሙ በማይታወቅ የአክሱም ንጉሥ በአራቱ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ የዓባይ ሸለቆ፣ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አካባቢዎች በድምር በ30 በሚቆጠሩ አገሮች ላይ በምድርና በመርከብ ያካሄዳቸው ጦርነቶች[16] ናቸው። ከዚህ አኳያ፣ በመጀመሪያ ዘመቻ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በሰሜኑ ደጋአምባ ክልል በግምት በመረብ ወንዝና በጣና ሐይቅ መካከል በሚገኘው ምድር ንጉሡ ግዕዝ፣ አጋሜ፣ ስግዴ፣ አድዋ፣ ቲአሞ፣ ጋምቤላ፣ ዚንጋበነ፣ አንገበ፣ ትአማ፣ አገው (አታገው) ከሰና ሰሜን የሚላቸውን አሥራ ሁለት አዋማዊ አገሮችና መንግሥታት አስገበራቸው።

በሁለተኛው ዘመቻ በግምት በቀይ ባሕር፣ በአትበራ ወንዝ፣ በኑቢያ-ሜሮዌና በግብፅ መካከል ለዘን፣ ዘአ፣ ገበለ፣ አታልሞ፣ ቤጃና ተንገናይቴ (ታካ) የሚላቸውን ስድስት የተለያዩ የቤጃ አገሮች

[14] Ibid., pp. 41-43.

[15] Cosmas, Topography, pp. 55-56.

[16] Ibid., pp. 59-66; Kammerer, Essai Sur L'Histoire, pp. 57, 90.

ንና ማኅበረሰቦችን በማስገበር የመንግሥቱን የሰሜን ምዕራብ ወሰን በላይኛው የዓባይ ሸለቆ እስከ የግብፅ ጠረፎች ድረስ አስፋፋ።

በሦስተኛው ዘመቻ ጠረኛው ንጉሥ በክፍለ አህጉሩ ከትግራይ ደጋአምባ በደቡብ ምስራቅ በግምት ከአዋሽ ሸለቆ እስከ ቀይ ባሕርና የኤደን ባሕረሰላጤ ድረስ ባለው ቆላማና በጥንቱ ዓለም በዕጣን ምርትና ንግድ በታወቀ የትሮጅሎዳውያንና የበርበራውያን ምድር አነን፣ ምጤን፣ ሰለአ፣ ሮሳይና ሶስቴ የተሰኙ አምስት የቆላ ሕዝቦች ንና አገሮችን አስገበራቸው።

በአራተኛውና በመጨረሻው ዘመቻ የንጉሡ ጦር በመርከብ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በአረቢያ ረጅም ምዕራባዊ ጠረፍ ዳርቻ ላይ በሰሜን ምዕራብ ክልል በሚገኘው በሂጃዝ-አሲር አገር በዘመኑ የሮማውያን ይዞታ ከነበረ ከለኡኮመ ወደብ ጀምሮ በመሀል፣ በምስራቅና በደቡብ አረቢያ እስከ ሳባ-ሂሚያሪት ጠረፎችና እስከ ባብአልመንደብ ሰርጥ አካባቢ ድረስ ሙሉ ዘመቻ በማካሄድ በዘመኑ በሂጃዝ-አሲር ጠረፍ ኪናይዶኮልፕቴና በሂሚያሪት ጠረፍ አራብቴ የተሰኙ ሁለት እስትራቴጂያዊ አገሮችን የመንግሥቱ የባሕር ማዶ ግዛቶች አድርጎ በቀጥታ ያዘ። በዚህ ረገድና ተግባር ከዚህ በፊት «በሀበሾችና በአክሱማውያን ነገሥታት» ገደረት፣ ዋዜባና አድባ ዘመን በደቡብ አረቢያ በየመን ጠረፍ ሀበሻ የተባለ የኢትዮጵያውያን ግዛት እንደነበር አይዘነጋም።

የአዱሊስን ታሪካዊ ጽሑፍ ከጻፈው ንጉሥ ቀጥሎ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ በዓባይ ሸለቆ፣ በቀይ ባሕርና በአረቢያ አጎራባች አካባቢዎች የኢትዮጵያን መንግሥት በ4ኛውና በ6ኛው ምዕተ ዓመታት በኢኮኖሚ፣ በድርጅት፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በዲፕሎማሲና በትጥቅ ከጥንቱ ኩሻዊ የግብፅና የኑቢያ መንግሥታት ቀጥሎ የአፍሪካ ታላቁ ዓለማቀፋዊ ሥርዓት አድርገው የገዙት ሁለት አጼ ነገሥታት ኢዛና (320-344) እና ካሌብ (493-534) ናቸው።

በዚህ ረገድና ተግባር የኢትዮጵያ የመጨረሻ አዋማዊና የመጀመሪያ ክርስቲያን መሪ የሆነው አጼ ኢዛና በኢትዮጵያና በአረቢያ በግሪክ፣ በግዕዝና በሳባ ጥንታዊ ቋንቋዎች በተጻፉ ዜና መዋዕሎቹ (1) «ሰዎቼ» እያለ የሚጠራቸው መሀዛ፣ ሀራ፣ ደመወ፣ ፌልሀ፣ ፅራእ፣ ሀሌን፣ ምጤን፣ ዳኬን፣ ለኬንና ሰብራት የተባሉ የጦር ድርጅቶች፣ (2) «አባቶቼ» የሚላቸው አርስ፣ መሕረም፣ አስተር፣ ብሔር፣ ምድር፣ የሰማዩ አምላክ፣ ክርስቶስ፣ አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ተብለው በልዩ ልዩ ስሞችና ቋንቋዎች የሚታወቁ የውጭና የአገር ውስጥ አማልክት እንደነበሩት፣ (3) እንዲሁም «ግዕዝ»፣ «ካዕብ»፣ «ሳልስ»፣ «ራብዕ»፣





«ሐምስ»፣ «ሳድስ» እና «ሳብዕ»፣ የተሰኙ የኢትዮጵያ ልዩ የቋንቋ ድምፅ፣ ንግግርና ንባብ ሥዕላዊ የፊደል ምልክቶች ለመጀመሪያ ጊዜ በዘመነ መንግሥቱ እንደተገኙ የሰነዶቹ ጥናት ያሳያል።[17]

በተጨማሪም በተከተቡት የድንጋይ ላይ ጽሑፎች «የአክሱም፣ የሂሚያር፣ የረይዳን፣ የኢትዮጵያ፣ የሀበሻት (የሀበሾች)፣ የሳባ፣ የሰልሄን፣ የፅያሞ፣ የቤጃ፣ የካሱ ንጉሠ ነገሥት የድል አድራጊው መሕረም ልጅ»[18] የሚለው የአጼ ኢዛና የአገርና የመንግሥት ስም ንጉሡ በ4ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በ330ዎቹ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ከመግባቱ በፊት የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት የአራቱ አጎራባች የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ የዓባይ ሸለቆ፣ የቀይ ባሕርና የአረቢያ አገሮች ሉአላዊ የበላይ ኃይልና ሥርዓት እንደሆነ ያመለክታል።

ከእነዚህ ከኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ግዛቶች ሂሚያር፣ ረይዳን፣ ሀበሻ፣ ሳባና ሰልሄን የመንግሥቱ አምስት የአረቢያ ግዛቶች፣ እንዲሁም ፅያሞ፣ ቤጃና ካሱ የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ ግዛቶች፣ አክሱምና ኢትዮጵያ ደግሞ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በሰሜኑ ደጋአምባ ላይ የአጼው መንግሥት ማዕከላዊ ከተማና አገር ናቸው።

ከአጼ ኢዛና ዘመን 200 ዓመታት በኋላ በ6ኛው ምዕተ ዓመት በ530ዎቹ «የአክሱም፣ የካሱ፣ የረይዳን፣ የሳባ፣ የሰልሄን፣ የትአሞ፣ የየመን፣ የቲሃማት፣ የራባም፣ የቤጃ፣ የኖባ፣ የአራብት፣ ንጉሥ»[19] የሚለው የአጼ ካሌብ የአገርና የመንግሥት ስም በሁለቱም የአፍሪካና የእስያ አጎራባች አህጉራት የኢትዮጵያ መንግሥት ከአጼ ኢዛና ዘመን የበለጠ እንደተስፋፋ በግልጽ ያሳያል።

በአጼ ካሌብ ዜና መዋዕል ከተጠቀሱት ግዛቶች ረይዳን፣ ሳባ፣ ሰልሄን፣ የመን፣ ቲሃማት፣ ራባምና አራብት ሰባት የኢትዮጵያ መንግሥት የአረቢያ ግዛቶች ናቸው። በዘመኑ ቲሃማት[20] በሰሜን ምዕራብ ጠረፍ ከሂጃዝ በደቡብ ምስራቅ ጠረፍ እስከ የመንና ከዚያም ባሻገር ያለው ረጅም የደቡብ አረቢያ ምዕራባዊ ጠረፍ አጠቃላይ ስያሜ ነው። ካሱ፣ ትአሞ፣ ቤጃና ኖባ ደግሞ፣ ከሦስቱ ተከታታይ የአዱሊስ ሐውልት፣ የአጼ ኢዛናና የአጼ ካሌብ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች እንደ

---

[17] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፣ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ ገጽ 78-84

[18] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፣ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ ገጽ 68

[19] ላጵሶ ጌ ድሌቦ፣ የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ ገጽ 68

[20] H. T. Norris, "The Himyaritic Tihama: Evidence for a Multi-Racial Society in Pre-Islamic and Early Islamic Arabia," Abbay, No. 9 (1978), pp. 101,116; Kamal Salibi, The Bible Came From Arabia (London Jonathan Cape, 1985), pp. 38-39.

ሚታወቀው፣ በቤጃና በሚሮዋ ሕዝቦችና አገሮች ላይ እየሰፉ የመጡ የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ ግዛቶች ናቸው።

### *የ517-525 የይሁዳውያኑ አመፅ በአረቢያ*

### *በአረቢያ የኦሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች ጦርነትና ውድቀት*

በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ስድስት ምዕተ ዓመታት የኢትዮ-አረብ ታሪካዊ ግንኙነት በሚመለከት፣ በ130 ዓመተ ምህረት ደቡብ አረቢያ ከአፍሪካ በአንድ ጥቁር ኢትዮጵያዊ ንጉሥ ይገዛ እንደነበር ረቢ አቂባ የተባለ ይሁዳዊ ጸሐፊ በዓይኑ አይቶ በመጽሐፉ አረጋግጧል። ቀጥሎም በ170-220ዎቹ ሦስቱ «የሀበሾችና የአክሱማውያን» ነገሥታት ገደረት፣ ዋዜባና አድባ በሰሜን ምዕራብ ከሂጃዝ-አሲር በደቡብ ምስራቅ እስከ ኤደን የመን ድረስ የደቡብ አረቢያን ረጅም ምዕራባዊ ጠረፎችን ከሁለቱም ከምድርና ከባሕር በቀጥታ ይቆጣጠሩ እንደነበር በየመን ከጥንታዊ የማሪብ ከተማ በሳባ ቋንቋና ፊደል ተጽፈው በተገኙ ብዙ የአረብ ነገሥታት ዜና መዋዕሎች በስፋትና በዝርዝር ተገልጿል።

በተጨማሪም በ3ኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ገደማ የአዱሊስ ሐውልትን የግሪክ ጽሑፍ የጻፈው የአክሱሙ ንጉሥ በአረቢያ የቀይ ባሕር ጠረፍ ከልል ከሂጃዝ እስከ ሳባ የመን ድረስ በሚገኘው ምድር ኪናይዶኮልፒቴና አረብኤ በተሰኙ ሁለት እስትራቴጂያዊ ቀበሌዎች ላይ የፀጥታ ዘመቻ እንዳካሄደ በጽሑፉ በግልፅ ተቀምጧል።

በ4ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በአጼ ኢዛና (320-344) ዜና መዋዕል አምስቱ የሂሚያር፣ የረይዳን፣ የሀበሻ፣ የሳባና የሰልሂን ሕዝቦችና አገሮች በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት ግዛቶች እንደሆኑ ተመልክቷል። እንዲሁም ከአጼ ኢዛና ዘመን 200 ዓመታት በኋላ በ6ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በአጼ ካሌብ (493-534) ዜና መዋዕል ሰባቱ የረይዳን፣ የሳባ፣ የሰልሂን፣ የየመን፣ የቲሃማት፣ የአራብምና የአራብት ሕዝቦችና አገሮች በዘመኑ የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕር ማዶ ግዛቶች ሆነው ቀርበዋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ በ170-220ዎቹ ከላይ በስምና በተግባር ዝርዝር በተገለፁ አያሌ የደቡብ አረቢያ መንግሥታትና ማኅበረሰቦች መካከል ለረጅም ዘመን በተካሄዱ የጎሳ፣ የመሬት፣ የግዛትና የሥልጣን ጦርነቶች መጨረሻ ላይ የሂሚያር-ሳባውያኑ ጥምር መንግሥት በሂሚያሩ መሳፍንትና የጦር አበጋዞች አመራር በኢትዮጵያውያኑ የውጭ ተፅእኖ ሥር የደቡብ አረቢያ ጠንካራው የአረብ ኃይል ሆኖ እንደተነሳ





በአጠቃላይ መንገድና መልክ ይታወቃል። ይሁን እንጂ ከዝርዝር የታሪክ መረጃና እውቀት አኳያ፣ ከላይ ከተጠቀሱ የአዱሊስ ሐውልት፣ የአጼ ኢዛናና የአጼ ካሌብ ሰነዶችም ሆነ ከሌላ የመረጃ ምንጮች የተጠቀሰው የሂሚያር-ሳባ ጥምር አገርና መንግሥት ታሪካዊ ዕድገትና ሂደት ሁኔታ እስከ የይሁዳውያኑ የ517-525 ፀረ-ክርስቲያን አመፅ ድረስ ለ325 ዓመታት በትክክል አይታወቅም።

በሌላ በኩል፣ በተባለው ዘመን ከአፍሪካ ኢትዮጵያውያን ሰፋሪዎች በደቡብ አረቢያ በሂሚያር-ሳባ አገር ማለትም በየመን በሥፍራ፣ በጊዜና በቁጥር ተስፋፍተው እንደኖሩበት በዚህ ጥናት ከዚህ በላይና በታች የቀረቡ የታሪክ መረጃዎችና ትንተናዎች ያሳያሉ። በተጨማሪም በግምት ከ115 ዓመተ ዓለም እስከ 517-525 ዓም ድረስ ባለው የሰባት ምዕተ ዓመታት ዘመን ውስጥ ብዙ ይሁዳውያን[21] በፍልሳ መጥተው በየመን እንደሰፈሩ ታውቋል። እንዲሁም ከ4ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ የክርስትና ሃይማኖት በኢትዮጵያውያንና በሮማውያን አማካይነት ገብቶ በየመን አረቦችና በኢትዮጵያውያን ሰፋሪዎች ዘንድ እንደተስፋፋ የታሪክ መረጃና ጥናት ያሳያል።[22]

ከተግባር፣ ከታሪክና ከሥርዓት አኳያ፣ በ6ኛው ምዕተ ዓመት በደቡብ አረቢያ በሮማውያን፣ በፋርሳውያንና በኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት መካከል ለንግድና ለኃይል ሚዛን በተካሄደው ጂኦ-ፖለቲካዊ ትግል ሁለቱም የኦሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች በተፋላሚዎች ዘንድ የፖለቲካ መሣሪያዎች እንደተደረጉ ታውቋል። በአጼ መንግሥታቱ መካከል በተፈጠረው የፖለቲካና የኢኮኖሚ ግፊትና ግጭት የአገሩ የክርስትና ተከታይ አረቦችና የውጭ ሰፋሪ ክርስቲያኖች ከሮማውያንና ከኢትዮጵያውያን መንግሥታት[23] ወገን ተሰለፉ። ይሁዳዊ ሰፋሪዎችና አዋማዊ አረቦች ደግሞ ከሂሚያር-ሳባውያን አማፅያን ጋር ከፋርሳውያኑ የአጼ መንግሥት ወገን ሆኑ።

በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት ከዚህ በታች እንደሚታየው፣ በአካባቢው በሦስቱ የአጼ መንግሥታት መካከል የተፈጠረው የገበያና የኃይል ሚዛን ትግል እንዲሁም በሁለቱ መለኮታዊና አሀዳዊ የኦሪትና የክርስትና ሃይማኖቶች መካከል የተከሰተው ግጭት በአንድነት ባጭር

---

[21] Ibid., p. 22.

[22] Sergew Hablesellassie, History, pp. 126-27; Vassilios Christides, "The Himyarite-Ethiopian War and the Ethiopian Occupation of South Arabia in the Acts of Gregentius, Ca. 530 A. D.; Annales D' Ethiopie, Vol. 9 (1972), pp. 130-131.

[23] Ibid., The Acts of Gregentius, p. 119.

ጊዜ ውስጥ በአረቢያ ለሦስተኛው መለኮታዊና አሀዳዊ የእስልምና ሃይማኖት ክስተትና ዕድገት የየራሳቸውን አስተዋጽኦ ያደርጋሉ።

ከዚህ አኳያ በ517 በየመን አረቢያ አንድ ማዝሩቅ፥ ዙ ኑዋስ፥ ዩሱስ እና ፊንሃስ ተብሎ በልዩ ልዩ ስሞች የሚታወቅ ይሁዳዊ[24] የጦር አበጋዝ ማዕአድከርብ የተባለ የሂሚያርሳባ ንጉሥን ገልብጦ በምትኩ በራሱ መሪነት ይሁዳዊ የሂሚያር መንግሥት ለስምንት ዓመታት (517-525) በደቡብ አረቢያ መሠረተ።[25]

የይሁዳውያኑ የጦር አበጋዝ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ የሂሚያርን በትረ መንግሥት እንደያዘ በደቡብ አረቢያ በኢትዮጵያውያን፥ በሮማ ውያንና በአረብ ክርስቲያኖች ላይ የዘር፥ የቀለም፥ የቋንቋ፥ የጾታ፥ የዕድሜና የሙያ ምርጫና ልዩነት ሳያደርግ አጠቃላይ ግድያ ጀመረ። ለምሳሌም ኢትዮጵያውያን በሚኖሩበት የዛፋር ከተማ ውስጥ በአንድ የእልቂት ዘመቻ ብቻ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ 13,000 ሰዎችን ገደለ። 9,500 ሰዎችን ከ280,000 ግመሎች ጋር በምርኮ ወሰደ። የምዕመናንን ቤቶችና ቤተ ክርስቲያኖች በመደዳ አቃጠለ ተብሎ ተጽፏል።[26]

*የ517-525 የአረብ ስደተኞች በኢትዮጵያ*

በ517 ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ በአረቢያ በሕዝበ ክርስቲያን ላይ የጭፍጨፋ ዘመቻ እንደከፈተ የአረቢያ ክርስቲያኖች መሪና አስተማሪ አቡነ ቶማስ[27] ከናግራን ከተማ አምልጦ የአደጋውን ዜና በአክሱም ለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች በማድረስ አስቸኳይ የነፍስ አድን እርዳታ ጠየቀ።

በመሆኑም በግንቦት-ሰኔ 517 በንጉሥ የሚመራ ፈጣን የኢትዮጵያ የጦር ሠራዊት ቀይ ባሕርን በሰሜን ምዕራብ ጠረፍ ተሻግሮ የቲሃማትን ጠረፍ ያዘ።[28] ከቲሃማት ጠረፍ አገሩን ሲቆጣጠር ንጉሥ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ ግን በሽሽት አምልጦ ወደ አንድ ተራራ ገባ። የኢትዮጵያ መንግሥት ጦር ከቲሃማት ጠረፍ ተነስቶ የሂሚያርሳባ መንግሥትን የዛፋር መዲና በመያዝ ደቡብ አረቢያን በቀጥታ የኢትዮጵያ መንግሥት የባሕር ማዶ ግዛት አደረገ። ይሁን እንጂ በዓመቱ መጨረሻ ከፊሉ የኢትዮጵያ መንግሥት ሠራዊት ተመልሶ ወደ አገሩ ገባ።[29]

[24] Ibid., p. 136.
[25] Kobishchanov, Axum, p. 91.
[26] Sergew Hablesellassie, History, pp. 130-131.
[27] Kobishchanov, Axum, p. 91.
[28] Ibid.,
[29] Ibid., p. 92





ከኢትዮጵያ መንግሥት ሠራዊት ከፊሉ ከደቡብ አረቢያ እንደ ዚህ በችኮላ ወደ አገሩ ከተመለሰ በኋላ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ ከሸሸበት ተራራ ተመልሶ ከታህሳስ 517 እስከ ህዳር 518 ድረስ ሸረክህል ያክቡል ከተሰኘው የጦር አበጋዙ ጋር በአገሩ በየአከባቢው ማለትም በሙሃ፥ በዛፋር፥ በናግራን፥ በማሪብና በሃድራማዊ ከተሞችና ከሌሎች ክርስቲያኖችን በእሳትና በጎራዴ ስለት በመፍጀት እስከ 525 ድረስ አገሩን ለሰባት ዓመታት ተቆጣጠረ።[30]

ከ518 እስከ 525 ድረስ የኢትዮጵያ ንጉሥ አጼ ካሌብ በአገሩ ውስጥ በነበረው የፀጥታ ችግር ምክንያት በአረቢያ በይሁዳውያኑ እጅ የሚሰቃዩ ክርስቲያኖችን በዘመቻ ሄዶ ለመርዳት አልቻለም።[31] በዚህ ጊዜ በአረቢያ ከንጉሥ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ መከራና ስቃይ በመሸሽ የዘርና የሃይማኖት ልዩነት ሳያግዳቸው ከአረቢያ ብዙ አረቦች፥ ሮማ ውያንና ኢትዮጵጵያውያን ስፋሪዎች ወደ አክሱም በስደት እንደመጡ ተመዝግቧል።[32]

የንጉሥ ማዝሩቅ ዙ ኑዋስ የጦር አበጋዝ ሸረክህል ያክቡል አዋማዊ ወንድምና የታዋቂው ያዛን ጎሳ ተወላጅ ሱማፋ አሸዋን በኢትዮጵያ የስደተኞቹ ጉዳይ ኃላፊ ሆነ።[33] በ517 አዋማዊ የአረብ መስፍን ሱማፋ አሸዋን ከጦር አበጋዝ ወንድሙ ሸረክህል ጋር በማዝሩቅ ዙ ኑዋስ ወገን ሆኖ በክርስቲያኖቹ ላይ ጦርነት እንዳካሄደ ታውቋል።[34] ነገር ግን ከ517 በኋላ የማዝሩቅ ዙ ኑዋስ ጦርነት በአዋማዊ አረቦችም ላይ ጥቃትና ጥፋት ስለአደረሰ ሱማፋ አሸዋን ከሌላ ብዙ የአረብ ስደተኞች ጋር ወደ ኢትዮጵያ በስደት መጣ።[35]

*የይሁዳውያኑ የአረቢያ አመፅና ውድቀት*

የኢትዮጵያ ንጉሥና ጦር በአገር ቤት በተፈጠረው የፖለቲካና የፀጥታ ችግር ምክንያት ከግንቦት እስከ ሰኔ 517 የአረቢያ ዘመቻ በፍጥነት ወደ አገሩ እንደተመለሰ ታውቋል። አጼ ካሌብ በአገር ቤት የተፈጠረውን ችግር እስከ 523 ድረስ ተቆጣጠረ።[36] በመሆኑም በ524-525 በደቡብ አረቢያ በይሁዳውያኑ አማፅያን መንግሥት ላይ ሁለተኛውንና የመጨረሻውን የቅጣት ዘመቻ ለማካሄድ ተዘጋጀ።

[30] Ibid., pp. 92-94
[31] Ibid., pp. 95-96
[32] Ibid., pp. 99-100
[33] Ibid.,
[34] Ibid., pp. 99-100
[35] Ibid., p. 100
[36] Ibid., p. 96

በዚህ ረገድና ተግባር፥ በቅድሚያ በሚያዝያ-ሰኔ 524 አጼ ካሌብ በሂሚያሩ መስፍን ሱማፋ አሸዋን መሪነት በኢትዮጵያ የሚኖሩ የአረቢያ ስደተኞችን አስታጥቆ ወደ አገራቸው በመመለስ በይሁዳ ውያኑ አማፅያን ላይ አዘመታቸው።[37] በመጨረሻም በሰኔ-ሐምሌ 525[38] አጼ ካሌብ በራሱ መሪነትና አዝማችነት ሠራዊቱን በ70 መርከቦች አደራጅቶ በአዱሊስ ወደብ አጠገብ ከሚገኘውና ገበዘ ከተሰኘው ወደብ ቀይ ባሕርን ተሻግሮ በየመን የይሁዳውያኑን የአመፅ መንግሥትና ጦር በአንድ የግምባር ውጊያ ደመሰሰ።

ድል አድራጊው አጼ ካሌብ፥ የመን አረቢያን እንደገና የኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት አደረገው። ግዛቱንም እንዲመራ የሂሚያሩን ስደተኛ መስፍን ሱማፋን የክርስትና ልጁና በአረቢያ የመንግሥቱ እንደራሴ ንጉሥ (525-535) አድርጎ አነገሠ።[39] በተጨማሪም አጼ ካሌብ በንጉሥ ሱማፋ ሥር በጦርነቱ የፈረሰውን የአረቢያ ቤተ ክርስቲያን መልሶ እንዲያቋቁመው ከግብጹ ቤተ ክርስቲያን አንድ አቡነ ግሪገን ቲዩስ የተሰኘ የሃይማኖት መሪና አስተማሪ አስመጣ።[40]

*የኢትዮጵያ የ525-577 የደቡብ አረቢያ መንግሥት ዕድገትና ውድቀት*

በ525 አጼ ካሌብ በአንድ በኩል የአረብ መስፍን ሱማፋን በደቡብ አረቢያ የመንግሥቱ እንደራሴ ንጉሥ አድርጎ አነገሰ። በሌላ በኩል ደግሞ በአንድ የጦር አበጋዞች ጉባኤና ትእዛዝ የሚመራ ሠራዊት በአገሩ አሰፈረ።[41] በዚህ ጉዳይ በምንም ሥፍራና ጊዜ የአገሩን የተደራጀ ጦር የማይገዛ መንግሥት በሁኔታው ደካማ የፖለቲካ ሥርዓት ነው። ከሕግና ከኅብረተሰብ በላይ የሆነ የጦር ኃይል ደግሞ ውሎ ሳያድር ለመንግሥቱም ለኅብረተሰቡም የሰላምና የፀጥታ ጠንቅ እንደሚሆን የሥልጣኔ ታሪክና ልምድ ያስተምራል።

በመሆኑም በአረቢያ አጼ ካሌብ የፈጠረው የደካማ መንግሥት እና የጠንካራ ጦር ጥምር የፖለቲካ ሥርዓት ባጭር ጊዜ ውስጥ መጀመሪያ በራሱ በአረቢያ የሥርዓት ቀውስና ውድቀት ያስከትላል። ቀጥሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ በሶስቱ የሮማውያን፥ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት መካከል የኃይል ሚዛን ያዛባል። በመጨረሻም በአካባቢው ለተጠቀሱ የአጼ መንግሥታትና ለክርስትና

[37] Ibid., p. 100
[38] Ibid., pp. 78, 100-101; Sergew Hablesellassie, History, pp. 133-136.
[39] Ibid., Axum, pp. 102-103, 105.
[40] Christides, "The Himyarite-Ethiopian War", p. 137.
[41] Kobishchanov, Axum, pp. 102-1-3.





ሃይማኖት ውድቀት በአንድ በኩል፥ ለምዕተ ዓመታት በመንግሥታቱ ሲጨቆኑ ለኖሩ የአረብ ነገዶች እስላማዊ አመፅና ዓለማቀፋዊ እንቅስቃሴ በሌላ በኩል የራሱን አስተዋጽኦ እንደ ሚያደርግ ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ይታያል።

በዚህ ረገድና ተግባር በ517-525 በአረቢያ የይሁዳውያኑን ፀረ-ክርስቲያን አመፅ በማጥፋት ጦርነት ኢትዮጵያውያንና ሮማውያን የጋራ ስምምነት እንደነበራቸው ይታወሳል። በሌላ በኩል በዘመኑ በተለይ በ529-531 በመካከለኛው ምስራቅ የሮማውያንና የፋርሳውያን መንግሥታት በጦርነት ላይ እንደነበሩና በጦርነቱም ፋርሳውያኑ አሸና ፊዎች እንደሆኑ ታውቋል።[42]

በዚህም ምክንያት በ531 እና በ533 የሮማውያን መንግሥት ባለሥልጣኖች ከቁስጥንጥንያ መዲናቸው በቅደም ተከተል ዩሊያንና ኖኖሱስ በተሰኙ አምባሳደሮች የተመሩ ሁለት ተከታታይ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮኖችን በአክሱም ወደ አጼ ካሌብ፥ በዛፋር የመን ደግሞ ወደ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴው ንጉሥ ሱማፋ አሸዋን በመላክ በፋርሳውያኑ መንግሥት ላይ የሦስቱንም መንግሥታት አጠቃላይ ወታደራዊና ኢኮኖሚያዊ ጦርነት ለመክፈት ያልተሳኩ ሀሳቦችንና ዕቅዶችን አቀረቡ።[43]

የኢትዮጵያ መንግሥት ባለሥልጣኖች ግን በፋርሳውያኑ ላይ ከሮማውያኑ ጋር የጦርነት ግምባር ለመፍጠር ምንም አስፈላጊና በቂ ምክንያት አልነበራቸውም። ይልቁንም በደቡብ አረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት ጦር ባለሥልጣኖች የሮማውያን መንግሥት ባለሥልጣኖች በተንኮል ከኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ ሱማፋ አሸዋን ጋር በቀጥታ ዲፕሎማቲክ ግንኙነት ማድረጋቸውን በአንድ ሉአላዊ መንግሥት የውስጥ ጉዳይ ላይ ጣልቃ እንደመግባት አድርገው የወሰዱት ይመስላል።[44]

በዚሁ ዓለማቀፋዊ ሁኔታና ሂደት በ535 በደቡብ አረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት ሰፋሪ ጦር አዛዥ አብርሃ፥ እንደራሴ ንጉሥ ሱማፋ አሸዋንን በኩዴታ ገልብጦ በምትኩ ራሱን (535-558) አነገሠ።[45] በአመፁ ምክንያት ለቅጣት ከአክሱም የተላኩ ሁለት ወታደራዊ ዘመቻዎችን ንጉሥ አብርሃ አሸንፎ መለሳቸው። ነገር ግን በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ አላመፀም።

[42] Ibid., p. 103.
[43] Ibid., pp., 103-105,
[44] Ibid., pp. 105-106.
[45] Ibid.,

በ543፥ በየመን ደቡብ አረቢያ በጥንታዊው የማሪብ ከተማ ውሃ ግድብ ላይ በሳባ ቋንቋና ፊደል በድንጋይ ላይ ተጽፎ የተገኘ በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴና የጦር አበጋዝ ንጉሥ አብርሃ ዙፋናዊ የአገርና የመንግሥት ስም[46] «የሳባ፥ የዲሁረይዳን፥ የሃድራማዊ፥ የየመን፥ የቲሃማት፥ የደጋና ቆላ አረቦች ንጉሥ አብርሃ የነገደ ግዕዝ ተወላጅና አዝማች 'Rumahis Zabiyaman'»[47] ተብሎ በውርስ የአማርኛ ትርጉም ይነበባል።

ከስሙ ጋር ከቀረበ የአረብ አገሮች ዝርዝር፥ ከሰንዓ መዲናና ቤተ ክርስቲያን ግምባታ፥ ከ543 የማሪብ ከተማ ውሃ ግድብ ላይ ጽሑፉ፥ ከንግድ ፖሊሲውና እንቅስቃሴው፥ እንዲሁም በ547 ወደ መካ ካካሄደው ወታደራዊ ዘመቻ በግልፅ እንደሚታየው፥ ንጉሥ አብርሃ በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴና የጦር አበጋዝ በሰንዓ መዲናው ማዕከልነትና በክርስትና ሃይማኖት መሠረት መላ ምድረ አረቢያን በአንድ የአረብ መንግሥት ሥር የማድረግ ዓላማና ፖሊሲ ነበረው።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ የመንግሥትን ሥልጣን በኃይሉ እንደያዘ የደቡብ አረቢያ መዲናን ከጥንቱ የሂሚያር-ሳባውያኑ የዛፋር ከተማ በስተሰሜን የማሪብ ውሃ ግድብ አጠገብ ወደ አዲሱ የሰንዓ ከተማ አዛወረ። እንዲሁም በአቡነ ግሬንገቲዩስ ጠንካራ ትምህርትና ምክር በዛፋር፥ በሰንዓ፥ በማሪብ፥ በናግራንና በተለያዩ ሌላ የአገሩ ከተሞችና አካባቢዎች ብዙ አብያተ ክርስቲያናትን አሰራ። የማሪብን ጥንታዊ የውሃ ግድብ ብዙ የአረብ ነገዶችንና የሀገር መሪዎችን አስተባብሮ በከፍተኛ የሰው ጉልበትና የንብረት ወጭ አደሰ። የዕደሳው ሥራ በሁለት ወራት ሲጠናቀቅ ንጉሡ ለሠራተኞቹ ቀለብ 5,806 የዱቄትና 26,000 የተምር ጆንያ ዎችን፥ 3,000 ከብቶችንና 300 ግመሎችን ከ11,000 ዶሮዎች ጋር እንደሰጠ በሳባ ቋንቋ በድንጋይ ላይ በተጻፈ የግድቡ ረጅም ታሪክ ተገልጿል።[48]

የአገሩን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴና ዕድገት በሚመለከት፥ ንጉሥ

[46] Sergew Hablesellassie, History, p. 48.

[47] ከንጉሥ አብረሃ የአገርና የመንግሥት ስም ጋር "Rumahis Zabiyaman" ተብሎ የተጻፈውን ቃል/ሐረግ ዕውቁ የቋንቋና የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር (A. J. Drewes, Inscriptions, p. 108), "la lance dans sa main drite"? ብሎ በፈረንሳይኛ ሲያስቀምጥ ፕሮፌሰር (Kobishchanov, Axum, p. 107), ደግሞ "Spear of the Right Hand" በማለት ወደ እንግሊዝኛ መልሶታል። ይህን የምሁራኑን ትርጉም መሠረት በማድረግ "አዝማች" በሚል ውርስ ትርጉም ወደ አማርኛ መልሻለሁ። ላኪድ።

[48] Sergew Hablesellassie, History, p. 149.





አብርሃ በደቡብ ምስራቅ አረቢያ የመንን በመካከለኛው ምስራቅ ከፍልስጤምና ከሶርያ ጋር በኤደን፥ በሰንዓ፥ በናግራን፥ በጣይፍ፥ በመካ፥ በየትሪብ (የዛሬው መዲና) አገር አቋራጭ የሲራራ ንግድ መንገድና ሥርዓት አጠናክሮ አገናኘ። እንዲሁም በቀይ ባሕርና በሕንድ ውቅያኖስ የንግድ መስመር በእስያ፥ በአፍሪካና በአውሮፓ አህጉራት መካከል የሚካሄደውን የዓለም ንግድ እንቅስቃሴና ምንጭ ከኤደን ወደብ ተቆጣጣሪ ኬለኛ ንጉሥ ሆነ።

በተጨማሪም በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ በአቡነ ግሬገንቲዩስ ጠንካራ ትምህርትና ስብከት የአገሩን አዋማዊ አረቦችንና ይሁዳውያን ሰፋሪዎችን በኃይል ግፊትና በኢኮኖሚ ተፅእኖ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ለማስገባት ብርቱ የፖሊሲና የተግባር እርምጃዎችን ወሰደ።[49]

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ንጉሥ አብርሃ በሰንዓ መዲናው በአገሩ የሃይማኖት፥ የኢኮኖሚና የባህል ማዕከልና መሳቢያ የሚሆን አረቦች ቃሊስ ብለው የሚጠሩትን ታላቅ ቤተ ክርስቲያን ከቁስጥንጥንያ በመጡ ሮማውያን ሙያተኞች[50] እርዳታ በዕብነ በረድ፥ በወርቅ፥ በብር፥ በዝ ሆን ጥርስና በውድ እንጨት አስጊጦ ከሠራ በኋላ በአገሩ የሚኖሩ ሕዝ ቦች ሁሉ ከየአካባቢያቸው ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የስግደትና የስለት ጉዞና ጉብኝት እንዲያደርጉ የሚያስገድድ የፖሊሲ ሕግና ትዕዛዝ አወጀ።[51]

ነገር ግን እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ በአረቢያ ይህን ቅይጥ የሃይ ማኖት፥ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለመተግበር ሲጀምር በእስትራ ቴጂያዊው የመንሶሪያ አገር አቋራጭ የሲራራ ንግድ መንገድ ላይ ማዕከላዊ ኬላ በሆነ የመካ የንግድና የሃይማኖት ከተማ በመጽሐፍ ቅዱስ የአብርሃምና የኢስማኤል መቅደስ እንደሆነ የሚነገርለትና ለሕዝበ አረቡ ሁለአቀፍ የእምነት፥ የስግደት፥ የስለት፥ የገበያ፥ የትምህርትና የባህል መሠረትና ማዕከል የሆነ የከዕባ ጥንታዊ መቅደስ አንድ ታላቅ የፖለቲካ እና የባህል ችግር ፈጠረበት።

በመሆኑም፥ በ547[52] አረቦች በተረት የዝሆን ዓመት (ዓመልፊል) ብለው በሚያስታውሱት ዘመን፥ ንጉሥ አብርሃ የከዕባን መቅደስ ለማጥፋት በመካ አካባቢና በማዕከላዊ አረቢያ ላይ አንድ 60,000 ወታደሮችን ያቀፈና በዝሆን የሚጓዝ ታላቅ ሠራዊት አስከትሎ ያካሄደው ዘመቻ በመንገድ ላይ በተከሰተ የፈንጣጣ በሽታ ምክንያት

[49] Ibid., pp. 150-153.

[50] Kobishchanov, Axum, p. 106.

[51] Sergew Hablesellassie, History, pp. 150-151.

[52] Kobishchanov, Axum, p. 107.

ሳይሳካ ቀረ ተብሏል።[53]

ከዚህ በላይ በቀረቡ ልዩ ልዩ መንገዶችና መሣሪያዎች ደቡብ አረቢያን ከሦስቱ የሮማውያን፣ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን አጼ መንግሥታት ተፅእኖ ውጭ አንድ ጠንካራ የአካባቢ መንግሥት አድርጎ ለ23 ዓመታት ከገዛ በኋላ፣ እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ በ558[54] ሞተ።

እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ ዙ ያዛን የተባለ የሂሚያሩ መስፍንን ሬንሃባ የተባለች ቆንጆ ሚስትና ሰይፍ የተባለ የሁለት ዓመት ሕፃን እናት በሥልጣን ተፅእኖ የራሱ ሚስት አደረጋት። ሬንሃባ ለንጉሥ አብረሃም ያክሱምና ማዝሩቅ የተባሉ ሁለት ልጆች ወለደችለት። ሦስቱም የሴቲቱ ልጆች ሰይፍ፣ የአክሱምና ማዝሩቅ በአንድነት አብረው በቤተ መንግሥቱ እንዳደጉ ታውቋል።[55]

ከሬንሃባ ሦስቱ ልጆች፣ በአባቱ ወገን ይሁን በእናቱ መሆኑን ለይቶ በግልፅ ባያስቀምጥም፣ ፕሮፌሰር ኮቢሽካኖቭ አክሱም በተሰኘ ጥናቱ፣ ሰይፍ ዙ ያዛን የእንደራሴ ንጉሥ ሱማፋ አሸዋን የልጅ ልጅና የሂሚያር መስፍን እንደሆነ ገልጿል።[56] ውድ ሚስቱን ከሕፃን ልጁ ጋር በግፍ ከተቀማ በኋላ፣ ዙ ያዛን ከአገሩ ተሰዶ በሮማውያንና በፋርሳውያን መንግሥታት ዘንድ በአገሩ ላይ በሚካሄደው «የሀበሾች» አገዛዝ ላይ ለአሥር ዓመታት የአመፅ ፕሮፖጋንዳና ሴራ ሲያካሂድ ኖሮ በፋርሳውያኑ ቤተ መንግሥት በስደት እንደሞተ ታውቋል።[57] እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ እስኪሞት ድረስ ሰይፍ አብርሃን እንደአባቱ፣ ያክሱምንና ማዝሩቅንም ደግሞ እንደወንድሞቹ ቆጥሮ ይኖር ነበር። በ558 ንጉሥ አብርሃ በሞተ ጊዜ ትልቁ ልጅ ያክሱም ነገሠ። እርሱም በ562 ሞተ። ከንጉሥ ያክሱም ሞት በኋላ በማዝሩቅና በሰይፍ መካከል የከረረ የሥልጣን ትግል ተፈጠረ። በዚህ ወቅት ሰይፍ በማዝሩቅ የት አባክ ተብሎ ከተሰደበ በኋላ ከእናቱ አንደበት የዙ ያዛን ልጅ መሆኑን ለመጀመሪያ ጊዜ ሰማ። አባቱ ከአገሩ ተሰዶ እንዴት በፋርሳውያኑ ቤተ መንግሥት እንደሞተም አወቀ። በዚህ ጊዜ ሰይፍ ራሱ በስደት ወደ ፋርሳውያኑ ቤተ መንግሥት ሄደ። የአገሩን ነፃነት በሚመለከት በኢትዮጵያውያን ሰፋሪ ኃይሎች ላይ ከፋርሳውያን ባለሥልጣኖች ጋር የፖለቲካ ውልና ውሳኔ አደረገ።[58]

---

53 Sergew Hableselassie, History, pp. 151-153.
54 Kobishchanov, Axum, p. 107.
55 Sergew Hablesellassie, History, p. 153; Norris, "The Himyaritic Tihama," p. 105.
56 Kobishchanov, Axum, pp. 1110-111.
57 Norris, "The Himyaritic Tihamma", p. 105.
58 Ibid., pp. 105-106; Kobishchanov, Axum, 111.





በውሉም መሠረት በ577 ሰይፍ ዙ ያዛን ዋህሪስ በተሰኘ የፋርሳውያን ጦር አበጋዝ የሚመራ የ800 ምንደኞች ጦር በ8 መርከቦች አስከትሎ በኤደን ወደብ በር በየመን አረቢያ በኢትዮጵያ ሰፋሪዎች ላይ ወሳኝ ጦርነት ከፈተ። የፋርሳውያኑ ጦር የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ ማዝሩቅን ገደለ። ጦሩንም ደመሰሰ። አገሩንም ያዘ። ሰይፍ ዙ ያዛንንም የፋርሳውያን መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ አድርጎ በሰንዓ መዲና አነገሠ።[59] ንጉሥ ሰይፍ ዙ ያዛን በ517 ዙ ኑዋስ እንዳደረገው ሁሉ፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የእምነትና የሙያ ምርጫና ልዩነት ሳያደርግ፣ የእሱ የክብር ዘብ ከሚሆኑ ጥቂት ወታደሮች ሌላ፣ በየመን አረቢያ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን በያሉበት ሁሉ እንዲገደሉ አደረገ።

በየመን አረቢያ የኢትዮጵያውያንን ጦርና መንግሥት ደምስሶ በምትኩ ሰይፍ ዙ ያዛንን ካነገሠ በኋላ የፋርሳውያኑ ጦር አበጋዝ ዋህሪስ በድል ወደ አገሩ ተመለሰ። ዋህሪስ ወደ አገሩ እንደተመለሰ በ599 ገደማ ሰይፍ ዙ ያዛንም በኢትዮጵያውያን የክብር ዘበኞቹ ተገደለ። ይህ የኢትዮጵያ ወታደሮች አመፅ እንደተሰማ የፋርሳውያን ባለሥልጣኖች የጦር አበጋዝ ዋህሪስን ከ4,000 ወታደሮች ጋር የየመን አረቢያ ነዋሪ ገዥ አድርገው ላኩት። ከአገሩ መንግሥት በተሰጠው የፖሊሲ መመሪያ መሠረት፣ አገረ ገዥው ዋህሪስ ኢትዮጵያውያን ከአረብ ደጋፊዎቻቸው ጋር ከአገር በሞት እንዲጠፉ የምንጠራ ዘመቻ አካሄደ።

በዚህ ወቅትና ሁኔታ ከፋርሳውያኑ የዘር ማጥፋት ዘመቻ ካመለጡ ኢትዮጵያውያን ከፊሎቹ ባሕሩን ተሻግረው ወደ አገራቸው ገቡ። ከፊሎቹ ወደ አጎራባች የመካና የሂጃዝ አረብ አገሮች በመሰደድ ከአካባቢው የቁረይሽ አረብ ሕዝብ ጋር ወደኋላ የሚታየውን አዲስ የታሪክ ምዕራፍና ዘመን ይጀምራሉ።

## የኢትዮጵያና የቁረይሽ አረብ ግንኙነት መነሻና ዕድገት (577-610)

### *የኢትዮጵያውያኑ የሂጃዝ አረቢያ ስደትና ሰፈራ*

የእስልምና ሃይማኖት መሥራች ነቢዩ ሙሐመድና የቁረይሽ አረብ ተከታዮቹ የኢትዮጵያ መንግሥትና ዜጎች ከነናቸው በመሰለፍ በተፃራሪ ኃይሎች ላይ ለሃይማኖቱ ድል፣ ዕድገትና መስፋፋት በፖለቲካ፣ ለስደተኞች ጥገኝነት በመስጠት፣ በትጥቅ፣ በሥራ፣ በድርጅት፣ በትምህርትና በእምነት ሁለአቀፍ ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ እንዳደረጉ ለዓለምና ለታሪክ በይፋ አስታውቋል።

---

59 Ibid., "The Himiyaritic Tihama",

በተጨማሪም በቅዱስ ቁርአን - ቤት፥ ደም፥ ነፍስ፥ አፈር፥ አንቦሳ፥ መጽሐፍ፥ ድማምት፥ ፀሐይ፥ ዲያብሎስ፥ ሐዋርያ፥ የዋህ፥ ማዕድ፥ መናፍቅ፥ ብላኢ፥ ታቦት፥ ብርሃን፥ ጣኦት፥ ምኩራብ፥ መስኮት፥ ክፍል፥ ፈጠረና ደመደመ የተሰኙ የኢትዮጵያ የግዕዝ ቋንቋ ቃላት ከአረብኛ ጋር የሃይማኖቱ ትምህርት ባህላዊ መግለጫና መሣሪያ ሆነው አገልግለዋል።[60]

ይህ ልዩና ጠቃሚ የሆነ ቷሪክ ከሁሉ በፊትና በላይ በሁለቱ አጎራባች የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦች መካከል በቀይ ባሕር በርና ድልድይ አማካይነት ለረጅም ዘመን በመልክአ ምድር፥ በኢኮኖሚ፥ በጋብቻ፥ በቋንቋ፥ በባህል፥ በእምነትና በሥርዓት የተፈጠረ ጥልቅና ጥብቅ ግንኙነት ተግባራዊ ማስረጃና መግለጫ ነው።

ከታሪክና ከጊዜ አኳያ ይህ የኢትዮ-አረብ የቀረበ ግንኙነት ከዘመነ ክርስትና መባቻ ጀምሮ እስከ 577 ድረስ ለብዙ ምዕተ ዓመታት የኢትዮጵያ ጥንታዊ የአክሱም መንግሥት ከአቻ የሮማውያንና የፋርሳውያን የአጼ መንግሥታት ጋር በአካባቢው አንድ ዓለማቀፋዊ ኃይልና ሥርዓት በነበረበት ዘመን በየመን ደቡብ አረቢያ በሁለቱ አጎራባች የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦች መካከል እንዴት ተፈጥሮና አድጎ እንደ ዳበረ ከላይ በቀረበው ጥናታዊ ቢጋር ባጭሩ ተገልጿል።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ በ577 የመን ደቡብ አረቢያ በፋርሳውያን እጅ ከወደቀ በኋላ በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ በተጠቀሰው ረጅም የኢትዮ-አረብ ግንኙነት ታሪክ ላይ አዲስና ከፍተኛ የዕድገት አቅጣጫ፥ መንገድና ምዕራፍ ተከፈተ። በዚህ ረገድና ተግባር ከየመን ደቡብ አረቢያ በ577-600 በፋርሳውያን ከተባረሩ ኢትዮጵያውያን ብዙዎቹ ወዳገራቸው ተመለሱ። ከፊሎቹ ደግሞ በሰሜን ምዕራብ አረቢያ በሂጃዝ ግዛቶችና ከተሞች በተለይም በመሀል ሀገር በሚገኘው የመካ የንግድና የ360 ጣኦቶች ከተማ እንዲሁም ከመካ ከተማ በ70 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ከዛሬ የጅዳ ወደብ ከተማ በስተደቡብ በነበረውና ሹአይባ[61] በተሰኘው የሂጃዝ የቀይ ባሕር ወደብ ላይ በነዋሪነት ሰፍረው ከነባር የቁረይሽ አረብ ነገድ ጋር አዲስና ዘላቂ የሆነ ሁለአቀፍ የኢኮኖሚ፥ የባህልና ማኅበራዊ ግንኙነት ጀመሩ። ይህ በኢትዮጵያውያንና በአረቦች መካከል በሹአይባና በመካ የሂጃዝ ከተሞች የተፈጠረው አዲስ ግንኙነት በእስልምና ሃይማኖት ክስተት ዋዜማ ላይ በተለይም በንግድና በባህል መስኮችና መንገዶች በኃይል አድጎና ዳብሮ

60 ቅዱስ ቁርአን ያማርኛ ትርጉም «አዲስ አበባ 1961» መቅድም ገጽ 8፥11።

61 S. Hablesellassie, History, p; 154; R. Pankhurst, An Introduction to the Economic History of Ethiopia, (1961), pp. 49. 54.





ለሃይማኖቱ ዓለማቀፋዊ ዕድገትና መስፋፋት የሚያደርገው ልዩ የድል አስተዋፅኦ[62] ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ ይታያል።

*በእስልምና ክስተት ዋዜማ በሂጃዝ የኢትዮጵያና*

*የቁረይሽ አረቦች ታሪካዊ ግንኙነት*

በ535-558 በእስትራቴጂያዊው የመን አረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ንጉሥ አብርሃ በአዲሱ የሰንዓ መዲናው ማዕከልነትና በክርስትና ሃይማኖት መሠረት የተለያዩ የአረብ ማህበረሰቦችን፥ ነገዶችን፥ ክልሎችንና ባላባታዊ ግዛቶችን ባጎራባች የፋርሳውያን ተፃራሪ ኃይሎች ላይ በአንድ ማዕከላዊ መንግሥት ሥር ለማደራጀት በ547 በማዕከላዊና በሰሜናዊ አረቢያ በፋርሳውያኑ የአረብ ወኪሎች ላይና በመካ አካባቢ በሮማውያኑ የፖለቲካ ድጋፍ ያካሄዳቸውን ተከታታይ ወታደራዊ ዘመቻዎች ጨምሮ ብዙ የፖሊሲና የተግባር እርምጃዎችን እንደወሰደባቸው ከታሪክ መረጃና ትምህርት ይታወቃል።[63]

ነገር ግን ንጉሥ አብርሃ ከሦስቱ የሮማውያን፥ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት በተለይም ከፋርሳውያኑ የፖለቲካ ተፅእኖ ነፃ የሆነ አንድ ጠንካራ የአረብ አገርና መንግሥት ለመገንባት የነበረው ዓላማና ፖሊሲ በመጨረሻ በ577-600 የፋርሳውያኑ ጦር የመንን በያዘ ጊዜ ተደመሰሰ።[64] በዚህ ረገድና ተግባር፥ የፋርሳውያኑ ጦር ኢትዮጵያውያንን አሸንፎ ከየመን ደቡብ አረቢያ አባረረ። እንዲሁም የኢትዮ-ሂሚያር ጥንታዊ መንግሥትንና የንግድ ሥርዓትን አፈረሰ። በተጨማሪም እስከ 630 ድረስ የመን ደቡብ አረቢያ ራሱ የፋርሳውያኑ መንግሥት አንድ የጠረፍ አውራጃ (ማርዝፖኒት) እንዲሆን ተደረገ።

በመጨረሻም ፋርሳውያኑ በሕንድ ውቅያኖስና በቀይ ባሕር ዓለማቀፋዊ የንግድ መስመር በሦስቱ የእስያ፥ የአፍሪካና የአውሮፓ አህጉራትና ሕዝቦች መካከል በሚካሄደው ዓለማቀፋዊ የንግድ ሥርዓትና እንቅስቃሴ ላይ ማዕቀብ አደረጉ። ይህ የፋርሳውያኑ የኢኮኖሚ ፖሊሲና ተግባር በደቡብ አረቢያ ላይ ብቻ ሳይሆን በራሳቸው በሦስቱ የፋርሳውያን፥ የኢትዮጵያውያንና የሮማውያን የአጼ መንግሥታቱም ላይ አፍራሽ የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካና የፀጥታ ተጽዕኖ ያሳድራል። በዚህ ሁኔታና ሂደት የደቡብ አረቢያ ነባር የኢኮኖሚ፥ የፖለቲካ፥ የንግድና ማኅበራዊ ሥርዓቶች ሁሉ ፈረሱ። ይህ አካባቢያዊና ዓለም

63 Cuoq, Islam en Ethiopia, pp. 23-32; Kobishchanov, Axum,, pp. 113-114; Erlinch, Ethiopia and the Middle East, pp. 5-10; Norris, "The Himaritic Tihama", pp. 107-116.

63 Ibid., Axum, pp. 106-107; Doresse, Historoire Sommaire, pp. 101-102, 113-114.

64 Ibid., Histoire Sommaire.

አቀፋዊ ድርብ ሁኔታና ሂደት በ7ኛው ምዕተ ዓመት መባቻ ላይ በሦስቱ ተጠቃሽ የአጼ መንግሥታት ላይ ታላቁን የአረቦች አብዮታዊ ኃይል እንዴት እንደሚያስከትል ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ በስፋትና በዝርዝር ይታያል።[65]

በሌላ በኩል፣ ይህን መሰሉ የደቡብ አረቢያ ሁለንትናዊ ውድቀት ባንፃሩ በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ በተለያዩ የምድርና የባሕር አቋራጭ የንግድ ሥርዓቶችና እንቅስቃሴዎች በሚኖሩ የቁረይሽ አረቦችና በተለያዩ የኢትዮጵያ ሰፋሪ ማኅበረሰብ ክፍሎች - ነጋዴዎች፣ ወታደሮችና ባሮች - መካከል በንግድ፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በጋብቻና በሃይማኖት አዲስ የግንኙነት ሁኔታዎችን፣ ሂደቶችንና ኃይሎችን ይፈጥራል።[66]

በዚህ ወቅትና ሁኔታ በሁለቱ ማለትም የበረሃ አቋራጭ የየመን-ሶሪያ የሲራራ ንግድ መስመርና በቀይ ባሕሩ የአዱሊስና የሹአይባ አንጓራባች ወደቦች በኩል የሚያልፈው ድንበር-ዘለል የኢትዮ-ኢራቅ ዓለማቀፋዊ የንግድ መንገድ የመገናኛ ኬላ ላይ የሚገኘው የቁረይሽ አረቦች[67] የመካ ከተሜ-መንግሥት በፍጥነት አደገ። ይህ ትንሹ የመካ የንግድ ከተማና መንግሥት ባጭር ጊዜ ውስጥ ለምዕተ ዓመታት በሦስቱ የሮማውያን፣ የፋርሳውያንና የኢትዮጵያውያን የአጼ መንግሥታት መካከል የጂኦ-ፖለቲካ ትግል መድረክ በሆነው የአረብ ምድር ላይ የአረቦቹ ጠንካራ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የባህልና የትምህርት ማዕከል ቀጥሎም የታላቁ የእስልምና ሃይማኖት መካነ ልደት እንዴት እንደ ሚሆን ከዚህ በታች ይታያል።

በተጨማሪም በትንሹ የመካ የንግድና የሃይማኖት ከተማ ከየአካባቢው አዋማዊ የአረብ ነገዶችና ጎሳዎች ለስግደት፣ ለሥለትና ለንግድ የሚመጡበትና 360 ጣኦቶች የሚገኙበት ታላቁ የከዕባ[68] መቅደስ ተቋም ከኢስማኤል ምንጭ ጋር ለአዳጊ የቁረይሽ ነጋዴዎችና ባለሥልጣኖች አንድ ታላቅ የሀብትና የኃይል መሠረት፣ ማዕከልና መሣሪያ ይሆናል።

በአረቦቹ ትውፊታዊ እምነት መሠረት፣ በመካ ከተማ የከዕባ መካነ መቅደስ ከዛሬ 4000 ዓመታት በፊት በመጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ለአብርሃም[69] የተሰጠ ቅዱስ የስግደትና የስለት ቦታ

[65] Ibid., p. 114.

[66] Erlich, Ethiopia and the Middle East, p. 5.

[67] W. M. Watt, Muhammad et Mecca (1952), p. 3.

[68] Ibid., pp. 4-5.

[69] S. Hablesellassie, History, p. 152.





ነው። በዚህ ቅዱስ የከዕባ መካነ መቅደስ በዘመነ ክርስትና በ5ኛው ምዕተ ዓመት አንድ ቁሰይ የተሰኘ የቁረይሽ አረብ ባላባት የመካን ከተማ ለሕዝበ አረብ የሃይማኖት፣ የፖለቲካና የገበያ መሠረትና ማዕከል አድርጎ እንደቀረቀረው ታውቋል።[70]

የመካ ከተማ መሥራች ባላባት ቁሰይ - አብድቁሰይ፣ አብድ አዳር፣ አብድሜናፍና አብድአልኡዛ የተባሉ 4 ወንድ ልጆች ይወል ዳል። ከአራቱ የቁሰይ ልጆች አንዱ ማለትም አብድመናፍ በበኩሉ አብድሸምስ፣ ነውፈል፣ ሀሺምና አልሙጠሊብ የተባሉ አራት የነቢዩ ሙሐመድ አብደላህ (570-632) ቅድመ አያቶችንና በ6ኛው ምዕተ ዓመት በተለይም የመን ደቡብ አረቢያ በኢትዮጵያውያን አስተዳደር ሥር በከፍተኛ የዕድገት ደረጃና እንቅስቃሴ ሂደት ላይ በነበረበት ዘመን (525-577) የመካ ከተሜ-ኅብረተሰብንና መንግሥትን በንግድ፣ በሥራ፣ በሃይማኖትና በፖለቲካ ሥርዓት በከፍተኛ ደረጃ እንደገነቡ የሚነገርላቸውን የቁረይሽ አረብ ታዋቂ መሳፍንታዊ ጎሳዎችን መሠረተ።[71]

ከእነዚህ አራቱ የመካ ቁረይሽ መሳፍንታዊ ጎሳዎች (1) የአብድሸምስ ተወላጆች ከመካ ከተማ በደቡብ ግምባርና የሲራራ ንግድ መንገድ ከየመን የዕጣን ምርትና ንግድ አገር ጋር፣ (2) የአልሙጠሊብ ተወላጆች በምዕራብ ግምባር በሲራራና በባሕር ንግድ መስመሮች በቀይ ባሕሩ የአረብ ሹአይባና የኢትዮጵያ አዱሊስ አጎራባች ወደቦች በኩል በአፍሪካ አህጉር ከኢትዮጵያ ታላቅ የሰውና የተፈጥሮ ሀብት አገር ጋር፣ (3) የነውፈል ተወላጆች በምስራቅ ግምባርና የሲራራ ንግድ መስመር ከኢራቅና ከፋርስ አገሮች ጋር፣ (4) የሀሺም ተወላጆች ደግሞ በሰሜን ግምባርና የሲራራ ንግድ መንገድ በዘመኑ የሮማውያን ግዛቶች ከነበሩ የፍልስጤምና የሶርያ አገሮች ጋር ለመካው የቁረይሽ አረብ ከተሜ-ኅብረተሰብና መንግሥት ህልውናዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች የሆኑ የንግድ ዝብያዎችን፣ ፖሊሲዎችን፣ ስምምነቶችንና እንቅስቃሴዎችን በየበኩላቸው መሠረቱ።[72] በእስልምና ክስተት ዋዜማ እነዚህ አራቱ ዓለማቀፋዊ የንግድ መንገዶችና ዝብያዎች የመካ ከተሜ-ኅብረተሰብና መንግሥት የኢኮኖሚ መሠረቶችና መሣሪያዎች እንደነበሩ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል።

[70] Watt, Muhammad at Mecca, pp. 5. 30.

[71] Ibid., p. 7,

[72] Ibid., pp. 13, 30

ከማኅበራዊ ዕድገት መርህ አኳያ፣ በምንም ሥፍራና ጊዜ የዕድገት ደረጃ ምርጫና ልዩነት ሳይደረግ የአንድ የፖለቲካ ሥርዓትና ኅብረተሰብ ሁለት የተያያዙ መሠረቶችና መግለጫዎች የኢኮኖሚ ታሕታይና የፖለቲካ ላዕላይ መዋቅሮችና ድርጅቶች ናቸው።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ ከዛሬ 1400 ዓመታት በፊት በምድረ አረቢያ በአመዛኙ በእንስሳት እርባታ ተሰማርተው በዘላንነት በሚኖሩ የአረብ ነገዶች አገር ውስጥ በትንሹ የመካ የንግድና የጣኦት ከተሜ-ኅብረተሰብና መንግሥት ሊታላቁና የእስልምና ሃይማኖት ክስተትና ዕድገት ታሪካዊ መነሻ የሆነው ነገደ ቁረይሽ ከላይ ባጭሩ በተገለጸው ቅይጥ የሲራራ ንግድ ኢኮኖሚ፣ የመቅደስ አገልግሎትና የባሪያ ጉልበት የሚኖር አንድ አናሳ የፖለቲካ ማኅበረሰብ ነበር።[73] ባንፃሩ በተባለው የመካ ቁረይሽ አናሳ አገርና መንግሥት የዘላንም ሆነ የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚ ለዓይነት አልነበረም።[74]

በዘመኑ በተቀሩት የአረቢያ ክልሎች ከእንስሳት እርባታ ጎን ለምሳሌ በየመን ደቡብ አረቢያ የመስኖ እርሻና የዕጣን ምርት፣ ቢየትሪብ ማለትም በመዲና በኦአሲስ ምንጮች ሥፍራ የተምር ዛፍ ምርትና ንግድ እንዲሁም ከመካ የንግድና የጣኦት «ደሴት» አጠገብ ጣይፍ በተሰኘው ተራራማ ቀበሌ ከንግድና ከጣኦት ሥራዎች ጎን የተለያዩ የምግብና የንግድ ሰብሎች በዓይነትና በመጠን ይመረቱበት ነበር።[75] ነገር ግን በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን በትንሹ የመካ አገርና መንግሥት እነዚህ በምድረ አረቢያ የታወቁ የእንስሳት እርባታና የእርሻ ሥራዎች አልነበሩም።

ባጭሩ በዚህ በመካ ልዩ የንግድ፣ የጣኦትና የባሪያ ኅብረተሰብና መንግሥት ከንግድ ኢኮኖሚና ባህል ጋር አብሮ የሚፈጠረው የፋይናንስ አገልግሎት እንዲሁም የገንዘብ ወለድና የአራጣ ብድር ሥርዓት በሌላ ተመሳሳይ የከተማና የንግድ ኅብረተሰብ ዘንድ እንደ ሚያደርገው ሁሉ ባጭር ጊዜ ውስጥ በነቢዩ ሙሐመድ ትምህርት መሠረት ታላቅ ማኅበራዊ የሥርዓት ቀውስና ለውጥ ያስከትላል።[76]

በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን (570-632) የትንሹ መካ ከተማ ነዋሪዎችን የዘር፣ የቋንቋ፣ የባህልና የሃይማኖት ይዘት፣ ጥንቅርና ተግባር በሚመለከት ደግሞ ከተማው ከሞላ ጎደል የሁለት ልዩ ሕዝቦች ማለትም የቁረይሽ አረብ ነገድና የኢትዮጵያ ሰፋሪ ነጋዴዎች፣

[73] Ibid.,
[74] Ibid.,
[75] Ibid.,
[76] Ibid., pp. 3, 16-19.





ሙያተኞች፣ አስተማሪዎች፣ ወታደሮችና ባሮች መኖሪያ እንደነበር የነቢዩና የሃይማኖቱ መነሻ ታሪክ ያሳያል።[77]

በዚህ ረገድና ተግባር፣ ለምሳሌ በ6ኛው ምዕተ ዓመት በየመን ደቡብ አረቢያ የአዋማዊዝም፣ የኦሪትና የክርስትና ሃይማኖቶችን የሚከተሉ ነባር አረቦች ከሰፋሪ ኢትዮጵያውያን፣ ይሁዳውያን፣ ሮማውያን፣ ፋርሳውያን፣ አርመናውያንና ግሪኮች ጋር አብረው የሚኖሩበት አንድ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች አገር እንደነበር ከላይ በቀረበው የ517-535 የይሁዳውያን ጦርነት ታሪክ ተመልክቷል። እንዲሁም በዘመኑ ከመካ በስተሰሜን በሚገኘው የየትሪብ (የመዲና) የኦአሲስ ተምር ዛፍ ምርትና ንግድ አገር አዋማዊ አረቦችና የኦሪት ሃይማኖት የሚከተሉ ይሁዳውያን ሰፋሪዎች በእርሻ ኢኮኖሚ ተሰማርተው በአንድነት ይኖሩበት እንደነበር የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል።

በተጠቀሰው ዘመንና ሥርዓት በመካው የቁረይሽ አረቦች የንግድ፣ የጣኦትና የባሪያ አሳዳሪው ኅብረተሰብና ከተሜ-መንግሥት ግን ከኢትዮጵያውያን ሰፋሪ ነጋዴዎች፣ ሙያተኞች፣ አስተማሪዎች፣ ወታደሮችና ባሮች በስተቀር ሌላ የታወቁ የውጭ አገር ሕዝቦችና ሃይማኖቶች እንደነበሩ በግልፅ የሚያሳይ የታሪክ መረጃና ትምህርት እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም።[78]

በሌላ በኩል አረቦች ከጥንት ጀምሮ በዘልማድ «አልሀበሻ» ብለው በወል የሚጠሩዋቸው ኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ መስኮች፣ መንገዶችና ደረጃዎች የመካው ከተሜ-ኅብረተሰብና መንግሥት ውስጣዊ አባላትና አካላት እንደነበሩ በዝርዝር የሚያሳዩ ብዙ የሰው፣ የቋንቋ፣ የሰነድና የባህል መረጃዎችና ማስረጃዎች አሉ።

ከሁሉም በላይና በፊት በዚህ ወቅትና ጉዳይ ከ610 እስከ 632 ድረስ በ23 ዓመታት ውስጥ በመካና በመዲና ከፈጣሪው አላህ በመልአኩ ጅብሪል «ቅዱስ ገብርኤል» እንደበት ለነቢዩ ሙሐመድ በአረብኛ ቋንቋ የተገለጸው ቅዱስ ቁርአን የዘመኑን ታላላቅ የይሁዳዊ፣ የግሪክ፣ የፋርስና የላቲን ዓለማቀፋዊ ቋንቋዎችን ጨምሮ ከየትኛውም ሌላ ቋንቋ የበለጠ በኢትዮጵያ የግዕዝ ቋንቋ ተገልጿል።[79] ይህም ነቢዩ ሙሐመድ ከአረብኛ የእናት ቋንቋው ቀጥሎ በመካ ከተማው ከኢትዮጵያውያን ሰፋሪ ነጋዴዎች፣ ሙያተኞች፣ ወታደሮችና ባሮች

[77] Trimingaham, Islam in Ethiopia, p.44.
[78] Watt, Muhammad at Mecca, pp. 3, 5, 8-9.
[79] ቅዱስ ቁርአን ያማርኛ ትርጉም ገጽ 11።

ጋር አብሮ በመኖርና በመነጋገር የኢትዮጵያን የግዕዝ ቋንቋ ደህና አድርጎ ያውቅ እንደነበር ይጠቁማል።

## በእስልምና ምሥረታና ግምባታ የኢትዮጵያውያን ተሳትፎና የድል አስተዋጽኦ

### *የታሪክ መረጃ ምንጮች*

በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ በታላቁ የእስልምና ሃይማኖት ክስተት፣ ዕድገትና መስፋፋት ዘመን በሃይማኖቱ መሥራች ነቢዩ ሙሐመድና በኢትዮጵያውያን ደጋፊዎቹ መካከል በእምነት፣ በባህል፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በተግባር የተፈጠረውን የትብብር ታሪክ ለዓለምና ለትውልድ መዝግበው በማቆየት ባለውለታ የሆኑት የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች በከፊል የሚከተሉት ናቸው፡-[80]

ከእነዚህ ባለውለታ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች አንዱና የመጀመሪያው በ712 የሞተ፣ የነቢዩ ሙሐመድ ቤተዘመድና የካሊፋ አቡበክር (632-634) እህት አስማ ልጅ ኡርዋህ ዙቤይር (Urwah Zubayr) ለኡማያዱ ካሊፋ ለአብድ አልማሊክ (685-705) በጻፈው ደብዳቤ ነቢዩ ሙሐመድ የመጀመሪያ ሙስሊም ተከታዮቹ በእምነት ምክንያት በመካ የቁረይሽ ባለሥልጣኖች እጅ መከራና ሥቃይ ስለደረሰባቸው ሰላምና ፍትሕ ወዳለበት ወደ ኢትዮጵያዊው (ሀበሻው) ንጉሥ ነጃሺ አገር በጊዜያዊ ስደት ሂዱ ብሎ እንዳዘዛቸው ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፉ አረጋግጧል።[81] በተጠቀሰው ደብዳቤ፣ ኡርዋህ በዘመኑ የኢትዮጵያ አገር ለቁረይሽ አረቦች ታላቅ ሀብት፣ ሰላምና የሥራ ዕድል ያለበት ገበያ እንደነበር ጨምሮ አስታውቋል።

በ768 የሞተው ኢብን ኢስሓቅ የነቢዩ ሙሐመድን የሕይወት ታሪክ፣ በ822 የሞተው አልዋቂዲ የነቢዩ ሙሐመድን ዘመቻዎች ታሪክ፣ በ833 የሞተው ኢብን ሂሻም የነቢዩ ሙሐመድን የሕይወት ታሪክ፣ በ845 የሞተው ኢብን ሰይድ የነቢዩን ተከታዮች የሕይወት ታሪክ፣ በ870 የሞተው አልቡኻሪ የነቢዩን ሀዲሶች ማለትም ምርጥ ትውፊታዊ ንግግሮችና አባባሎች፣ በ922 የሞተው አልጣባሪ የነቢዩን ዜና መዋዕሎች፣ በ1234 የሞተው ኢብን አልአጢሂር የነቢዩን ተከታዮች የሕይወት ታሪክ፣ እንዲሁም በ1449 የሞተው የግብፁ የእስላም ሼክና የካይሮ ዋና ቃዲ ኢብን ሐጀር የነቢዩን ተከታዮች የሕይወት ታሪክ አስመልክተው በየበኩላቸውና በየዘመናቸው ባቀረቧ

[80] Watt, Muhammad at Mecca, pp. XI-XXI; Norris, "The Himyaritic Tihama", pp. 107-116.

[81] Ibis., Muhammad at Mecca, pp. 100-101.





ቸው ዘገባዎች፣ በ610-661 የእስልምና ሃይማኖት ክስተት፣ ዕድገትና መስፋፋት ዘመን ከባሪያ እስከ ንጉሠ ነገሥት ድረስ በልዩ ልዩ ማኅበራዊ መደቦችና ደረጃዎች የነበሩ ኢትዮጵያውያን የቦታ፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የቋንቋና የሙያ ልዩነት ሳይገድባቸው በመካ፣ በአክሱም፣ በመዲና፣ በፍልስጤም፣ በሶርያ፣ በግብፅ፣ በአርመን፣ በኢራቅና በፋርስ በነቢዩ ሙሐመድና በመጀመሪያ አራት ወራሽ ካሊፋዎቹ አቡበክር (632-634)፣ ዑመር፣ (634-644)፣ ዑስማን (644- 656) እና ዓሊ (656-661) ትምህርትና አመራር በተግራሪ የውስጥና የውጭ ኃይሎች ላይ ለሃይማኖቱ ፈጣን ማዕከላዊ ድልና ዕድገት በፖለቲካ፣ በዲፕሎማሲ፣ በትምህርት፣ በሥራ፣ በድርጅትና በትጥቅ ከፍተኛ ተሳትፎና የድል አስተዋፅኦ እንዳደርጉ በታላቅ አድናቆት መዝግበዋል።

በተጨማሪም በኋላ በመካከለኛው ክፍለ ዘመን ከተነሱ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች በተለይ ኢብን አልጀውዚ (1116-1200)፣ አልሱዩጢ (1402-1515) እና በ1583 የሞተው ሙሐመድ አልባቂ በአንድ ላይ በአራት ምዕተ ዓመታት ዘመን ውስጥ (1116-1583) ከላይ የተጠቀሱ ቀዳሚ የመረጃ ምንጮችን መሠረት አድርገው (1) *Ibn al-Jawzi, Tanwir al Gabash fi fadl al Sudan wal Habash, (2) Al Suyati, Rafshain, and (3) Al Bukhari, al-Tiraz al-Manqush fi Mahasin al-Hubush* በተሰኙ ርዕሶች ባዘጋጁት መጻሕፍት ከነቢዩ ሙሐመድና ከመጀመሪያ አራት ወራሽ ካሊፋዎቹ ጋር ተሰልፈው ለእስልምና ሃይማኖት ድልና ዓለማዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦካደረጉትና በሙስሊሙ ዓለም ታሪክ በታላቅ ክብር ከሚታወሱ ዕውቅ ኢትዮጵያውያን መካከል ከዚህ በታች ዝቅ ብሎ የሚቀርቡ ብዙ ባለታሪኮችን ስምና ታሪክ በወግ መዝግበዋል።[82]

### *የእስልምና ዓለም አቀፋዊ ክስተትና ዕድገት (610-661)*

በ610 በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ በመካ ጥንታዊ የእስማኤል ምንጭ፣ የአብርሃም መቅደስና የንግድ ከተማ፣ የቁረይሽ አረብ ተወላጅና የአርባ ዓመት ጎልማሳው ሙሐመድ አብደላ ከፈጣሪው አምላክ - አላህ በወረደ ቅዱስ ቁርዓንና በመልአክ ገብርኤል እንደበት በተገለፀው መለኮታዊ ራዕይ ለሰው ልጆች አዲስ ሃይማኖት ከአንዱ እግዚአብሔር ተቀብያለሁ በማለት የከተማ ነዋሪዎቹን አዋማዊ ሃይማኖትና በአራጣና በወለድ ትርፍ የተመሠረተ የንግድ ኢኮኖሚ ሥርዓት በማውገዝ ስብከቱን ጀመረ። የሃይማኖቱ መሠረተ ትምህርት፤ «የአላህ አንድነትንና የመሐመድ መልእዕተኝነትን ማመን፣ ጸሎት

[82] Norris, "The Himyaritic Tihama", pp. 107-116

(ስላት) መስገድ፣ ምጽዋት (ዘካት) መስጠት፣ የረመዳንን ወር መጾም፣ ሐጅ መድረስ አቅም ካለ» የሚል ነው። ይህ ታላቅ የነቢዩ ሙሐመድ መለኮታዊ ትምህርትና ስብከት በመካ ኃይለኛ ባለሥልጣኖችና ከበርቴ ነጋዴዎች ዘንድ በነቢዩና በተከታዮቹ ላይ ብርቱ ቁጣ፣ ተቃውሞና መከራ ስላስከተለ ነቢዩ በ615-16 በሁለት ተከታታይ ቡድኖች በድምሩ በ150 የሚቆጠሩና «ሙስሊሞች» ማለትም «እውነተኛ አማኞች» ተብለው የሚጠሩ ተከታዮቹን በአማቹ ዑትማን ቢን አፋንና በወንድሙ ልጅ ጀዕፈር አቡጣሊብ መሪነት «ራሳችንን ለመከላከል አላህ ብርታቱን እስከሰጠን ድረስ ወደ ሀበሻ አገር ሄዳችሁ እዚያው ቆዩ። የሀቀኞችና የጻድቃን አገር ናት። ንጉሷም ፍርድና ፍትሕ አዋቂና አስተዋይ ስለሆነ በእርሱ ዘንድ ማንም አይበደልምና አትስጉ»[83] በማለት በአፍሪካ ምድር ወደ ኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት አፄ አስሓማ (600-630) ቤተ መንግሥት በስደት ላልተወሰነ ጊዜ እንዲሄዱ አዘዛቸው።

የነቢዩ ሙሐመድ አሳዳጊ ሞግዚት የነበረችው በረካ ኡም እይማንን ጨምሮ ከስደተኛ ሙስሊሞቹ ሀያ አንዱ የመጀመሪያ ኢትዮጵያውያን ሙስሊሞች ነበሩ።[84] በአጼ አስሓማ የሚመራው የኢትዮጵያ መንግሥት ለሁሉም ስደተኛ ሙስሊሞች የጥገኝነት መብት እንዲሁም ለነቢዩ ሃይማኖትና ትምህርት በዓለም ላይ የመጀመሪያውን እውቅና ሰጠ። በመሆኑም በዚህ ታሪካዊ አጋጣሚ የእስልምና ሃይማኖት ከመካ መካነ ልደቱ ቀጥሎ በዓለም ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ አገርና ቤተ መንግሥት በይፋ ተሰበከ። ከስደተኛ ሙስሊሞቹ አብዛኞቹ በጃዕፈር አቡጣሊብ መሪነት እስከ 631 ድረስ ለ15 ዓመታት በኢትዮጵያ ከኅብረተሰቡ ጋር በባህልና በሃይማኖት ተቀላቅለው ኖሩ። ዑትማን ቢን አፋንን ጨምሮ ብዙዎቹ ደግሞ በፈቃዳቸው ወደ አገራቸው ተመልሰው ከነቢዩ ጋር በተፃራሪ ኃይሎች ላይ በመካና በመዲና የተሳካ የፖለቲካና የትጥቅ ትግል በማካሄድ ሃይማኖቱን በአገር ውስጥ አጠናከሩ። ከውድቀትና ከመጥፋት አደጋ በቆራጥነት አዳኑ።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ ነቢዩ ሙሐመድ ተከታዮቹን በ615-616 በስደት ወደ ኢትዮጵያ ከላካቸው በኋላ ራሱ ከመካ በደቡብ ምስራቅ በ110 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘውና ጣይፍ በተሰኘው ታዋቂ የንግድና የወይን እርሻ አገር ሃይማኖቱን ለማስፋፋት ያልተሳካ ሙከራ አደረገ። በወይን ምርትና ንግድ የታወቁ የጣይፍ አዋማዊ

[83] ሐሰን ዑመር አብደ «ሐበሻ ማንነው?» ፣ ጦቢያ ቅ 5 ቁ 4 (1989)፣ ገጽ 32

[84] Earlich, Ethiopia and the Middle East, p. 10.





አረቦች የነቢዩን መለኮታዊ ሃይማኖት ውግዘና ውድቅ አደረጉ። ራሱንም ከአገራቸው አባረሩት።[85]

በመጨረሻ፣ በመስከረም 622 ነቢዩ ሙሐመድ በመካ ከቁረይሽ ተፃራሪ ኃይሎች በድብቅ የግመል ጉዞ አምልጦ ከመካ በስተሰሜን በ430 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ወደሚገኘውና አረቦችና ይሁዳውያን በጉርብትና ወደሚኖሩበትና የትሪብ ተብሎ ወደሚጠራው የተምር እርሻ አገር በስደት ገባ።[86] የትሪብ አረቦችና ይሁዳውያን ስደተኛውን ነቢይ አስተማሪና መሪ አድርገው በሰልፍ በደስታ ተቀበሉት። የትሪብ የሚለው የአገራቸው ስም አሁን «መዲና» ማለትም «የነቢይ ከተማ» ተብሎ ተለወጠ። በተጨማሪም ነቢዩ ሙሐመድ ከመካ በስደት ወደ የትሪብ-መዲና የገባበት መስከረም 22 ቀን የሙስሊሙ ታሪክ መነሻ ዘመን «ሂጅራ» ተብሎ ተሰየመ።

ነቢዩ ሙሐመድ በስደት ከመካ ወደ መዲና እንደደረሰ ተከታዮቹ የሚተዳደሩበትን ባለ47 አንቀጽ «የመዲና ሕገ መንግሥት» መሠረተ።[87] በሕገ መንግሥቱም መሠረት ነቢዩ ሙሐመድ በመዲና ከተማ የሙስሊምና የይሁዲ ተከታዮቹን በኅብረት አስተባብሮ በ624[88] ገደማ «ኡማ» የተሰኘውን የሙስሊሞች መንግሥትና ኅብረተሰብ በይፋ በማቋቋም የመንግሥትን ሥልጣን በቀጥታ ያዘ። ነገር ግን በኋላ የመዲና ይሁዳውያን የነቢዩ ሙሐመድን ነብይነት ውድቅ ስለአደረጉ እርሱም በአጸፋ እርምጃ ከአገር አስወጣቸው።

በቅዱስ ቁርአንና በ624 የኡማ ሕገ መንግሥት ጥምር መሠረቶችና መሣሪያዎች፣ ነቢዩ ሙሐመድ በመካና በመዲና ተፃራሪ ኃይሎች ላይ ሁለአቀፍ የሃይማኖት፣ የዲፕሎማሲ፣ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የትጥቅ ግፊቶችንና እርምጃዎችን በመጠቀም በጥር 630 መካንና መዲናን የመንግሥቱ መንትያ ከተሞችና ክፍለ ግዛቶች አደረጋቸው።[89] የመካን ጥንታዊና አዋማዊ የጣኦት መቅደስንም ደግሞ ቀድሶ ወደ ታላቁ የመካ መስጊድ[90] ቀየረው።

ከሥርዓት፣ ከፖሊሲ፣ ከተግባርና ከጊዜ አንፃር ሲታይ፣ ነቢዩ ሙሐመድ በመካና በመዲና ከተሞችና አካባቢዎች የአረብና የይሁዲ ተፃራሪ ኃይሎችን በልዩ ልዩ መስኮች፣ መንገዶችና መሣሪያዎች

[85] Watt, Muhammad at Mecca, pp. 138-140.

[86] Ibid., p. ፲፭፲.

[87] Ibid., Muhammad at Medina, (1956), pp. 221-28.

[88] Ibid., 225-228.

[89] Ibid., pp. 40-69.

[90] Ibid., p. 69.

ሁሉንም አንድ በአንድ ተቆጣጥሮ በጥር 630 በአንድ እስላማዊ የኡማ መንግሥትና ኅብረተሰብ ሥር ባዋላቸው ጊዜ በቅዱስ ቁርአን ትምህርት መሠረት በ610 የጀመረው እስላማዊ የሃይማኖት፥ የመንግሥትና ማኅበራዊ አመፅና ለውጥ ወደ አንድ ከፍተኛ የዕድገት ደረጃ ደረሰ ለማለት ይቻላል።

በዚህ አኳያ ነቢዩ ሙሐመድ ከ610 እስከ 632 ድረስ በ23 ዓመታት ውስጥ በመካና በመዲና በሁለቱ የአረብና የይሁዲ ማኅበረሰቦች ዘንድ በቅዱስ ቁርአን ትምህርት መሠረት ያስተማረውንና ያደራጀውን ሁለአቀፍ እስላማዊ የሃይማኖት፥ የፖለቲካ፥ የኢኮኖሚ፥ የባህል፥ የሕግና ማኅበራዊ ሥርዓት ከ632 እስከ 661 ድረስ በሦስት አሥርታት የነቢዩ አራቱ ቤተዘመድና ወራሽ ካሊፋዎች አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑትማንና ዓሊ በሁለቱ አኅጉራት የእስያና የአፍሪካ አህጉራት የዘመኑ ኃያላን የነበሩ የፋርሳውያንና የሮማውያን የአፄ መንግሥታትን ደምስሰው በምትካቸው አንድ እስላማዊ የዓለም መንግሥትና ሃይማኖት መሠረቱ።

በዚህ ታላቅ ዓለማቀፋዊ የእስላም ሃይማኖትና መንግሥት ግምባታ ፖሊሲና ተግባር በዓለም ላይ ከቁረይሽ አረብ መሪዎችና አስተማሪዎች ጎንና ግምባር የቆሙ ደጋፊዎች የኢትዮጵያ መንግሥትና ተወላጆች ብቻ እንደሆኑ የታሪኩ ባለቤት የሆኑት አረቦች ራሳቸው ለታሪክና ለትውልድ በይፋ አስታውቀዋል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ነቢዩ ሙሐመድ ራሱ ለተከታዮቹ «ኢትዮጵያውያንን ሳይነኩዋችሁ አትንኩዋቸው፥ በግድ የማስለም ዘመቻ አታውጁባቸው» ብሎ የፖሊሲና የተግባር መመሪያ እንደ ሰጣቸው ተከታዮቹ ጨምረው አስታውቀዋል። እንዲያውም የተጠቀሱ ተከታዮች ከነቢዩና ከወራሽ ካሊፋዎቹ ጎን ተሰልፈው ከ610 እስከ 661 ድረስ ለሃይማኖቱ ድል፥ ዕድገትና መስፋፋት ታሪካዊ አስተዋፅኦ ያደረጉ ኢትዮጵያውያንን ስምና ሥራ በወግ ጽፈው ለታሪክና ለትውልድ እንደሚከተለው አቆይተዋል።

*የኢትዮጵያውያን ተሳትፎና የድል አስተዋፅኦ በእስልምና ምሥረታ*

አረቦች «የሀበሾችና የአክሱማውያን» ነገሥታት ገደረት፥ ዋዜባና አድባ የሚሉዋቸው የኢትዮጵያ የጥንቱ አዋማዊ ያገር መሪዎች በዘመነ ክርስትና በግምት ከሁለተኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ እስከ ሦስተኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ በየመን ደቡብ አረቢያ የነበራቸውን የባሕር ማዶ ግዛት ታሪክ የሳባ-ሂሚያር አረቦች በቋንቋቸው በድንጋይ ላይ ዜና መዋዕሎች ቀርፀው ለታሪክና





ለትውልድ እንዳቆዩ በዚህ ጥናት ከላይ ተመልክቷል።

አሁን ደግሞ በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ የጽሑፍ መረጃ ባልተገኘበት የ550-1300 ዘመን፥ በሂጃዝ ሰሜን ምዕራብ አረቢያ የቁረይሽ አረቦች የኢትዮጵያ መንግሥትና ተወላጆች በግምት ከ610 እስከ 661 ድረስ ባለው ዘመን ውስጥ ከነቢዩ ሙሐመድና ካልጋወራሽ ካሊፋዎቹ አቡበከር፥ ዑመር፥ ዑትማንና ዓሊ ጎን ተሰልፈው ለታላቁ የእስልምና ሃይማኖት ድል፥ ዕድገትና መስፋፋት ጉልህ ተሳትፎና የድል አስተዋፅኦ በማድረግ ሌላ ታሪክ በዓለም ደረጃ እንደሠሩ በሰነድ ቀርፀው ለታሪክና ለትውልድ እንደሚከተው አስታውቀዋል።

ከዚህ በታች በስም የቀረቡ ኢትዮጵያውያን በልዩ ልዩ መንገዶችና ደረጃዎች ከነቢዩ ሙሐመድና ከወራሽ ካሊፋዎቹ ጋር ተሰልፈው በእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ ዘመን (610- 661) ለሃይማኖቱ ድል፥ ዕድገትና መስፋፋት ተግባራዊ ተሳትፎና የድል አስተዋፅኦ ያደረጉ ሰዎች ናቸው። የስማቸውና የታሪካቸው ዝርዝር የተገኘው ከላይ ከተጠቀሱ ጥንታዊ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች ኡርዋህ ዙቤይር፥ ኢብን ኢስሐቅ፥ አልዋቂዲ፥ ኢብን ሂሻም፥ ኢብን ሰይድ፥ አጢታባን፥ አልአጢሂር፥ ኢብን ሐጀር፥ ኢብን አልጀውዚ፥ አልሱዩጢ፥ መሐመድ አልባቂና ሌሎችም በልዩ ልዩ ወቅቶችና መንገዶች ከቆዩዋቸው ሰነዶች በልዩ ልዩ ምሁራን ተለቅሞ ነው።

1. **Baraka Umm Ayman** <u>በረካ ኡም አይማን</u> የሕፃኑ ሙሐመድ አብደላ ኢትዮጵያዊት አሳዳጊ ሞግዚትና በኋላም የነቢዩ ሙሐመድ ሃይማኖት ተከታይ ሙስሊም ነበረች። በቅደም ተከተል በ875፥ በ989፥ በ1234፥ እና በ1277 የሞቱ ሙስሊም ኢብን ቁጠይባ፥ አጢሂርና ነዋዊ የተሰኙ የአረብ ታሪክ ጸሐፊዎች በየዘመናቸው እንዳረጋገጡት፥ በረካ ኡም አይማን ኢትዮጵያዊት ባሪያ ነበረች። ሌላ የታሪክ ምሁራን ደግሞ የነቢዩ ሙሐመድ አያት አብድአልሙጠሊብ በ543 ከየመን በመካ አካባቢ ዘመቻ ካካሄደው ከንጉሥ አብርሃ ክርስቲያን ሠራዊት በረካ ኡም አይማንን በምርኮ ይሁን በሌላ መንገድ እንደወሰዳት ጽፈዋል።[91]

ሕፃኑ ሙሐመድ ከነጋዴ አባቱ አብደላ አብድሙጣሊብና ከእናቱ አሚና ወሀብ በ570 ተወለደ። ሙሐመድ ከመወለዱ በፊት ነጋዴ አባቱ ከሶሪያ ሲመጣ በመንገድ እያለ በመዲና ሞተ። በመሆኑም ሕፃኑ ሙሐመድ ለመጀመሪያ ስምንት ዓመታት በተጠቃሹ አያት ዘንድ አደገ። የስድስት ዓመት ሕፃን ሳለ በ576 እናቱም ሞተች። ከሁለት ዓመታት በኋላ አያቱም ሞተ። አሁን ወላጅ አልባው ሙሐመድ በነጋዴ አጎቱ አቡጣሊብ አብድአልሙጠሊብ ዘንድ አደገ። እናቱ አሚና

[91] Norris, "The Himyaritic Tihama", pp. 107- 116; Erlich, <u>Ethiopia and the Middle East</u>, pp. 5- 10.

ስትሞት የቤተሰቡ ኢትዮጵያዊት ባሪያ በረካ ኡም አይማን የሙሐመድ አሳዳጊ ሞግዚት ሆነች። በኋላ ባለውለታው ሙሐመድ ሞግዚት እናቱን ከባርነት አርነት አውጥቶ ዘይድ ለተባለው አበልጁ ዳራት።[92]

በ595 ሙሐመድ ራሱ በ25 ዓመቱ በመካ የአርባ ዓመት ዕድሜ ባልቴትና የራሱም ቀጣሪ የነበረችውን ነጋዴ ወይዘሮ ከድጃን አግብቶ ከሷም ዘይነብ፥ ሩቅያ፥ ኡም ኩልቱማና ፋጢማ የተሰኙ አራት ሴትና ቃሲም፥ አብደላና ጣሂር የተባሉ ሦስት ወንድ ልጆቹን ወለደ። በረካ ኡም አይማን ለሙሐመድ ሚስት ከድጃ አገልጋይ እንዲሁም ለተጠቃሽ ልጆቹም አሳዳጊ ሞግዚት ሆነች። በተጨማሪም በረካ ኡም አይማን የነቢዩ ሙሐመድን የእስልምና ሃይማኖት መጀመሪያ ከተቀበሉ ሙስሊሞች አንዷ ነበረች።

በመሆኑም፥ በ615-16 ከመካ ወደ ኢትዮጵያ ከተሰደዱ የነቢዩ ሙሐመድ ተከታዮች መካከል በረካ ኡም አይማንና ልጁ ሩቅያ አብረው ነበሩ። የነቢዩ አብዛኛዎቹ ተከታዮች ወደ ኢትዮጵያ ከተሰደዱ በኋላ በ620 በመካ ሚስቱ ከድጃና አጎቱ አቡጣሊብ ተከታትለው በሞት ተለዩት። በ622፥ ከላይ እንደተመለከተው፥ በመካ ከቁረይሽ ጠላቶቹ በሽሽት አምልጦ ራሱም ወደ መዲና ገባ። በረካ ኡም አይማን ከኢትዮጵያ ስደት ከተመለሰች በኋላ በመዲና ከነቢዩ ጋር እንደገና አብራ መኖር ጀመረች። በዚህ ጊዜ ሁሉ ነቢዩ በረካ ኡም አይማንን እንደወላጅ እናቱ አድርጎ ይወዳትና ይጠራት ነበር። ከነቢዩ ሞት በኋላ አልጋወራሽ ካሊፋዎቹ አቡበከርና ዑመር ለበረካ ኡም አይማን ተመሳሳይ እንክብካቤ ያደርጉላት ነበር። እሷም የነቢዩን ብዙ ሀዲሶች ማለትም ምርጥ ትውፊታዊ ንግግሮች ለተከታዮቹ ታስረዳ እንደነበር ተጽፏል።

2. Bilal ibn Ribah <u>የረባሕ ልጅ ቢላል</u> ሙዓዚኑ (610-644)፥ የዘመኑ ታሪክ ጸሐፊዎች እንዳስታወቁት ሁሉ፥ በ610 በራዕይ የተገለፀለትን የነቢዩ ሙሐመድን መለኮታዊ የእስልምና ሃይማኖት የመጀመሪያው ደጋፊና ተከታይ ሚስቱ ከድጃ ስትሆን፥ ሁለተኛው አቡበከር የነቢዩ ሦስተኛይቱ ሚስት አይሻ አባትና የመጀመሪያው አልጋወራሽ ካሊፋ (632-634) እንደሆነ ተገልጿል። በአቡበከር አማካይነት የነቢዩ መሐመድ ትምህርትና ሃይማኖት ተከታይ ከሆኑ ሰዎች አንዱ ኢትዮጵያዊው ባሪያ የረባሕ ልጅ ቢላል ሙዓዚኑ እንደሆነ ታውቋል።[93] በእነዚሁ ታሪክ ጸሐፊዎች ቃል መሠረት፥ ቢላል በመካ የአንድ የቁረይሽ ከበርቴ ባሪያ ነበር። ቢላል የነቢዩን እስላማዊ ትምህርትና ሃይማኖት መከተሉን በመቃወም አሳዳሪ ጌታው በከፋኛ እንደ ሚያሰቃየው የነቢዩ ተከታይ አዛውንቱ አቡበከር ይሰማል። ከዚያ በኋላ አቡበከር ቢላልን ከጌታው ገዝቶና አርነት አውጥቶ

ወደ ነቢዩ ይወስደዋል። የእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ ዘመንና ተግባር፥ «ቢላል አል-ሀበሻ» ማለትም ኢትዮጵያዊው ቢላል ከነቢዩ ታላላቅ የሃይማኖትና የጦር ባለሥልጣኖች አንዱ ሆነ። በመጀመሪያ ደረጃ ከሩቅ የሚሰማ ከፍተኛ ድምፅ ያለው ሰው ስለሆነ፥ ቢላል አል-ሀበሻ የመጀመሪያው የሙስሊሞች ሙዓዚን (አቃቤ ፀሎት) ለምዕመናን የሰዓተ ስግደትን ጥሪ በድምፅ የሚያሰማ ኃላፊ ሆነ። በተጨማሪም ሙዓዚኑ ቢላል ታላቅ የሃይማኖት ጦር አበጋዝ ሆነ። በዚህ ረገድና ተግባር ቢላል አል-ሀበሻ በካሊፋ ዑመር ዘመንና አመራር (634-644) እስልምናን በመላው መካከለኛው ምሥራቅና በግብፅ ያስፋፋው የሙስሊም ጦር ሠራዊት አንድ አርበኛ ወታደር በመሆን ሲዋጋና ሲያዋጋ በ642 በደማስቆ ሶርያ ሞተ። መካነ መቃብሩም እስከ ዛሬ ድረስ በደማስቆ የሙስሊሙ ዓለም አንድ ቅዱስ ሥፍራ ሆኖ እንደሚገኝ ታውቋል።[94]

3. The Negash: <u>አጼ ነጃሺ አስሓማ፥</u> የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት፥ ከላይ እንደተጠቀሰው፥ አጼ ነጃሺ አስሓማ (600-630) በነቢዩ ሙሐመድ ፈቃድና ትእዛዝ በ615-616 ከመካ አረቢያ በስደት ወደ አገሩ ለገቡ የመጀመሪያ ሙስሊም ስደተኞች የጥገኝነትና የሃይማኖት ነፃነት መብት እንዲሁም ለእስልምና ሃይማኖት በዓለም ላይ የመጀመሪያውን የእምነትና የፖለቲካ እውቅና የሰጠው ኢትዮጵያዊ አስተዋይ የአገርና የመንግሥት መሪ ነው። የዘመኑ የአረብ ጸሐፊዎች በ628 በነቢዩ የደብዳቤ ጥሪ መሠረት አጼ አስሓማ ወደ እስልምና ሃይማኖት መግባቱንና በ630 በሞተም ጊዜ ነቢዩ ስምቶ ለሙስሊም ሙታን የሚደረገውን ፀሎተ ቅዳሴ በመዲና እንዳደረገለት ጽፈዋል።

4. Luqman the Wise: <u>ጠቢቡ ሉቅማን</u> በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን (610-632) በመካ አረቢያ አንድ ወደ ከፍተኛ የትምህርትና የጥበብ ደረጃ የደረሰ ብሎም ለእስልምና ሃይማኖት ድልና ዕድገት ታላቅ አስተዋጽኦ ያደረገ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም እንደሆነ ተገልጿል።[95]

ነቢዩ ሙሐመድ በሀዲስ ቃሉ ማለትም በትውፊታዊ ቃሉ፥ ሦስቱ ማለትም ጠቢቡ ሉቅማን፥ ነጃሺ አስሓማና ቢላል ሙአዚኑ ከእኛ ጋር መንግሥተ ሰማያት የሚወርሱ «ሱዳኖች» ማለትም ሀበሾች (ኢትዮጵያውያን) ስለሆኑ እንደወንድሞቻችሁ አድርጋችሁ ተቀበሉዋቸው ብሎ ለአረብ ሙስሊም ወገኖቹ እንዳስተማራቸው የዘመኑ ታሪክ ጸሐፊ ኢብን አባስ[96] ጽፏል።

የነቢዩ ሙሐመድን «ሱዳን» የሚለውን ቃል ግንዛቤና ትርጉም በሚመለከት፥ ታዋቂ የጥንቱ አረብ ሙስሊም ምሁራን እንደሚያስተ

[92] Ibid., "The Himyaritic Tihama", p. 114.
[93] Earlich, Ethiopia and the Middle East, p. 6.

[94] Ibid., p. 10.
[95] Norris, "The Himyaritic Tihama", pp. 108-109, 117.
[96] Ibid., p. 108.

ምሩት፣ «ሱዳን» እና «ሀበሽ» ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያውያን የአረቦቹ ሁለት ተለዋጭ ስሞች ናቸው።[97] ለምሳሌ በ1450 የሞተው የግብፁ ታዋቂ ምሁር ኢብን ሀጀር የእስልምና ሼክና የካይሮ ዋና ቃዲ ከእሱ በፊት በ870 በሞተው አልቡኻሪ የተጻፈውን የነቢዩ ሙሐመድን የትውፊት ቃልና ትምህርት ሲያስረዳ እንዳለው፣ በዘመኑ የኢትዮጵያውያን ምድር በአረቢያ ከየመን በደቡባዊ ምዕራብ በኩል የሚገኝ አገርና መንግሥት ነበር። የአገሩም ሕዝቦች የተለያዩ «የሱዳን» ዘሮች ናቸው። በአገሩ የሚኖሩ ሁሉም የሱዳን ሕዝቦች ለሀበሾቹ ንጉሥ ቓይታዘዙሉ። ንጉሡም በጥንት ዘመን «ነጃሺ» በ15ኛው ምዕተ ዓመት በሼክ ቃዲ ኢብን ሀጀር ጊዜ ግን «ሐጼ» ተብሎ ይጠራ እንደነበር በታሪካዊ መረጃና ትንተና አስረድቷል።[98]

5. Mihja ibn Saleh: የ<u>ሳልህ ልጅ ሚህጃ</u>፣ በ610 ነቢዩ ሙሐመድ ከአላህ የእስልምና ሃይማኖት ራዕይ ከተቀበለ በኋላ ዑመር ኢብን አልኸጣብ ዳግማዊ ካሊፋ (634-644) አርነት ያወጣው ኢትዮጵያዊ ባሪያና ከነቢዩ መጀመሪያ ሙስሊም ተከታዮቹ አንዱ ነበር። ሚህጃ በ615-16 ነቢዩ ሙሐመድ በስደት ወደ ኢትዮጵያ ከላኳቸው ሙስሊሞች አንዱ ሲሆን በ624 በበድር ጦር ሜዳ ላይ በአዋማዊ ቁረይሾችና በነቢዩ ሙሐመድ ተከታዮች መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ በተካሄደውና ሙስሊሞቹ የመጀመሪያ ድል በተቀዳጁበት ታሪካዊ ጦርነት የመጀመሪያው ሙስሊም ሰማዕት ሆነ።[99]

6. Saleh Shukran ibn Ali: የ<u>ዐሊ ልጅ ሳልህ ሹቅራን</u>፣ ሳልህ ሹቅራን ኢብን ዐሊ ነቢዩ ሙሐመድ ከአንድ የቁረይሽ ከበርቴ ገዝቶ አርነት ያወጣው ኢትዮጵያዊ ባሪያ ነበር። በ624 የበድር ጦርነት ጊዜ ሳልህ ሹቅራን የጠላት ምርኮኞችና ንብረት ጠባቂ ሹም ሆነ።

7. Nafi Abu Bakra ibn Masruh: የ<u>ማዝሩህ ልጅ ናፊ አቡበክራ</u>፣ ናፊ አቡበክራ ማዝሩህ አርነት ወጥተው የነቢዩ ሙሐመድ ከፍተኛ ተከታዮችና ባለሟሎች ከሆኑ ብዙ የቀድሞ ኢትዮጵያዊ ባሮች አንዱ ነበር። አርጅቶ በ675 ከመሞቱ በፊት ናፊ አቡበክራ ከነቢዩ ሀዲሶች ማለትም ትውፊታዊ ንግግሮችና አባባሎች 132ቱን ለታሪክና ለትውልድ በቃሉ ያሳለፈ ባለውለታ ነው።

8. Aslum al-Habashi: <u>አስሉም አል-ሀበሽ</u> (ሀበሻው አስሉም) አስሉም አልሀበሽ በመዲና ለአንድ ይሁዳዊ ባሪያ የነበረ ኢትዮጵያዊ ነው። የነቢዩ ሙሐመድ ተከታይ ወታደር ከሆነ በኋላ በ629 በከይበር በይሁዳውያንና በነቢዩ ተከታይ ሙስሊሞች መካከል በተካሄደው ጦርነት ሞቷል።

97 Ibid., p. 109.
98 Ibid., pp. 108-109.
99 Ibid., p. 111.





9. Khalid ibn Alhawari al Sabachi: <u>ካልድ ኢብን አልሀዋሪ አልሰበኪ</u>፣ ከነቢዩ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ ነበር።

10. Alaswas al Habash: <u>አልአስዋስ አልሀበሽ</u> ከነቢዩ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ እንደነበር ተመልክቷል።

11. Dhu Mihdem, Dhu Muhammas, Dhu Mukhbir, Dhu Dawjayn, and Dhu Munahib: <u>ዙ ሚህደም፣ ዙ ሙሐመስ፣ ዙ ሙክቢር፣ ዙ ዘውጃይንና ዙ ሙናሀብ፣</u> ዙ የተሰኘ የአረብ ማዕረግ ያላቸው አምስት የነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሹማምንቶች ነበሩ።

12. Asim al-Habashi: <u>አሲም አልሀበሽ</u>፣ ከነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ ነበር።

13. Nayil al-Habashi: <u>ናይል አልሀበሽ</u>፣ ከነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዱ።

14. Abu 'lQit al-Habashi: <u>አቡ ልቂጥ አልሃበሽ</u>፣ የነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታይ ነበር።

15. Yassar al-Habashi: <u>ያሣር አልሀበሽ</u>፣ የነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታይና የመስገድ ፅዳት ሠራተኛ ነበር።

16. Wahshi al-Habashi: <u>ዋሕሽ አልሀበሽ</u>፣ የነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታይና በጦር ውርወራና ውጊያ ዕውቅ ወታደር ነበር።

17. Bulaha al-Habashiya: <u>ቡለሀ አልሀበሺያ</u>፣ የነቢዩ ሙሐመድ ሚስት የኡም ሀቢባ ኢትዮጵያዊት ሙስሊም ሠራተኛ ነበረች። ኡም ሀቢባ ነቢዩ ሙሐመድንና የእስልምና ሃይማኖቱን ለማጥፋት ያልተሳካ ሙከራ ያደረገ የቁረይሽ መንግሥት መሪ አቡሱፍያን ልጅ ናት። ከአዋማዊ አባቷ አቡሱፍያ ተለይታ የነቢዩ ሙሐመድን የእስልምና ትምህርትና ሃይማኖት ከተቀበለች በኋላ ኡም ሀቢባ በታዋቂ መስፍንና ሙስሊም ባልዋ ዑበይ ዑበደላ ጃህሽ ጋር በ615-16 በስደት ወደ ኢትዮጵያ ሄደች። ነገር ግን በኢትዮጵያ ባልዋ ዑበይ ዑበደላ ጃህሽ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የእስልምና ሃይማኖቱን ትቶ በፈቃዱ ወደ ክርስትና ሃይማኖት ገባ። በመሆኑም ኡም ሀቢባ ከዑበይ ዑበደላ ጃህሽ ጋር ለረጅም ጊዜ የመሠረተችውን የጋብቻ ትዳር አፍርሳ የእስልምና ሃይማኖት ስደተኛ እንደሆነች ቆየች።

በመዲና ነቢዩ ሙሐመድ በኡም ሀቢባ የአቡሱፍያን ልጅ በሃይማኖት ልዩነት ከመስፍን ባልዋ ጋር የመሠረተችውን የረጅም ጊዜ ጋብቻ አፍርሳ መለያየቷን እንደሰማ በአክሱም የአጎቱ ልጅና የስደተኛ ተከታዮቹ መሪ ጃዕፈር አቡጣሊብንና የኢትዮጵያ አፄ አስሓማን በእርሱና በባልቴቷ ሀቢባ መካከል ሥርዓተ ጋብቻ ለመፈጸም አማላጆች እንዲሆኑለት ጠየቃቸው።[100] ኡም ሀቢባም በአማጮቹ አስተባባሪነት ከነቢዩ

100 Earlich, <u>Ethiopian and the Middle East</u>, p. 80.

የቀረበላትን የጋብቻ ጥያቄ በደስታ ተቀበለችው። ንጉሡም ነቢዩ በጠየቀው መሠረት ኡም ሀቢባን እንደአገሩ ባህል 400 ዲናር ጥሎሽ ከፍሎ ዳራት።[101]

በመሆኑም በ628 በመዲና አረቢያ ነቢዩ ሙሐመድና ኡም ሀቢባ አቡ ሱፍያን ሥርዓተ ጋብቻ ፈጸሙ።[102] ሰደተኛዋ ኡም ሀቢብ አቡሱፍያን ከኢትዮጵያ ወደ መዲና ለጋብቻ ስትሄድ ኢትዮጵያዊት ቡለህ አልሀበሺያን እንደሠራተኛዋ ይዛ ሄደች።[103] በዚህ መንገድ ቡለህ አልሀበሺያ ከነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ታዋቂ ሙስሊም ተከታዮች አንዷ ሆነች።

በተጨማሪም በዚህ በሙሐመድና ኡም ሀቢባ የፖለቲካ ጋብቻ ምክንያት በወቅቱ (624-630) የቁረይሽ አዋማዊ መንግሥት መሪ የነበረው የኡም ሀቢባ አዋማዊና ተቃዋሚ አባት አቡሱፍያን በልጁ ብርቱ ግፊት በአዋማዊ የቁረይሽ ሕዝብና መንግሥት ላይ በምሥጢር ከነቢዩ ሙሐመድ ጋር ሆኖ ተገኘ።[104] በመሆኑም በመጨረሻም በጥር 630 ነቢዩ ሙሐመድ መካን አለውጊያ ያዙ።[105] መካ በተያዘ ቀን አቡሱፍያን በመዲና በነቢዩ ሠፈር ነበር።

18. **Barira al-Habashiya:** <u>በሪራ አልሀበሺያ</u>፣ በነቢዩ ሙሐመድ ሦስተኛይቱ ሚስትና የቀዳማዊ ካሊፍ አቡበከር ልጅ አይሻ ብርቱ ድጋፍ ራሷን ከአንድ የቁረይሽ አሳዳሪ ጌታዋ አርነት አውጥታ ከዕውቅ የነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንድዋ ሆነች።

19. **Shagira al-Habashiya:** <u>ሸግራ አልሀበሺያ</u>፣ ከአንድ የቁረይሽ አሳዳሪ ጌታዋ አርነት ወጥታ ከነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዷ ሆነች።

20. **Nabgha al-Habashiya:** <u>ነብጋ አልሀበሺያ</u>፣ የነቢዩ ሙሐመድ አጎት አቡጣሊብ ልጅ ኡም ሀኒ ባሪያ የነበረችና አርነት ወጥታ ከነቢዩ ዕውቅ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ተከታዮች አንዷ ለመሆን የበቃች ሴት ናት።

21. **Aslum al-Bujawi:** <u>አስሉም አልቡጃዊ</u>፣ ዳግማዊ ካሊፋ ዑመር (634-644) ከባርነት አርነት አውጥቶት በ114 ዓመት ዕድሜው በ702 የሞተ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ነው።

22. **Ayman al-Habashi al-Makki:** <u>አይማን አልሀበሽ አልመኪ</u>፣ አንድ ከባርነት አርነት የወጣ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ነው።

23. **Ata ibn Abi Ribah Aslum al Nakki:** <u>አጣ ኢብን አቢ ረበህ</u>

[101] <u>Ibid</u>.,

[102] Watt, <u>Muhammad at Medina</u>, p. 396,

[103] Norris, "The Himyaritic Tihama", p. 115.

[104] Watt, <u>Muhammad at Medina</u>, pp. 63-64.

[105] <u>Ibid</u>., pp. 65-70.





<u>አስሉም አልናቂ</u> አንድ ሌላ ከባርነት የወጣ ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ነው።

በኢትዮጵያ የ615-631 የነቢዩ ሙሐመድን የሙስሊም ስደተኞች ሕይወትና ሥራ በሚመለከት፣ በመጋቢት 1904 በአዲስ አበባ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የቱርክ የመጀመሪያ ልዑካን ቡድን መርቶ የመጣው ሌ/ጄ ሰድቅ አልሙአያዩ አልዐዝም በዓመቱ *Habesh Siyahetnamehsi* በሚል ርዕስ በቱርክኛ ቋንቋ ጽፎ በ1908 *Rihlat al Habasha (The Ethiopian Voyage)* ጉዞ በሚል ስም ወደ አረብኛ ቋንቋ በተተረጎመው ተወዳጅ መጽሐፍ የጥንት አረብ ሙስሊም ጸሐፊዎችን ሰነዶች በስፋትና ጥልቀት መርምሮ ብዙ አዲስና ጠቃሚ መረጃዎችን እንዳቀረበ በቅርቡ በአንድ ምሁራዊ ጥናት ተገልጿል።[106]

የቱርኩ ጄኔራል በአዲስ አበባ ቆይታው ወቅት ከሁሉ በላይ የአገራቸውን ታሪክ በወግ ለማያውቁ ለኢትዮጵያ ባለሥልጣኖች የአገራቸው የጥንት መንግሥትና ሕዝብ ነቢዩ ሙሐመድን በእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ ተግባር እንዴት በልዩ ልዩ ሥራዎች፣ መንገዶችና መሣሪያዎች እንደረዱት ለመጀመሪያ ጊዜ በማሳወቅ በእጅጉ አስደነቃቸው።[107]

ሁለተኛ፣ የጄኔራል አልዐዝም ጥናት በ615-631 በኢትዮጵያ ከነበሩና በድምሩ በ150 ከሚቆጠሩ የነቢዩ ሙሐመድ ሙስሊም ስደተኞች ከበረካ ኡም አይማን ጋር አምስት ሴቶችን ጨምሮ ሃያ አንድ በዘርና በትውልድ ኢትዮጵያውያን እንደነበሩ ያሳያል። በተጨማሪም የተባሉ ኢትዮ-አረብ ሙስሊም ስደተኞች በ615-631 በኢትዮጵያ በነበሩበት ዘመን ብዙ ኢትዮጵያውያንን ወደ እስልምና ሃይማኖት እንደመለሱ የጄኔራሉ ጥናት ጨምሮ ያመለክታል።[108]

ሦስተኛ፣ በዚህ ረገድና ተግባር በ631 በነቢዩ ሙሐመድ ወንድም ልጅ በጃዕፈር ሙጠሊብ መሪነት ስደተኞቹ ወደ አረቢያ በተመለሱ ጊዜ ከተጠቀሱት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ነቢዩን ለመርዳት 72 ወዶ ዘማቶች በአጼ አስሓማ ወንድም ልጅ በዙ ማህጃር አልሀበሽ፣ የቀድሞ ኢትዮጵያዊ የአረቢያ ንጉሥ አብርሃ (535-558) የልጅ ልጅ አብርሃ ቢን ሰባህ አልሀበሽና በአንድ ዕውቅ የታሪክና የቅኔ ባለሙያ በዙ ማህጃር አልሀበሽ አዝማችነት ከስደት ተመላሾች ጋር አብረው እንደሄዱ ተገልጿል።[109]

[106] Earlich, <u>Ethiopia and The Middle East</u>, pp. 10, 79-82.

[107] <u>Ibid</u>., p. 81.

[108] <u>Ibid</u>., p. 10.

[109] <u>Ibid</u>.,

ከእነዚህ ከኢትዮጵያ ከፍተኛ የመንግሥትና የጦር ሹማምንቶች አንዱ በዙ ማህጀር አልሀበሽ ለነቢዩ ሙሐመድ የኢትዮ-አረብ ጥንታዊ ታሪክ ያስተምር ነበር ተብሏል።[110]

*በቁረይሽ አረቦች ጦርነት የኢትዮጵያ ሀበሾች ማንነትና ሚና*

የእንግሊዙ ታሪክ ጸሐፊ ሞንትጎማሪ ዋት ጥንታዊ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎች ኡርዋህ ዙቤይር፣ ኢብን ኢስሓቅ፣ አልወቂዲ፣ ኢብን ሂሻም፣ ኢብን ሰይድ፣ አጢታባሪና ብዙ ሌሎችም ያቆዩዋቸውን የጽሑፍ መረጃዎች ብቻ አጥንቶ ማለትም ዘመናዊ የአርኪኦሎጂና የሊንጉዊስቲክስ (የሥነልሳን) ማጠናከሪያ መረጃዎችን ሳይጨምር የነቢዩ ሙሐመድን የሕይወት፣ የሃይማኖት፣ የትምህርትና የሥራ ታሪክ በሚመለከት ሙሐመድ በመካ፣ ሙሐመድ በመዲና በተሰኙ ርዕሶች በ1950ዎቹ ባዘጋጃቸው መጻሕፍት (W. M. Watt, Muhammad at Mecca, 1953; Muhammad at Medina, 1956), በ624-630 በመካና በመዲና ከተሞች በአዋማዊና በእስላማዊ የቁረይሽ አረብ ጎሳዎች መካከል በተካሄደው የሃይማኖትና የእርስ በርስ ጦርነት111 ወገንና ጠላት ሆነው በራሳቸው ጦር፣ ድርጅት፣ ትጥቅና ስንቅ የተዋጉትንና በአረቦች ሀበሻ፣ አልሀበሽ፣ አሀብሽ[112] አልአሀብሽ፣ ሀበሻትና አልሁብሻት ተብለው በነጠላና በብዙ ስሞች የሚጠሩ ሰፋሪ ኢትዮጵያውያንን እንደአንድ «ምሥጢራዊ አሀብሽ» (the mysterious Ahabish)[113] የተሰኘ አንድ የአረብ ማኅበረሰብ (tribeless people) አድርጎ ለማቅረብ ሞክሯል።[114]

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል በ1966 በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው የኢትዮጵያ ዓለማቀፋዊ ጥናት ሦስተኛ ጉባኤ «ደቡብ አረቢያና ኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ የፈረንሳዩ ምሁር ፕሮፌሰር ሰርጂ፣ (R. B. Serjeant "South Arabia and Ethiopia") የተለያዩ ጥንታዊና ዘመናዊ የመረጃ ምንጮችን አገናዝቦ ባቀረበው ሚዛናዊ ጥናት እንዳለው፣ ከላይ በአረቦቹ የተጠቀሱ የአገርና የሕዝብ ስሞች ቢያንስ በዓመተ ዓለም ከመጀመሪያው ምዕተ ዓመት ጀምሮ ከምድረ አፍሪካ በወታደራዊ ዘመቻና ሰፈራ ገብተው በደቡብና በሰሜን ምዕራብ አረቢያ በቲሃማት ጠረፍ ክልል ማለትም በየመንና በሂጃዝ ጠረፎች አካባቢ በሰፈራ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተሰጡ ስያሜዎች

110 Ibid.,

111 Watt, Muhammad at Medina, pp. 10-77.

112 Watt, Muhammad at Mecca, pp. 10-11.

113 Ibid., p. 156.

114 Ibid., pp. 154-157.





ናቸው።[115]

የአረቦቹ በነጠላ ሀበሻ፣ አል-ሀበሽ፣ በብዙ ሀበሻት፣ ሁብሻት የተሰኙ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ስሞች ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪክ ሰነድ ተጽፈው የተገኙበት ዘመን፣ ከላይ እንደተመለከተው፣ በዘመነ ክርስትና በ2ኛው ምዕተ ዓመት በ183 በሳባ ቋንቋና ፊደል በድንጋይ ላይ ተቀርጸው በየመን ደቡብ አረቢያ ከማሪብ ጥንታዊ የሳባ ከተማ በተገኙ የአረብ ዜና መዋዕሎች «የሀበሻት እና የአክሱማውያን» ነገሥታት ገደረት፣ ዋዜባና አድባ በተባሉና አረቢያን ይገዙ በነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት ታሪክ ነው። ቀጥሎም፣ (1) በ320-344 በግዕዝ፣ በግሪክና በሳባ ቋንቋዎችና ፊደሎች ተጽፈው «የአክሱም፣ የሂሚያር፣ የረይዳን፣ የኢትዮጵያ፣ የሀበሻት[116] የሳባ፣ የሰልሂን፣ የፅያሞ፣ የቤጃ፣ የካሱ ንጉሠ ነገሥት የድል አድራጊው መሕርም ልጅ» የሚሉ ብዙ የአፄ ኢዛና ዜና መዋዕሎች፣ (2) በ493-534 በግዕዝ ቋንቋና በሳባ ፊደል ተጽፎ «የአክሱም፣ የካሱ፣ የረይዳን፣ የሳባ፣ የሰልሂን፣ የቲአሞ፣ የየመን፣ የቲሃማት፣ የራባም፣ የቤጃ፣ የኖባ፣ የአራባት ንጉሥ» የሚለው የአፄ ካሌብ ዜና መዋዕል፣ (3) በ535-558 በደቡብ አረቢያ በሳባ ቋንቋና ፊደል በድንጋይ ላይ ተጽፎ ከማሪብ ጥንታዊ ከተማ የተገኘውና «የሳባ፣ የዱሁረይዳን፣ የሃድራማዊ፣ የየመን፣ የቲሃማት፣ የደጋና የቆላ አረቦች ንጉሥ አብርሃ የነገደ ግዕዝ ተወላጅና አዝማች» የሚለው በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴና የጦር አበጋዝ ንጉሥ አብርሃ መንግሥታዊ ስምና ሥልጣን በአንድነት ከላይ ከተጠቀሰው የኢትዮጵያ ጥንታዊ ነገሥታት ገደረት፣ ዋዜባና አድባ ታሪክ ጋር በዘመኑ በኢትዮጵያውያንና በአረቡ አጎራባች ሕዝቦች መካከል በኢኮኖሚ፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካና በባህል ሰምዕተ ዓመታት ለነበረው ግንኙነት ታሪካዊ መረጃዎች ናቸው።

በሁለቱ የአፄ ካሌብና የንጉሥ አብርሃ ዜና መዋዕሎች የተጠቀሰው የቲሃማት አረቢያ የጠረፍ አውራጃ በዘመኑ በሰሜን ምዕራብ አረቢያ ከሂጃዝ ጀምሮ በደቡብ ምስራቅ እስከ ሳባ፣ ሰሃርት፣ ሂሚያር፣ ሀበሻ፣ የመን ጠረፍ ወሰኖችን የሚሸፍን አንድ እስትራቴጂያዊ ክልል ነበር።[117]

115 R. B. Sergeant, "South Arabia and Ethiopia: African Elements in the South Arabian Population", Proceedings of the 3rd International Conference of Ethiopian Studies, 3 Vols. (Addis Ababa: HSIU, 1966), I, pp. 25-26.

116 J. T. Bent, The Sacred City of The Ethiopians (London) 1896),pp. 240, 246-47.

117 Salibi, The Bible Came from Arabia, pp. 38-39, 76-78; Norris, "The Himayaritic Tihama", p. 116; Kobishchanov, Axum, Map 1, pp. X, 50, 54; Serjeant, "South Arabia and Ethiopia", pp. 25-28.

በዘመነ ክርስትና ለመጀመሪያ ሰባት ምዕተ ዓመታት ማለትም በግምት እስከ 700 ድረስ ይህ የአረቢያው የቲሃማት ጠረፍ አውራጃ በዘመኑ የሦስቱ አኅጉራት የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ የቀይ ባሕርና የላይኛው አባይ ሸለቆ ዓለማቀፋዊ የበላይ ሥርዓት ለነበረው የኢትዮጵያ ያጼ መንግሥት አንድ ዋና የግዛት፣ የገቢያና የተፅእኖ ክልል ነበር።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ በ570ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ኢትዮጵያውያን በፋርሳውያን ጦር ከየመን ደቡብ አረቢያ ግዛታቸው ከተባረሩ በኋላ እስከ ነቢዩ ሙሐመድ መነሳት ድረስ ለአራት አሥርታት በሰሜን ምዕራብ አረቢያ የቲሃማት ጠረፍ አውራጃና በመሀል አገር የመካ የንግድና የሃይማኖት ከተማ በመላው ምድረ አረቢያ ለኢትዮጵያዊ ህበሾች ዋና የሰፈራና የንግድ ማዕከላት ሆኑ።[118]

በተጠቀሰው የሽግግር ዘመን መጨረሻ ላይ በነቢዩ ሙሐመድ ሃይማኖታዊ ትምህርትና አመፅ በቁረይሽ አረብ ጎሳዎች መካከል በተከሰተው የእርስ በርስ ጦርነት በሂጃዝ አረቢያ በልዩ ልዩ መንገዶችና ምክንያቶች ሰፍረው የሚኖሩ የኢትዮጵያ የተለያዩ ማኀበራዊ ክፍሎችና ኃይሎች ማለትም ወታደሮች፣ ነጋዴዎች፣ የዕደጥበብ ባለሙያዎች፣ ባሮችና አስተማሪዎች በየፊናቸው በሁለቱ ተፋላሚ የአዋማውያንና የሙስሊም ግምባሮች ተሰልፈው እንደተዋጉ ታውቋል።

ከዚህ አኳያ በሙስሊሞች ግምባር ተሰልፈው የተዋጉት ኢትዮጵያውያን በአንፃራዊ አነጋገር በአመዛኙ ጥቂት ግለሰብ ባሮችና ባለሙያዎች ነበሩ። በሌላ በኩል በሂጃዝ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ የሀበሻ ማኀበረሰብ በጥቅል መልኩ በራሱ ወታደራዊ አመራር፣ ትጥቅና ስንቅ የተሰለፈው በነቢዩ ወገን ሳይሆን በቁረይሽ አዋማዊ መንግሥት ግምባር ነበር። የዚህ የአዋማውያንና የሙስሊም ቁረይሾ ችን ጦርነት ታሪካዊ መነሻና ውጤት በሚመለከት፣ በ622 ነቢዩ ሙሐመድ በስደት የመዲና ማዕከሉን ከመሠረተ በኋላ በመካና በሶሪያ መካከል በሲራራ ንግድ መንገድ በሚንቀሳቀሱ የመካ ቁረይሽ ነጋዴዎችና በነቢዩ ተከታይ ሙስሊሞች መካከል ጦርነት ተፈጠረ።[119]

በመሆኑም በመጋቢት 624 በድር በተሰኘው ሥፍራ በነቢዩ ሙሐመድ 324 የሙስሊም ተከታዮችና በቁረይሽ መንግሥት መሪ አቡ ጃህል በተመሩ 950 አዋማዊ የመካ መንግሥት ተዋጊዎች መካከል በተካሄደው ጦርነት አዋማውያኑ ከአዝማች መሪያቸው ጋር በሙስሊ

[118] Ibid., "South Arabia and Ethiopia", p. 26, Cited from Ibn Duraid, Al-Ishtiqaq, (Cairo, 1958), p. 193.
[119] Watt, Muhammad at Medina, pp. 2-3.





ሞቹ እጅ ተደመሰሱ።[120] በዚህ በበድር ጦርነት ታላቅ ሽንፈትና ውድቀት የደረሰባቸው የመካ ቁረይሽ አዋማዊ ባለሥልጣኖችና ነጋዴዎች በሟቹ አቡ ጃህል ምትክ በተመረጠው መሪያቸው በአቡ ሱፍያን አመራር በመዲና ሙስሊሞች ላይ ከመካና ከቲሃማት የኪናና አረብ ነገድንና ኢትዮጵያዊ የሀበሻ ማኀበረሰብን ጨምሮ ብዙ የአኅጉራት ሕዝቦችን ወታደራዊ እርዳታ መጠየቅ ግዴታ ሆነባቸው።[121]

በዚሁ የፖሊሲና የተግባር እርምጃ መሠረት የመካ ቁረይሽ አናሳ መንግሥት መሪና አዝማች አቡ ሱፍያን ከመካ ማዕከሉ በመጋቢት 625 እና በመጋቢት 627 ከሰፋሪ የሀበሻ ማኀበረሰብ፣ ከአረቡ የኪናና ነገድና ከቲሃማት አውራጃ ነዋሪዎች የተውጣጡ ብዙ ሺህ ወታደሮችን አስከትሎ በመዲና ከተማ ሙስሊሞች ላይ በቅደም ተከተል <u>ኡሑድና</u> <u>ኸንደቅ</u> በተሰኙ ሁለት የጦር ሜዳዎች ያልተሳኩ ተከታታይ ዘመቻዎችን አካሂዶ በሽንፈት ወደ መጣበት ተመለሰ።[122] ኸንደቅ በሁለቱ የቁረይሽ ተፋላሚ ኃይሎች መካከል በመዲና የተካሄደው የምሽግ ጦርነት ሥፍራ ስም ነው።

እንግሊዛዊው ምንትጎመሪ ዋት የመረጃ ምንጭ ጠቅሶ እንደ ዘገበው፣ በጦርነቱ በአዋማዊ ቁረይሾች ግምባር የዘመቱ የሀበሻ ወታደሮችን ቁጥር በሚመለከት፣ በኡሁዱ ጦርነት 3,000፣[123] በኸንደቁ ጦርነት ደግሞ 10,000[124] ነበር። እንዲሁም በመጨረሻ፣ በጥር 630 የመካ ከተማና መንግሥት በነቢዩ ሙሐመድ እጅ አለውጊያ በወደቀ ጊዜ ነቢዩን በትጥቅ ከተቃወሙ ጥቂት ሰዎች መካከል ኢትዮጵያዊ ህበሾች አብረው እንደነበሩ ተመልክቷል።[125]

የእነዚህ አልህበሽ/ሁበሻት ተብለው በ624-630 የቁረይሽ አረብ ጎሳዎች የእርስ በርስ ጦርነት በአዋማዊ አንጃው ግምባር የተሰለፉ ኢትዮጵያውያንን ማንነትና ተግባር በሚመለከት ብዙ የዘመናችን አውሮፓውያን የታሪክ ጸሐፊዎች የተለያዩ አስተያየቶችን ሰንዝረዋል። ለምሳሌ ኤች ላሚንስ የተሰኘ አንድ ጸሐፊ «አህበሾችና የመካ ወታደራዊ ድርጅት በሂጅራ ዘመን» በሚል ርዕስ በ1916 ባዘጋጀው ጽሑፍ የመካ አዋማዊ ቁረይሾችን ወደ ሽንፈትና ውድቀት ያደረሱት አህበሾች የተባሉ ኢትዮጵያዊ ባሪያ ወታደሮች ናቸው በማለት

[120] Ibid., pp. 10-13.
[121] Ibid., p. 20; Ibid., Muhammad at Mecca, pp. 154-155.
[122] Ibid., Muhammad at Medina, pp. 21, 35.
[123] Ibid., Muhammad at Mecca, p.155, Passage F.
[124] Ibid., Passage F.
[125] Ibid., Passage F.

ተችቷል።[126]

ነገር ግን የእንግሊዙ ታሪክ ጸሐፊ ዋት በበኩሉ አህበሾች የተባሉና በአዋማዊ ቁረይሾች ግምባር የተዋጉ ምንደኛ ወታደሮች ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ «አህበሽ»[127] እና «አልሁብሽ»[128] (Ahbash and Al-Hubshi) በተሰኙ ቦታዎች የተቋቋመ አንድ «ልዩ» የአረብ ማኅበረሰብ ወይም የድርጅት ምንደኛ ወታደሮች ናቸው በማለት በብርቱ ተከራክሯል።[129]

ይሁን እንጂ ከታሪክ መረጃና ትምህርት አኳያ፥ ሁለቱም ጸሐፊዎች _ላሜንስና ዋት_ ረጅም የኢትዮ-አረብ ታሪካዊ ግንኙነት በሚመለከት ኢታሪካዊ ግድፈት ፈፅመዋል። ምክንያቱም በአጎራባቹ የአረቢያ ምድር በአረቦቹ አል-አህበሽ፥ አል-ህበሽ፥ ህበሻት፥ ሁብሻት ተብለው በተለያዩ የነጠላና የብዙ ስሞች የሚታወቁ ኢትዮጵያውያን ሰፋሪዎች በነቢዩ ሙሐመድ ዘመን ሆነ ከዚያም በፊት ወይም በኋላ ባሮችም አረቦችም አልነበሩም። ይህ ግን በተጠቀሰው ጊዜ ሆነ በሌላ ክፍለ ዘመን በአረብ ምድርና ታሪክ እንደነቢዩ ሙሐመድ አሳዳጊ ሞግዚት በረካ ኡም አይማን፥ የነቢዩ ሙሐመድ የትግል አጋርና የሃይማኖት ወዳጅ ቢላል ሪባሕ ሙዓዚንና ሌሎችም ብዙ ግለሰብ ኢትዮጵያዊ ባሮች አልነበሩም ማለት አይደለም።

ታሪክ ጸሐፊው ላሜንስ ከቁረይሹ አዋማውያን ጋር በጦር ሜዳ የተሰለፉ ሀበሾችን ኢትዮጵያዊ ባሮች ናቸው በማለቱ የእንግሊዙ አቻው ዋት በብርቱ ነቅፎታል።[130] ይሁን እንጂ ጸሐፊው ዋት ራሱ በሌላ በኩል የተጠቀሱ ሀበሾች ኢትዮጵያውያን ሳይሆኑ አህበሽና ሁብሽ በተሰኙ የወንዝና የተራራ ስሞች የተሰየሙ ያንድ ልዩ የአረብ ማኅበረሰብ ወይም ማኅበር ምንደኛ ወታደሮች ናቸው የሚለውን የግል ግምትና እምነት ለማሳመን «ሁብሻት/ሀበሻት»[131] (Hubashat/ Habashat) ማለትም በአረብኛ ቋንቋ «አህበሾች/ሀበሾች» የተሰኙ የሕዝብ ስሞችን በታሪክ ሳይሆን በሰዋስዋዊ የቃላት ትርጉም የሥፍራ ስያሜዎች[132] አድርጎ አቅርቦአቸዋል።

126 Ibid., p. 154, Cited from H. Lemmens, "The Ahabish et l'Organisation Militire de la Mecque, au Siche de 'hejire", Journal Asiatique, Vol. 8, (1916), 425-82.

127 Watt, Muhammad at Mecca, p. 154, Passage B.

128 Ibid., p. 156, Passage L.

129 Ibid., pp. 11, 156.

130 Ibid., pp. 154, 157

131 Serjeant, "South Arabia and Ethiopia", p. 26.

132 Watt, Muhammad at Mecca, pp. 154, 156.





ባጭርና በጥቅል አነጋገር በአጎራባቹ አረቢያ በአረቦቹ አል-አህበሽ፥ አል-ህበሽ፥ ህበሻት፥ ሁብሻት ተብለው በልዩ ልዩ የነጠላና የብዙ ስሞች የሚታወቁ ኢትዮጵያውያን ሰፋሪዎች ለረጅም ዘመን በሁለቱ የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦች መካከል በቋንቋ፥ በሃይማኖት፥ በባህልና በዘር ዘላቂ የመገናኛ መንገድና ድልድይ መሥራች ሕዝቦች ናቸው። በመልካም ሥነምግባር፥ በአካል፥ በመንፈስና በጠባይ ጥንካሬ፥ በትዳር ፍቅርና ፅናት፥ በወታደራዊ ጥበብ ችሎታና ወኔ፥ በአእምሮ ንቃትና በግንዛቤ ጥራት፥ በአስተዳደርና በአመራር ብቃት፥ በጠንካራ እምነትና ታማኝነት በአረቡ ኅብረተሰብና መንግሥታት ዘንድ የታወቁና የተወደዱ ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ብዙ ታዋቂ የአረብ ሙስሊም ታሪክ ምሁራንና ጸሐፊዎች በየዘመኑ መስክሮላቸዋል።[133] በመሆኑም የሀበሻን ማንነትና ታሪክ ለማወቅና ለማሳወቅ እነዎትን መሰል የሰዋሰውና የጂአግራፊያ አስተማሪዎች የሚሰጡት ትምህርታዊ ግምዛቤ የለም። ምክንያቱም የሁበሾቹ መነሻና ማንነት ከተግባራቸው ጋር በጊዜና በታሪክ የታወቀ ነውና።

በአረቡ ዓለምና ታሪክ ከቅድመ እስልምና ጀምሮ ይህ ዓይነቱ ሕዝባዊና ማኅበራዊ አመለካከትና እምነት ኢትዮጵያዊ ሴቶችን፥ ባሮችንና ወታደሮችን በተለይ በጣም ተፈላጊና ተወዳጅ ማኅበራዊ አካላትና ኃይሎች እንዳደረጋቸው የራሳቸው የአረቦች የታሪክና የትውፊት መረጃዎች ያስተምራሉ።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ለምሳሌ ከነቢዩ ሙሐመድ የቁረይሽ ከፍተኛ የመንግሥትና የጦር መሪዎች መካከል ዳግማዊ ካሊፋ ዑመር[134] (634-644) እና በ641 ግብፅን በጦር ኃይል ያስገበረው አምሩ አልአስ[135] በአንድ ወገን ኢትዮጵያዊ ተወላጆች እንደነበሩ ታውቋል። ከሁለቱ ኢትዮ-አረብ ሙስሊም መሪዎች በሴት አያቱ ወገን ኢትዮጵያዊ የነበረው ካሊፋ ዑመር በአዲሱ እስላማዊ ሕግ መሠረት በመዲና የሚኖሩ ክርስቲያን ኢትዮጵያውያንን ከባድ የሃይማኖት ግብር ማስከፈሉን በተቃወመና አቡ ሉሉ በተባለ በአንድ ኢትዮጵያዊ ህብታም የዕደጥበብ ባለሙያ እጅ በ644 በጎራዴ ስለት እንደተገደለ የአረቡ ታዋቂ የታሪክ ጸሐፊ አጢታባሪ አስታውቋል።[136]

133 Erlich, Ethiopia and the Middle East, p. 5; Couq, Islam En Ethiopie, p. 27; Ibn Fadl Umari, Masalik El Absar, pp. 19-21, 30-31.

134 Ibid., Ethiopia and the Middle East, p. 5

135 Ibid., p. 7.

136 Sergew H. Sellassie, History, p. 192.

## ሀበሻ መንግሥት መነሻና ውድቀት በየመን አረቢያ (1021-1159)

በሂጃዝ አረቢያ የሀበሾችን ፍጻሜ በሚመለከት፣ የ632-661 የአራቱ የመዲና ካሊፋዎች አቡበከር፣ ዑመር፣ ዑስማንና ዓሊ የእስልምና ዘመንና ግዛት በ661 ባላንጣቸው ካሊፋ ሞአዊያ (661-680) በደማስቆ ሶሪያ የኡማያድን መሳፍንታዊ ዘመንና ግዛት (661-750) በመሠረተ ጊዜ በመካ፣ በአክሱምና በመዲና በቁረይሽ አረብ ሙስሊሞችና በኢትዮጵያውያን ደጋፊዎቻቸው መካከል ከ610 ጀምሮ ለግማሽ ምዕተ ዓመት የነበረው ታሪካዊ የቀረበ ግንኙነት ወደ መጨረሻው ደረሰ ለማለት ይቻላል።

በተጠቀሰው ረጅም የእስልምና ሃይማኖት ምሥረታና ግምባታ ዘመን (610-750) በቀይ ባሕር የሁለቱን ማለትም የኢትዮጵያ ጥንታዊ የክርስቲያንና የአዲሱ የአረብ እስላማዊ መንግሥታትን ብሔራዊ ጥቅምና የኃይል ሚዛን በሚመለከት፣ የዳህላክ ደሴትንና የአዱሊስ ወደብን ጨምሮ የባሕሩ ንግድ፣ ወደቦችና ደሴቶች በሙሉ በኢትዮጵያውያኑ ባሕር ኃይል[137] ቁጥጥር ሥር ነበሩ። በአንፃሩ ግን በኢትዮጵያውያኑ ባሕር ኃይል[137] ቁጥጥር ሥር ነበሩ። በአንፃሩ ግን በግመልና በፈረስ ጦር በምድረ በዳ የፋርሳውያንንና የሮማውያንን ያጼ መንግሥታት የማስገበር ትግል ያካሄዱ የነበሩ አረቦች ከኢትዮጵያኑ ጋር የሚወዳደራቸው የንግድም ሆነ የጦር መርከብ መሣሪያና ድርጅት ገና አልነበራቸውም።[138] የሀብትም ሆነ የሰው ኃይል ሚዛንም ቢሆን በኢትዮጵያውያኑ በኩል ነበር።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል በ610ዎቹ በሂጃዝ አረቢያ በቁረይሽ አረቦች መካከል በተካሄደው የእርስ በርስ ጦርነት ኢትዮጵያውያን ጣልቃ በመግባት ከውስጥም ከውጭም በአካባቢው የአገራቸውን የዝቢያ ሆነ የፖለቲካ ጥቅም ለማግኘትና ለማስፋፋት በ616 በቁረይሾቹ መንግሥት በኩል በይፋ የቀረበውን የኅብረት ጥሪ ውድቅ እንዳደረጉ ይታውሳል። ነገር ግን የቁረይሽ ሙስሊም አረቦች አገራቸውን ከተቆጣጠሩ በኋላ በ630፣ በ640፣ በ702 ኢትዮጵያውያን ከቀይ ባሕሩ የአዱሊስ ወደብና የዳህላክ ደሴት በቁረይሾቹ የሹዐይባና የጅዳ ወደቦች ላይ ያልተሳኩ ተከታታይ የባሕር ወረራዎችን እንዳካሄዱ ታውቋል።[139]

በመሆኑም በ703 ከደማስቆ ሶሪያ ማዕከላቸው የአረቡ የኡማያድ ባለሥልጣኖች በአፀፋ እርምጃ የዳህላክ ደሴትን በሰፋሪ ጦር በመያዝ

137 Erlich, Ethiopia and the Middle East, p. 11.

138 Tedeschi, "Note Storiche sulle Isole Dahlak", p. 52.

139 Erlich, Ethiopia and the Middle East, pp. 9-11; Couq, Islam En Ethiopie, pp. 35-36.





የፖለቲካ እስረኞቻቸው ግዞት አደረጉት።[140] በተጨማሪም የአረብ ሙስሊም ኃይሎች ከዳህላክ ደሴት በትክክል ባልታወቀ ወቅትና ሁኔታ የኢትዮጵያን የአዱሊስ ወደብ አጠፉት።

ይሁን እንጂ ይህ ሁሉ የቀይ ባሕር ጂኦፖለቲካ ለውጥ በጥንታዊ የኢትዮጵያና የአረብ ሕዝቦች መካከል በቆየው ታሪካዊ መስተጋብርና መወራረስ ሂደት ላይ ከአካባቢ፣ ከማዕከልና ከአሠራር ለውጥ ባሻገር አዲስ መሠረታዊ ለውጥ አላስከተለም። በዚህ ረገድና ተግባር፣ በአረቢያ የኢትዮጵያ ሀበሾች መሠረትና ማዕከል አሁን በሰሜን ምዕራብ ከሂጃዝ፣ መካና ቲሃማት በደቡብ ጠረፍ በጥንት ዘመን ከ577 በፊት እንደነበር በየመኑ ቲሃማት ሆነ። በመሆኑም አሁን በኢትዮጵያና በየመን አረቢያ መካከል የዳህላክ ደሴትና የዜይላ ወደብ አዲስ የንግድና የባህል ልውውጥ መንገዶችና በሮች ሆኑ።

እንደዚህ የኢትዮ-አረብ የንግድና የባህል ልውውጥ ማዕከልና መንገድ የሆነው የዳህላክ ደሴት ከአጎራባቹ የምፅዋ ወደብ ጋር ከ703 እስከ 1159 ድረስ ለ460 ዓመታት ከደማስቆ ሶሪያና ከባግዳድ ኢራቅ በቅደም ተከተል በአረቡ የኡማያድና የአባሲድ (750-1517) ተፃራሪ ባለሥልጣኖች፣ በግብፅ መንግሥታት፣ ከሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በቤጃ መሳፍንታዊ ኃይሎችና በኢትዮጵያ ነገሥታት እንዲሁም በ1021-1159 የመንን ለ138 ዓመታት በገዙ ኢትዮጵያዊ የሀበሻ ባኒናጃህ ባለሥልጣኖች መካከል ታላቅ የጂኦ-ፖለቲካ ትግል ደሴት እንደሆነ የታሪክ መረጃ ጥናት ያሳያል።[141]

ከዚህ አኳያ ከ703 እስከ 809 ድረስ[142] ለአንድ ምዕተ ዓመት የዳህላክ ደሴት ከሶሪያና ከኢራቅ ማዕከላት ለኡማያድና ለአባሲድ አረብ ባለሥልጣኖች፣ ከላይ እንደተጠቀሰው፣ የፖለቲካ እሥረኞች ግዞት ሆነ። ቀጥሎም በ831 በቤጃው የናቅስ አካባቢ መንግሥትና በግብፁ የአረብ መንግሥት መካከል በተፈጸመው የንግድና የወዳጅነት ውል የዳህላክ ደሴት ከምፅዋ ወደብ ጋር የናቅስ ቤጃ መንግሥት ግዛት መሆኑ ዕውቅና አገኘ።[143] በ872[144] ደግሞ የዳህላክ ደሴት የኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት እንደነበር የአረቡ ታሪክ ጸሐፊ የዕቁቢ መዝግቧል። በዘመኑ የዳህላክና ፎምፅዋ እስላማዊ ገዥ ራሱን ሱልጣን

140 Tedeschi, "Note Storiche sulle Isole Dahlak", pp. 52-53.

141 Ibid., pp. 52-57.

142 Ibid., pp. 52-53.

143 Ibid., p. 53.

144 Ibid., p. 54., Cuoq, Islam En Ethiopie, p. 42.

ወይም ንጉሥ ብሎ ሲጠራ ኢትዮጵያውያኑ ግን «ሥዩመ ባሕር»[145] በሚል የገባር ስም ይጠሩት ነበር።

በ935 ደግሞ አንድ ሌላ የአረብ ታሪክ ጸሐፊ መስዑዲ ዳህላክና ምፅዋ ከዜይላ ጋር የኢትዮጵያ መንግሥት[146] ግዛቶች እንደነበሩ አስታውቋል። በተጨማሪም በዘመኑ በኢትዮጵያና በየመን አጎራባች መንግሥታት መካከል ጥሩ የወዳጅነትና የንግድ ስምምነት እንደነበር መስዑዲ ጨምሮ መዝግቧል። በ977[147] አሁንም አንድ ሌላ የአረብ ታሪክ ጸሐፊ ኢብን ሃውቀል የዳህላኩ ሥዩመ ባሕር ለየመኑ መንግሥት ገባር እንደነበር ጽፏል። በሌላ ቃል በ10ኛው ምዕተ ዓመት የዳህላኩ ሥዩመ ባሕር የኢትዮጵያም የየመንም ጥምር ገባር ነበር ማለት ነው።

በተጠቀሰው ዘመን የዳህላክ ደሴት ዋናው የኢኮኖሚ መሠረት የባሪያ ንግድ ነበር። የባሮቹ ሁለት አጎራባች ምንጮች ደግሞ በአፍሪካ ኢትዮጵያና ኑቢያ ነበሩ። በወቅቱ የዳህላኩ ሥዩመ ባሕር ለየመኑ መንግሥት ግብር የሚከፍለውም በባሪያ ነበር። በዚህ ረገድና ተግባር፣ ለምሳሌ አገሩን ለ80 ዓመታት ገዝቶ በ981 የሞተው የየመኑ ሱልጣን አቡጋይሽ ሚስቱን በደሴቱ ወኪል አድርጓት በማስቀመጥ ከዳህላኩ ሥዩመ ባሕር በዓመት በአንድ ሺህ የሚቆጠሩ የኢትዮጵያና የኑቢያ ባሮችን በግብር ስም ያገኝ እንደነበር አሁንም አንድ ሌላ የዘመኑ የአረብ ታሪክ ጸሐፊ እማሪህ[148] ጽፏል።

ከዚህ አኳያና ወቅት በ11ኛውና በ12ኛው ምዕተ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ባሮች በቀይ ባሕር አካባቢ አንድ ዋና የፖለቲካ ኃይል እንደነበሩ የዘመኑ ታሪክ ያስተምራል። ለምሳሌም ከ1021 እስከ 1159 ድረስ በየመንና በዳህላክ ደሴት አዲሱ ኢትዮጵያዊ የሀበሻ በኒ ነጃህ ሥርወ መንግሥትና ባለሥልጣኖች በየመኑ ቲሃማት የአረቡን ጥንታዊ የበኒ ዝያድ ሥርወ መንግሥት ደምስሰው ራሳቸውን የአገሩ መሪዎችና የገዥ መደብ አደረጉ።[149] በወቅቱ በየመኑ ቲሃማት ጃዛሊና ስሀርት የተሰኙ ሁለት ኢትዮጵያዊ የሀበሻ ነገዶች እንደነበሩና የተጠቀሰው የሀበሻ በኒ ነጃህ ሥርወ መንግሥትና የገዥው መደብ ከሁለቱም ማኅበረሰቦች እንደወጡ ታውቋል።[150]

145 Tadeschi, "Note Storiche Sulle Isole Dahlak" p. 58.
146 Ibid., p. 54; Cuoq, Islam En Ethiopie, pp. 44-45.
147 Ibid., "Dahlak" p. 55; Couq, Islam En Ethiopie, p. 46.
148 Ibid., "Dahlak", p. 55.
149 Ibid., pp. 55-57; Cuoq, Islam en Ethiopie, pp. 47-49.
150 Surjeant, "South Arabia and Ethiopia", p, 25.





የሀበሻ በኒ ነጃህ ሥርወ መንግሥትና የገዥው መደብ ከስተትና ተግባር በሚመለከት፣ በ981 የየመኑ ሱል[illegible] አቡጋይሽ ሲሞት በአገሩ ረጅም የሥልጣን ችግር ተፈጠረ።[151] በዚህ ወቅት ናጃህና ነፍስ የተባሉ ሁለት ኢትዮጵያዊ የቀድሞ ባሮችና አሁን ከፍተኛ የየመን ቤተ መንግሥት ባለሥልጣኖች ከነተከታዮቻቸው ጋር በ5,000 እና በ20,000[152] የሚቆጠሩ ኢትዮጵያዊ ወታደሮችና የጦር አበጋዞች አደራጅተውና እንዲሁም በዘርና በፖለቲካ ከዳህላክና ከኢትዮጵያ መንግሥታት ባለሥልጣኖች ጋር ጠንካራ ግንኙነት ፈጥረው ከ1021 እስከ 1159 ድረስ የመንን በሀበሻ መንግሥት ሕግና ጦር ሥር ለ138 ዓመታት በበላይነት አስተዳድረዋል።[153]

በመጨረሻ በ1159 ኢትዮጵያዊ የሀበሻ ባኒናጃህ ሥርወ መንግሥት መሪዎች፣ ባለሥልጣኖችና ወታደሮች፣ ከ582 ዓመታት በፊት በ577 ቅድመ አያቶቻቸው ከየመን በፋርሳውያን እንደተባረሩ ሁሉ፣ አሁን እነሱም በየመን አረብ አመፅ ተሸንፈው ወደ እናት አገራቸው ተመለሱ። ይህ ሁሉ ከሆነ በኋላ በ1173 ሁለቱም የመንና የዳህላክ ደሴት በግብፁ ባለሥልጣናት ተፅዕኖ ሥር ወደቁ። በዚህ ረገድና ወቅት፣ ግብፅ ከ1171 እስከ 1250 ድረስ አዩቢ ተብሎ በሚታወቀው የሰለሃዲን ሥርወ መንግሥት ሥር እንደነበር ይታወሳል።

## በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ የሙስሊሙ ዓለም ሚና

የአረቦችን እስላማዊ አመፅ ታሪካዊ መነሻና እንቅስቃሴ በሚመለከት፣ ነቢዩ ሙሐመድ ሃይማኖቱን ማስተማር በጀመረ ጊዜ በመካ ከተማ በንግድ ኢኮኖሚ የሚተዳደር የቁረይሽ ነገድ፣ በየትሪብ ማለትም በመዲና የገበሬ መንደር በእርሻ ሥራ የሚተዳደር የቃላይ ነገድና ከሁለቱም ከመካና ከመዲና በምዕራብ፣ በምስራቅ፣ በሰሜንና በደቡብ አረቢያ ምድረ በዳ በእንስሳት እርባታ በዘላንነት የሚኖሩ ብዙ የአረብ ነገዶች አንድ ማዕከላዊ የጋራ መንግሥት፣ ሕግና ሥርዓት ሳይኖራቸው በተለያዩ ማኅበራዊ የሥራና የዕድገት መስኮችና ደረጃዎች ተሰማርተው የሚገኙ አዋማዊ ማኅበረሰቦች ነበሩ።

በመጨረሻ በሰኔ 632 በ62 ዕድሜ ከመሞቱ በፊት ከ622 እስከ 630 ድረስ ነቢዩ ሙሐመድ ቁላይ በቀረበው ብርቱ ሥርዓታዊ ትግልና ድል በመካና በመዲና የእስላም ሃይማኖትና መንግሥት መሠረተ። ከ630 እስከ 632 ድረስ በሁለት ዓመታት ውስጥ ከመካና

151 Tedeschi, "Dahlak", 56.
152 Cuoq, Islam En Ethiopie, p. 48.
153 Trimingham, Islam In Ethiopia, p. 76.

ከመዲና ውጭ የተጠቀሱ የአረብ ዘላን ነገዶችና ጎሳዎች አንድ በአንድ በተወካዮቻቸው አማካይነት በመዲና ከተማ ለድል አድራጊው ነቢዩ ሙሐመድ ታማኝነታቸውን አረጋገጡ።[154]

ይሁን እንጂ በ632 የነቢዩ ሞት እንደታወቀ የተጠቀሱ የአረብ ነገዶች በየአካባቢያቸው በአዲሱ የሙስሊም መንግሥት ላይ አመፁ። ስለሆነም የነቢዩ አንጋፋው ተከታይና የመጀመሪያ አልጋወራሽ ካሊፋ አቡበክር (632-634) የዘላን ነገዶችን አመፅ በፈጣን ወታደራዊ እርምጃዎች በመቆጣጠር የነቢዩን የእስላም ሃይማኖትና መንግሥት ከመጥፋት አደጋ አዳነ።

ቀጥሎም ዳግማዊ ዑመር (634-644) በአንድ አሥርት ውስጥ ከመዲና ማዕከል በተባበረ የአረብ እስላማዊ ሃይማኖት፥ መንግሥትና ጦር በመካከለኛው ምስራቅና በግብፅ ጥንታዊ የፋርሳውያንና የሮማውያንን የአጼ መንግሥታት ደምስሶ በምትካቸው ዓለማቀፋዊ የእስላም መንግሥትና ሃይማኖት ግምቢታ አጠናከረ። በ644-661 ተከታይ ካሊፋዎች ዑስማንና ዓሊ የነቢዩን፥ የአቡበክርንና የዑመርን እስላማዊ የዓለም ሥርዓት ግምቢታ ፖሊሲና ተግባር የበለጠ ተግባራዊ አደረጉ።

ከእነዚህ አምስቱ ታላላቅ የእስላም ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ መሥራች መሪዎችና አዝማቾች ጎንና ግምባር አያሌ ኢትዮጵያውያን በተግባራዊ ትብብር አብረው እንደነበሩ ከላይ የቀረቡ የታሪክ መረጃዎችና ጥናቶች በሥፍራ፥ በጊዜና በቁጥር ዘርዝረው ያሳያሉ።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል፥ ከታሪክ አኳያ እንደዚህ በኢትዮጵያ መንግሥትና ሕዝብ ተግባራዊ ድጋፍ የዓለም ሃይማኖት፥ መንግሥትና ሥልጣኔ ሆኖ የተነሳው እስልምና በኢትዮጵያ ሥልጣኔና ታሪክ ላይ በዲያሌክቲካዊ መንገዶች ሁለቱንም አሉታዊና አዎንታዊ ማለትም የተፅዕኖና የአስተዋፅኦ ሁኔታዎችንና ሂደቶችን አስከትሏል። ከአሉታዊ የተፅዕኖ ሚና አኳያ፥ ከካሊፋ ዑመር ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በአካባቢው ዓለማቀፋዊ መንግሥት ሆኖ የተከሰተው የአረቦች እስላማዊ ኃይልና እንቅስቃሴ ከአረቢያና ከግብፅ እስትራቴጂያዊ ሥፍራዎች የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ የንግድ በሮችንና እንቅስቃሴዎችን የአዱሊስን ወደብ ጨምሮ ከመካ፣ያና ከመውጫ ኬላዎች በመቆጣጠር በ577 የፋርሳውያን ጦር ሰፋሪ ኢትዮጵያውያንን ከየመን አረቢያ ባባረራቸው ጊዜ የጀመረውን ኢትዮጵያውያንን ከውጭ ዓለም የመገለል ሁኔታና ሂደት የበለጠ አጠናከረ።

---

[154] Watt, Muhammad at Medina, Chap. 4.





ከአዎንታዊ የአስተዋፅኦ ሚና አኳያ ደግሞ በአካባቢው የአረቦች እስላማዊና ዓለማቀፋዊ ኃይል ራሱ በተለያዩ መንገዶችና መሣሪያዎች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለታላቁ የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች ህብረተሰብና መንግሥት ዕድገት የራሱን ጉልህ አስተዋፅኦ እንዳደረገ የታሪክ መረጃና ትምህርት በግልፅ ያስተምራል።

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ከካሊፋ ዑመር ዘመነ መንግሥት ጀምሮ በደቡብ ኢትዮጵያ በተለይም በሐርላና ህዲያ ጥንታዊ፥ አጎራባችና ተዛማጅ ሕዝቦች ምድር ላይ ከሂጃዝ አረቢያ ቀይ ባሕርን ተሻግረው የገቡ የቁረይሽ አረብ ሙስሊም አስተማሪዎችና ነጋዴዎች የኢትዮጵያን ተከታታይ የማኽዙማይት (896-1285) እና የሃሽማይት-ዋላስማ (1285-1577) ሥርወ መንግሥታትና አያሌ ተዛማጅ የሙስሊም ሱልጣኔቶች ማለትም መንግሥታት መሠረቱ።[155] የሸዋ፥ የህዲያና የይፋት ሱልጣኔቶችን ጨምሮ እነዚህ የኢትዮጵያ እስላማዊ መንግሥታትና ማኅበረሰቦች በተጠቀሰው ጥንታዊ ክፍለ ዘመን በሃይምኖት፥ በንግድ፥ በቋንቋና በባህል በአካባቢው ከአረቡ የሙስሊም ዓለም ጋር የቀረበና የጠበቀ ግንኙነት እንደነበራቸው በዚህ ጥናት ከዚህ በታች አግባብ ባለው ሥፍራና ጊዜ በዝርዝር ይታያል።[156]

በተጨማሪም በ330 የክርስትና ሃይማኖት ወደ ኢትዮጵያ ከገባበት ዘመን ጀምሮ በግብፅና በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያኖች መካከል የተፈጠረው ግንኙነት በ642 ግብፅ በአረብ ሙስሊሞች ከተያዘም በኋላ ለዘለቄታው በመቀጠል በተጠቀሰው የኢትዮጵያ ረጅም የገለልተኝነት ዘመን አገሪቱን በመጠኑም ቢሆን ከውጭው ዓለም ጋር የሚያገናኝ አንድ ሌላ መንገድ ሆነ።


በመጨረሻም በኢትዮጵያ ታሪክ ከአገር ውስጥ የሰነድ መረጃ ባልተገኘበት የ550-1300 'ጨለማ' ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያን የሙስሊም ሃይማኖት ታሪክ ጨምሮ በመጠኑም ቢሆን የዘመኑን ታሪክ ከውጭ በኩል በልዩ ልዩ ወቅቶች፥ ምክንያቶችና መንገዶች መዝግበው ለትውልድ በዓይነት ያቆዩት ብዙ የአረብ ሙስሊም ጸሐፊዎችና የታሪክ ባለሙያዎች ናቸው። ባጭሩ በተጠቀሰው ዘመን ለኢትዮጵያ በህውርታዊ ኅብረተሰብና መንግሥት ክስተትና ዕድገት እስልምና አንድ ማኅበራዊ መሠረትና መሣሪያ እንደሆነ የታሪክ መረጃና ትምህርት ያሳያል።

---

[155] Trimigham, Islam in Ethiopia, pp. 58-59.

[156] Umari, Masalik el Absar, Maqrizi, Moslem Kings in Abyssinia; Braukamper, “Islamic Principalities”.

## የኢትዮጵያ የ1520 – 1660 ታላቁ የሕዝቦች እንቅስቃሴ ካርታ



ምንጭ ላጊድ ፡ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።





# ክፍል አራት

## የእስልምና ሃይማኖትና መንግሥት መነሻና ዕድገት በኢትዮጵያ 615-1300

### *በዘመነ እስልምና የኢትዮጵያ የቀይ ባሕር በሮችና መንገዶች*

በ615-616 በነቢዩ ሙሐመድ መመሪያ መሠረት ከመካ በሁለቱ የቀይ ባሕር አጎራባች የሹአይባና የአዱሊስ ወደብ በሮች በስደት ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ የኢትዮ-አረብ የመጀመሪያ ሙስሊሞች በ631 ወደ መካ እስከተመለሱ ድረስ አብዛኞቹ በኢትዮጵያ ለአሥራ አምስት ዓመታት እንደኖሩና ከእነርሱም በሀያ የሚቆጠሩ በኢትዮጵያ ሞተው እንደተቀበሩ ታውቋል።

ዛሬ በሰሜን ኢትዮጵያ በዘልማድ «ጀበርቲ» ተብለው በወል ስያሜ የሚታወቁ የትግሬ፣ የአገውና የአማራ ሙስሊሞች በአክሱም አገርና ቤተ መንግሥት እስልምናን ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተማሩ ብሎም ቅድመ አባት አያቶቻቸውን ከዘመኑ የአክሱም ክርስቲያን ንጉሥ (ነጃሺ) አፄ አስሓማ ኢብን አብድጃር (600-630) ጋር ወደ እስልምና ሃይማኖት የመለሱ እነዚሁ ስደተኛ ሙስሊሞች ናቸው ብለው በጽኑ ያምናሉ። ያስተምራሉ። ለዚህ እምነታቸውና ትምህርታቸው በሰሜን ምስራቅ ትግራይ «ነጋሽ» በተሰኘው ቀበሌ የሚገኘውንና የአጼ አስሓማና ሌላም የዘመኑ ሙስሊሞች መካነ መቃብር ነው የሚሉትን እንደአንድ ታሪካዊ መረጃ ያቀርባሉ።[157]

በሰሜን ኢትዮጵያ ከ615-631 የመካ ስደተኛ ሙስሊሞች ትምህርትና ሥራ በኋላ ቀጣዩን የእስልምና ሃይማኖት እንቅስቃሴና ተግባር በሚመለከት ደግሞ፣ ከ981 እስከ 1154 ድረስ አሁንም በሰሜን ምስራቅ ትግራይ ከነጋሽ ቀበሌ በስተደቡብ በአምሳ ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በመቀሌ ከተማ አጠገብ በሚገኘው የኩሀ መንደር የቆሙና በአረብኛ ቋንቋ የተጻፈባቸው ብዙ የአረብ መቃብር ሐውልቶች በሀኛያው ምዕተ ዓመት በአርኪኦሎጂ ጥናት ተገኝተዋል።[158]

---

157 "Negash: The Second Mecca", Tigrai Culture, Tourism and Information Bureau (Mekelle, 1997).

158 M. Schneider, "Stelese Funeraires Arabes de Quiha", Annales D'Ethiopie, Vol. 7(1967), pp. 107-118; Trimingham, Islam In Ethiopia, p. 63, No. 2.

እንዲሁም በ15ኛው ምዕተ ዓመት በጤምድርና በደቡብ ትግራይ የተደራጁ የሙስሊም ማኅበረሰቦች እንደነበሩ በአጼ ነገሥታት ዘርዓያዕቆብና በዕደማርያም ዜና መዋዕሎች ተመልክቷል።[159] ቀጥሎም በ1520 የፖርቱጋል ልዑካን ቡድን ወደ ኢትዮጵያ በመጣ ጊዜ በደቡብ ትግራይ በአሸንጌ ሐይቅ አጠገብ ዶባ የተሰኘ አንድ ጠንካራ የሙስሊም የአካባቢ ሕዝብና አገር ነበር።[160] በመጨረሻም በ1533 ኢማም አሕመድ ግራኙ ከደቡብ ኢትዮጵያ በሰሜኑ ደጋማ አካባቢ ላይ ዘመቻ ባካሄደ ጊዜ በትግራይ በውቁሮ/ነጋሽ ቀበሌ ተከታዮቹ «አሕመድ ነጋሽ አስማሃ» መካነ መቃብርን እንደጎበኙና[161] እንዲሁም ወደ አክሱም ከተማ በደረሰ ጊዜ «በለው» የተሰኘ የሙስሊም ሕዝብ ተወካዮች መጥተው ኢማሙን በክብር እንደተቀበሉት በዜና መዋዕሉ ተጽፏል።[162] በኢማሙ የ1524-1543 የአመፅ ጦርነት ወቅትና በኋላ እስልምና በሰሜን ኢትዮጵያ በፍጥነት እንደተስፋፋ ታውቋል።

በሌላ በኩል፥ ከላይ እንደተመለከተው፥ በ550-1300 'ጨለማ' ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ የክርስቲያን ምድርና ታሪክ በድንጋይ ላይ ሆነ በብራና የተጻፈ የሰነድ መረጃ ባለመኖሩ ከኢማም አሕመድ ወታደራዊ እንቅስቃሴ በፊት በሰሜን ኢትዮጵያ በደጋው ክልል የተጠቀሱት ተከታታይ እስላማዊ ማኅበረሰቦች፥ ኃይሎችና እንቅስቃሴዎች በሹአይብ-አዱሊስ የወደብ በሮች ወደ ኢትዮጵያ ከገቡ የኢትዮ-አረብ ስደተኞች ጋር በሥፍራ፥ በጊዜና በተግባር ቀጥተኛ ግንኙነት እንደነበራቸው በትክክል የሚታወቅበት መንገድና መሣሪያ የለም። በዚህ ሁኔታ ከስደተኞቹ የአረብ ሰነዳዊ ታሪክ ጋር በቅርብ የተያያዘው ሕዝባዊ ትውፊት እንደአንድ አንፃራዊ የግንዛቤ መሠረትና መሣሪያ ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችል በዚህ ጥናት ከላይ የታሪክ መረጃ ዓይነት፥ ትርጉምና ትምህርት አስመልክቶ በቀረበው ትንታኔ ተገልጿል።

በመጨረሻም በዘመነ እስልምና የኢትዮጵያን የቀይ ባሕር በርና መንገድ በሚመለከት፥ በአንድ በኩል ከ700 ዓመተ ምህረት በኋላ ማዕከላቸውን በደማስቆ ሶሪያ ላይ ያደረጉት የአረብ ኡማያድ ባለሥልጣኖች በአረቢያ ላይ ከኢትዮጵያውያን ዘወትር ከባሕር የሚሰነዘረውን የዘረፋ ጥቃት ከምንጩ ለማቆም በቀይ ባሕር ጠረፍ ላይ የአገሪቱን ጥንታዊ የአዱሊስ ወደብ ከተማ ማጥፋትን አስቸኳይ የታክቲክም

[159] Cuoq, Islam En Ethiopie, pp. 157, 160.
[160] Trimingham, Islam In Ethiopia, p. 81.
[161] Arabfaqih, Conquete, p. 419.
[162] Ibid., pp. 420-421.





የእስትራቴጂም ፖሊሲና ተግባር አድርገው ወሰዱት።

ይሁን እንጂ በሌላ በኩል የአረብና የፋርስ ሙስሊም ሰፋሪ ነጋዴዎችና አስተማሪዎች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በቀይ ባሕር፥ በኤደን ባሕረ ሰላጤና በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻዎችና ደሴቶች ዳህላክን፥ ምፅዋን፥ ሱዋኪንን፥ ዜይላንና ሞቃዲሾን ጨምሮ ብዙ እስላማዊ የሰፈራ፥ የንግድ፥ የሃይማኖትና የባህል ማዕከላትንና በሮችን መሠረቱ።[163]

ከእነዚህ ቁልፍ የቀይ ባሕርና የሕንድ ውቅያኖስ እስላማዊ የደሴትና የጠረፍ ማዕከላት ዳህላክ፥ ምፅዋና ሱዋኪን በሰሜን ክልል ለኢትዮጵያ የክርስቲያን አገር እንዲሁም ለቤጃና ለኑቢያ አገሮች፥[164] በኤደን ባሕረሰላጤ ላይ የዜይላ ወደብ ከተማ በምስራቅና በመሀል ደቡብ ኢትዮጵያ ለጥንታዊ የሐርላና የሀዲያ ነባርና አጎራባች አገሮችና መንግሥታት እንዲሁም በሰሜን መሀል ደጋማው ክፍል ለኢትዮጵያ የክርስቲያን አገሮች፥[165] ሞቃዲሾ ደግሞ በደቡብ ምስራቅ ለአዛኒያና ለሱማሌ ሕዝቦችና አገሮች[166] አዲስ የእስላም፥ የንግድ፥ የሃይማኖትና የባህል ምንጮች፥ በሮችና መንገዶች ሆኑ።

## የኢትዮጵያ እስላማዊ ሥልጣኔ ክስተትና ዕድገት (896-1300)

### *የታሪክ መረጃ ምንጮች*

በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ እንደተመለከተው፥ በግምት ከ2800 ዓመተ ዓለም እስከ 700 ዓመተ ምህረት ማለትም እስከ ዘመነ እስልምና ድረስ በ3500 ዓመታት ውስጥ በልዩ ልዩ ክፍለ ዘመናት በጥንታዊ የግብፅ ሃይሮግላፊክስ፥ የደአማት፥ የሳባ፥ የግዕዝ፥ የግሪክ፥ የላቲንና የአረብ ቋንቋዎችና ፊደሎች በተቀረፁ የሰነድ መረጃዎች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በተለይም በረጅሙ የቀይ ባሕር፥ የኤደን ባሕረሰላጤና የሕንድ ውቅያኖስ ጠረፍና በሰሜኑ ደጋማው ክፍል የሚኖሩ ጥንታዊ የፑንት፥ የደአማት፥ የአክሱም፥ የቤጃ፥ የአገው፥ የሰሜን፥ የትሮጅሎድ፥ የበርበርና የአዛኒያ ነባር ሕዝቦችና አገሮች በሥፍራ፥ በጊዜና በስም ተጽፈው በታሪክ በልዩ ልዩ መንገዶችና ደረጃዎች ታውቀዋል።

[163] Cuoq, Islam En Ethiopie, Chap. 3; Trimingham, Islam In Ethiopia, p. 61; Doresse, Histoire Sommaire, Chap. 5
[164] Ibid., Islam En Ethiopie, pp. 42-53.
[165] Ibid., pp. 54-64.
[166] Doresse, Histoire Sommaire, pp. 116-150.

ነገር ግን እነዚህ የተጠቀሱ ጥንታዊ የግብፅ፣ የግሪክ፣ የሮም፣ የአክሱምና የአረብ ሕዝቦች፣ ነጋዴዎችና ጸሐፊዎች ከዘመነ እስል ምና በፊት ከክፍለ አህጉሩ የሰሜንና የምስራቅ ባሕር ጠረፎች እንዲሁም የዘመኑ ግሪኮ-ሮማውያን «ትሮጅሎዳውያን» እና «በርበራውያን» ብለው የሚጠሩዋቸው ብዙ ዘላንና አዳኝ የቆላ ማኅበረሰቦች በእንቅስቃሴ የሚኖሩባቸውን የቆላና የበረሀ ክልሎች ተሻግረው ደጋማና ውሃማ ለምና ሰፊ በሆነው መሀል ደቡብ ኢትዮጵያ ሰፍረው ብሎም በእርሻና በእንስሳት እርባታ ተግባራትና ባህል ተሰማርተው ከሚኖሩ የተለያዩ ሴማዊ፣ ኩሻዊና አሞአዊ የሐርላ፣ የሀዲያ፣ የጎንጋና የጋሞ-ወላይታ ሕዝቦች፣ ማኅበረሰቦችና መንግሥታት ጋር ግንኙነት አላደረጉም።

ከእነዚህ በውጭው የዓለም ክፍሎች ዘንድ እስከ ዘመነ እስልምና ድረስ በሥፍራና በጊዜ ሳይታወቁ ከኖሩ ብዙ ጥንታዊ የመሀል ደቡብ ኢትዮጵያ ሕዝቦች መካከል በግምት ከስምንተኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በዜይላ የንግድ በርና መንገድ ወደ ተጠቀሰው ለምና ሰፊ መሀል አገር በገቡ የአረብ ሙስሊም ነጋዴዎችና አስተማሪዎች አማካይነት ለመጀ መሪያ ጊዜ የእስልምና ሃይማኖት በመቀበል በክፍለ አህጉሩ ቀዳሚ የእስላም አገሮችና መንግሥታት የሆኑ ማኅበረሰቦች ከምሥራቁ ቆላማ የጠረፍ ክልሎች አንስቶ በምዕራቡ መሀል አገር እስከ ዓባይና ጊቤ ወንዞች ድረስ እንዲሁም በደቡብ ምስራቅ እስከ ዋቤና ገናሌ ወንዞች ድረስ በሚገኘው በክፍለ አህጉሩ የታላላቅ ወንዞችና ሐይቆች ምድር ላይ በሰፈራ የሚኖሩ ሴማዊና ኩሻዊ የሐርላና የሀዲያ አጎራባችና ተዛማጅ ሕዝቦችና መንግሥታት ናቸው።

በመሀል ደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ፣ የእነዚህ ሙስሊም አገሮ ችንና መንግሥታትን የታሪክ ምንጭና መነሻ በሚመለከት፣ አንደኛ፣ በ20ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ታዋቂ የኢጣሊያ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ ዶክተር ኢንሪኮ ቼሩሊ የ896-1285 የማኽዙማይትና የ1285-1577 የሃሽማይት-ዋልስማ ማለትም ተከታታይ የሸዋና የይፋት እስላማዊ ሥርወ መንግሥታትን፣ ሱልጣኔቶችንና ሱልጣኖችን ከስተት እና ዕድገት በተመለከተ በአረብኛ ቋንቋ ተጽፈው ከሐረር ጥንታዊ ከተማ የተገኙ የዜና መዋዕል ሰነዶችን መርምሮ *"The Chronological Repertory of Shoa"* እና *"The History of the Walasma"* በተሰኙ ጥናቶቹ የሱልጣኔቶቹን የሰባት ምዕተ ዓመታት (896-1577) እውነተኛ ታሪክ ለዓለምና ለትውልድ ለመጀመሪያ ጊዜ በትክክል አሳውቋል።[167]

---

[167] E. Cerulli, Ethiopia's Relations with the Muslim World, UNESCO, History of Africa, Vol. III (1988), pp. 575-585; Trimingham, Islam In Ethiopia, pp. 58-61; Cuoq, Islam En Ethiopia, pp. 120-129, 151.





ሁለተኛ፣ ከኢትዮጵያ የ550-1300 «የጨለማ» ክፍለ ዘመን በኋላ በ14ኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ በሁለቱ ማለትም በአጼ አምደጽዮን (1314-1344) የግዕዝ ዜና መዋዕልና[168] በግብፁ ጸሐፊ አል-ዑማሪ[169] *Masalik al-Absar fi Mamalik al-Amsar* በሚል ርዕስ በተጻፈው የአረብኛ መጽሐፍ በክፍለ አህጉሩ ማለትም በደቡብ ኢትዮጵያ ከ896 እስከ 1344 ድረስ ባለው ጊዜ ውስጥ በግምት በምስራቅ ጠረፍ ከኤደን ባሕረ ሰላጤ ጀምሮ በመሀል አገር አዋሽን ጨምሮና አልፎ እስከ ዋቤ፣ ጊቤና ዓባይ ወንዞች ድረስ በሚገኘው የታላላቅ ወንዞችና ሐይቆች ምድር ላይ የኢትዮጵያ ጥንታዊና እስላማዊ የሸዋ፣ የሀዲያ፣ የይፋት፣ የወርጂ፣ የገባል፣ የአዳል፣ የሞራ፣ የለበከላ፣ የሀገራ፣ የፈድሴ፣ የግደድ፣ የነገብ፣ የዚባ፣ የሐርላ፣ የሁብት፣ የተርሳ፣ የእይም፣ የእልብሮ፣ የዜይላ፣ የእስቴ፣ የደዋሮ፣ የመንዝ፣[170] የዜጋ፣ የኩልጉራ፣ የገደያ፣ የቀድሴ፣ የሐርጋየ፣ የብቁልዘር፣ የፈጠጋር፣ የአርጎባ (የጁባ)፣ የሸርካ፣ የአረባቢኒ፣ የባሌ፣ የደራ፣ የሐረር፣[171] የጉራጌ፣[172] የስልጤና፣[173] የአውሳ[174] ወዘተ ሕዝቦች፣ አገሮች፣ ከተሞችና መንግሥታት፣ በድምሩ ከ200 በላይ በሚሆኑ የይፋት ሱልጣኔት የአስተዳደር ክልሎች[175] የሚገኙ 17 የአካባቢ ነገሥታትን፣[176] ከ2700 በላይ የጦር አበጋዞችንና[177] ከ12,000[178] በላይ መስጊዶችን ጨምሮ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪክ ሰነድ በስምና በቁጥር ተመዝግበው ተገኝተዋል።

እነዚህ ሁለቱም የአምደጽዮን ዜና መዋዕልና የአልዑማሪ መጽሐፍ በአንድነትና በተናጠል የሚገልፁት በደቡብ ኢትዮጵያ ከ1270 እስከ 1577 ድረስ ለ300 ዓመታት በመሬት፣ በሞዘት፣ በንግድና በኃይል ሚዛን ምክንያቶችና ጥያቄዎች ከሰሜን ኢትዮጵያ አዲስና ተስፋፊ የአማራ መንግሥትና ከደቡቡ ነባር የሙስሊም ሱልጣኔቶች መካከል

---

[168] Huntingford, Amda Seyon, p. 3.

[169] Al-Umari, Masalik El Absar, pp. 1-10.

[170] Huntingford, Amda Seyon, p. 57; Crawford, Itineraries, p. 81; Trimingham, Islam In Ethiopia, p.71.

[171] Ibid., Amda Seyon, p.78.

[172] Ibid..

[173] Ibid , p. 75.

[174] Ibid., p. 79.

[175] Ibid., pp. 73-79; Perruchon, Histoire des Guerres d'Amda Seyon, Roi d' Ethiopie, Journal Asiatique, Ser. 8, T. 14 (1889), pp. 323, 361.

[176] Ibid., Amda Seyon, p. 74.

[177] Ibid., Amda Seyon, p. 80.

[178] Ibid.,

የተካሄደውን ረጅም ጦርነት የመጀመሪያውን ምዕራፍ ብቻ ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ የአልዑማሪን መጽሐፍ ምንጭና ትምህርት በሚመለከት፣ ክርስቲያኑ የአማራ ንጉሥ አጼ አምደጽዮን በተጠቀሱት ነባር ሙስሊም ሕዝቦች፣ አገሮችና መንግሥታት ላይ የ1316-1332 ወረራ ካካሄደ በኋላ፣ በ1332-1338 ይህንኑ የአጼ ጦርነት ፖሊሲና ተግባር በመግለጽ የይፋት ሱልጣኔት ባለሥልጣኖች የሰላም አስተዋፅኦ ያደርጉ ዘንድ በአንድ የዜይላ ሼክ ጀማልዲን አብደላህ በተባለ የሕግና የሃይማኖት ምሁር የሚመራ አንድ ከፍተኛ የዲፕሎማቲክ መልዕክተኞች ቡድን ወደ ግብፅ መንግሥት ባለሥልጣኖች ላኩ።[179]

የይፋት ዲፕሎማቲክ ልዑካን ቡድን መሪ ሼክ ጀማልዲን አብደላህ በካይሮ ግብፅ ቆይታው ወቅት ለግብፁ አስተዋይ የቤተ መንግሥት ባለሟልና የታሪክ ባለሙያ ኢብን ፋድል አላህ አል-ዑማሪ የኢትዮጵያን የዘመኑን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች ኅብረተሰብና መንግሥት በሚመለከት ዝርዝር የታሪክ መረጃዎችን እንደሰጠው የግብፁ ጸሐፊ በመጽሐፉ ከመግለፁም በላይ ከሼኩ በተሰጡ መረጃዎች መሠረት የሰባቱን የይፋት፣ የዳዋሮ፣ የአረባቢኒ፣ የሀዲያ፣ የሸርካ፣ የባሌና የደራ ሱልጣኔቶችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ለዓለምና ለትውልድ በጽሑፍ አስታውቋል።

ሰንጠዥ 7
በ14ኛው ምዕተ ዓመት በጀማለዲን-ዑማሪ ግምት
የኢትዮጵያ የሰባት ሡልጣኔቶች የመሬት ስፋትና የሠራዊት ብዛት

| አገር | ያገር ስፋት በስኩር ኪሎሜትር | | | ሠራዊት በወታደር ዓይነትና ብዛት | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ቁመት በኪሜ | ጎን በ ኪሜ | ስፋት በስኩር/ኪሜ | የእግር ጦር | የፈረስ ጦር | ድምር |
| ይፋት | 288 | 384 | 111000 | 20000 | 15000 | 35000 |
| ደዋሮ | 96 | 38 | 3600 | 2000 | 15000 | 35000 |
| አረባቢኒ | 77 | 77 | 5900 | 10000 | 10000 | 20000 |
| ሀዲያ | 160 | 172 | 27500 | 80000 | 40000 | 120000 |
| ሸርካ | 58 | 96 | 5500 | 5000 | 3000 | 8000 |
| ባሌ | 384 | 120 | 46000 | ብዙ ሺ,ህ | 18000 | +18000 |
| ደራ | 57 | 57 | 3300 | 2000 | 2000 | 4000 |
| ድምር | 1120 | 144 | 203000 | +137000 | 103000 | +240000 |

Source: Umari, Masalik, pp. 5-16; Huntington, Amdaseyon, pp. 20-23.

179 Umari, Masalik El Absar, pp. 35, 5, 29; Trimingham, Islam In Ethiopia, pp. 72-73.





ሦስተኛ፣ በኢትዮጵያ አጠቃላይ የመካከለኛው ዘመን ታሪክ ሁለት ቁልፍ የመረጃ ምንጮች የሆኑት የአጼ አምደጽዮን ዜና መዋዕ ልና የግብፁ አልዑማሪ መጽሐፍ በ1330ዎቹ በአንድ ጊዜ ከተጻፉበት ዘመን በኋላ አንድ መቶ ዓመት ቆይቶ ሌላ የግብፅ አረብ ታሪክ ጸሐፊ አሕመድ ማክሪዚ[180] (1366-1442) በኢትዮጵያ ጉዳዮች ላይ በአንድ በኩል የዑማሪን መጽሐፍ አንብቦ በሌላ በኩል ደግሞ ራሱም ከአጎራባቹ የየመን አገር ተጨማሪና ወቅታዊ መረጃዎችን አሰባስቦ በ1430ዎቹ *በኢትዮጵያ የሙስሊም ነገሥታት እውነተኛ ታሪክ መጽሐፍ* በሚል ርዕስ በጻፈው መጽሐፍ በተለይም የኢትዮጵያ የክርስቲያንና የሙስሊም ባላንጣ ነገሥታትን ረጅምና አውዳሚ ጦርነት በሚመለከት ብዙ አዳዲስና ቁልፍ መረጃዎችን ሰጥቷል።[181]

አራተኛ፣ በኢትዮጵያ የእስልምናና የሙስሊሞች ታሪክ አንድ ሌላ ቁልፍ የመረጃ ምንጭ በኢትዮ-የመኑ ተወላጅ ሸሃበዲን አሕመድ ቢን አብደልቃድር (አረብ ፋቂህ) የሀበሻ ዘመቻ (*Futuh al-Habasha*) በሚል ርዕስ በ1535 በአረብኛ ቋንቋ ተጽፎ በኋላ በ1897 በፈረንሳዩ ረኔ በሴት ወደ ፈረንሳይኛ ቋንቋ የተተረጎመው የኢማም አሕመድ ግራኙ የ1524-1543 ዜና መዋዕል ነው። ዜና መዋዕሉ ለምዕተ ዓመታት ተጠብቆ የኖረው በታላቁ የሐረር ከተሜ መንግሥት ነው።

## የኢትዮጵያ የማኽዙማይትና የሃሽማይት-ዋላስማ ሥርወ መንግሥታት ታሪካዊ መነሻ

በ1936 ከሐረር ከተማ በኢጣሊያዊ ምሁር *በዶክተር ቼሩሊ* በተገኘው የሸዋ እስላማዊ መንግሥት (896-1285) ሰነድና በ1430ዎቹ በግብፁ ማክሪዚ በተጻፈው የይፋት ሱልጣኔት (1285-1577) ታሪክ መሠረት፣ ሁለቱንም የኢትዮጵያ የማኽዙማይትና የሃሽማይት-ዋላስማ ሥርወ መንግሥታትንና ሱልጣኔቶችን በደቡብ ኢትዮጵያ የመሠረቱት ከመካ የመጡ የቁረይሽ አረብ ነገድ በቅደም ተከተል ማኽዙማ ይትና[182] ሃሽማይት[183] የተሰኙ ሁለት ጎሳዎች ተወላጆች ናቸው። ከላይ በተጠቀሰው በዶክተር ቼሩሊ ጥናት እንደተባለው፣ ከመካ የተወሰኑ የማኽዙማዊ ጎሳ ተወላጆች በዳግማዊ ካሊፋ ዑመር ዘመን (634-644) ቀይ ባሕርን በፍለሳ ተሻግረና በዜይላ በር ወደ መሀል

180 Maqrizi, The Book of the True Knowledge of the History of the Moslem Kings in Abyssinia, Tr. by G. W. B. Huntingford, (Typescript, 1955).
181 Ibid., pp. 1-29.
182 Cuoq, Islam En Ethiopie, p. 121; Trimigham, Islam In Ethiopia, p. 58, No. 2.
183 Maqrizi, Moslem Kings, p. 11.

ኢትዮጵያ ገብተው ከጊዜ በኋላ በ896 በሐርላው ሴማዊ ምድር የኢትዮጵያን የመጀመሪያ እስላማዊ የሸዋ ሥርወ መንግሥትና ሱልጣኔት መስርተው እስከ 1285 ድረስ ለ400 ዓመታት እንዳስተዳደሩት ተረጋግጧል።[184]

በዚህ ረገድና ተግባር፥ ነቢዩ ሙሐመድ አብድሸምስ፥ ነውፈል፥ ሃሺምና አልሙጠሊብ የተሰኙ አራት ቅድመ አያቶች እንደነበሩትና ነቢዩ ራሱም የሀሺም የልጅ ልጅ እንደሆነ ይታወቃል። በማክሪዚ ዘገባ መሠረት፥ ከዚህ ከነቢዩ ሙሐመድ የሃሽማይት ጎሳ የወጡ አባላት በአገው ዘመነ መንግሥት (1100-1270) ከሂጃዝ አረቢያ በዜይላ በር ወደ ኢትዮጵያ ገብተው መጀመሪያ «ጀበርቲ» ተብሎ በሚጠራው የዜይላ ቆላማ አገር ቀጥሎም በመሀል አገር በሐርላው ምድር በሸዋ ሱልጣኔት ሰፍረውና ተጠቃሹንም ሱልጣኔት ገልብጠው በ1285 የራሳቸውን አዲስ የዋላስማ ሥርወ መንግሥትና ሱልጣኔት በዑመር ዋላስማ መሪነት መሠረቱ።[185]

በአጭርና በጥቅል አነጋገር፥ የእስልምና ሃይማኖት ከመካ በመጡ የቁረይሽ አረብ ሙስሊም ስደተኞች፥ ነጋዴዎችና አስተማሪዎች አማካይነት በሰላማዊ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ የገባው በሁለት በተለያዩ መንገዶችና ጊዜያት ነው። መጀመሪያ በ615-616 ከመካ በሹዓይባና በአዱሊስ የጠረፍ በሮች በስደት ወደ አክሱም ቤተ መንግሥት የመጡ ኢትዮ-አረብ ሙስሊሞች በሰሜን ኢትዮጵያ ሃይማኖቱን በአክሱሙ የክርስቲያን አገርና ቤተ መንግሥት አስተማሩ። ሁለተኛ፥ ከስባተኛው ምዕተ ዓመት ሁለተኛ አጋማሽ ጀምሮ ከሂጃዝ አረቢያ በዜይላ በር ወደ አዋማዊ መሀል ደቡብ ኢትዮጵያ የገቡ የማኽዙማይትና የሃሽማይት አረብ ጎሳዎች በሐርላና በሀዲያ ሴማዊና ኩሻዊ አገሮች እስልምናን የሕዝብና የመንግሥት ሃይማኖት አድርገው አስተማሩ። መሠረቱ። የእነዚህ የኢትዮጵያ የሙስሊም ሕዝቦችና መንግሥታት ዝርዝር ታሪክ በሌላ መጽሐፍ (1300-1974) በስፋት ይጠናል።


[184] Cuoq, Islam En Ethiopie, p.121.

[185] Ibid., p. 124; Maqrizi, Moslem Kings, pp. 11-12.





## የኢትዮጵያ ማኽዙማይትና የሃሽማይት ዋላስማ ሥርወ መንግሥታት የነገደ ቁረይሽ ሐረግ




Source: Watt, Muhammad (1953).

## የኢትዮጵያ የሸዋ ቀዳሚ ሱልጣኔት ረጅም የጂኦ-ፖለቲካ ታሪክ (896-1991)

በመሀል-ደቡብ ኢትዮጵያ ቁልፍ ጂኦ-ፖለቲካዊ ምድር ላይ ከ896 እስከ 1991 ድረስ በ1100 ዓመታት ውስጥ «ሸዋ» የተሰኘው ጥንታዊና ማዕከላዊ የሐርላ አገር ተለዋዋጭ ስም በግምት።

1. ከ896 እስከ 1316 ድረስ በሙገር፣ በአዋሽ፣ በከሰም፣ በጀማና በአባይ ወንዞች መካከል በጥንቱ ሴማዊ የሐርላ ምድር የኢትዮጵያ የመጀመሪያው እስላማዊ አገርና መንግሥት (ሱልጣኔት) ስያሜ።[186]
2. ከ1316 እስከ 1600 ድረስ በጥንቱ የሐርላ እስላማዊ ሱልጣኔት ምዕራባዊ ክፊል ላይ የአዲሱ ሰለሞናዊ ክርስቲያን የአማራ መንግሥት ያንድ ያስተዳደር ክልል ስያሜ።
3. ከ1600 እስከ 1889 ድረስ በኢትዮጵያ ረጅም የሕዝቦች እንቅስቃሴና ያካባቢ ጦር አበጋዞች ዘመን አሁንም በጥንቱ የሐርላ እስላማዊ ሱልጣኔት ክፊል ክልል በቱለማ፣ በሜጫ፣ በወሎና በከረዩ ኦሮሞ ሰፋሪዎች ዙሪያ መልስ ቀለበት ውስጥ የትንሹ የመንዝ አማራ ባላባታዊ መንግሥት ስያሜ።
4. ከ1889 እስከ 1936 ድረስ በወሎና በአዋሽ መካከል የኢትዮጵያ የአጼ መንግሥት ማዕከላዊ የዘውድ አውራጃ ስያሜ።
5. ከ1936 እስከ 1941 ድረስ በአዲስ አበባና ዙሪያው የኢጣሊያ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት ማዕከላዊው የአስተዳደር ክልል ስያሜ።
6. ከ1941 እስከ 1974 ድረስ በወሎ፥ በአባይ፥ በጊቤ፥ በጥቁር ወንዝና በታችኛው የአዋሽ ሸለቆ መካከል የኢትዮጵያ የአጼ መጨረሻ መንግሥት የማዕከላዊ ጠቅላይ ግዛት ስያሜ።
7. ከ1975 እስከ 1986 ድረስ በወሎ፣ በዓባይ፣ በጊቤ፣ በጥቁር ወንዝና በታችኛው የአዋሽ ሸለቆ መካከል የኢትዮጵያ የጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት የማዕከላዊ ክፍለ ሀገር ስያሜ።
8. ከ1987 እስከ 1991 ድረስ በወሎ፣ በጎጃም፣ በኢሉባቦር፣ በሲዳሞ፣ በአርሲ፣ በሐረርጌና በአሰብ ክልሎች መካከል የኢትዮጵያ ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ሰሜን ሸዋ፣ ምዕራብ ሸዋ፣ ደቡብ ሸዋና ምስራቅ ሸዋ የተሰኙ አራት ማዕከላዊ ያስተዳደር ክልሎች የወል ስያሜ እንደሆነ ይታወሳል።

በመሀል ደቡብ ኢትዮጵያ በጥንቱ የሐርላ ምድር የሸዋ ቀዳሚ የእስላም አገርና መንግሥት የተከሰተበት ዘመን (896-1285) ባንፃሩ በሰሜኑ የክርስቲያን ኢትዮጵያ የታሪክ መረጃ ያልተገኘበት

[186] Cuoq, Islam En Ethiopie, p.120-121, 145; Huntingford, pp. 2, 14-16, 22.






የ550-1300 'ጨለማ' ዘመን እንደነበር አይረሳም። በመሆኑም ከ1300 በፊት በሸዋ ሱልጣኔት ማለትም በደቡብ ኢትዮጵያ ነባር ሕዝቦችና በሰሜኑ ተከታታይ የአክሱም፣ የአገውና የአማራ ክርስቲያን መንግሥታት መካከል የመጀመሪያ ጂኦ-ፖለቲካዊ ግንኙነት መቼና እንዴት እንደተጀመረ በሥፍራና በጊዜ ሚዛን በትክክል ለማወቅ ከ14ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ጸሐፊዎች ከሥፍራና ከጊዜ ቀመር ሚዛን ውጭ በተረትና በተአምር መልክ በየወቅቱ የተዘጋጁ ብዙ የትውፊትና የገድል ባሕረ መዛግብት እምብዛም የሚረዱ የታሪክ መረጃዎችና ማስረጃዎች አይደሉም። በዚህ ረገድና ተግባር፣ ለምሳሌ በቅርቡ ከአረብ ጥንታዊ የታሪክ መረጃዎች በትክክል እስከታወቀ ድረስ በተጠቀሱት የኢትዮጵያ የተረትና የገድል ድርሳናት በአካባቢው «ሸዋ» የሚባል ጥንታዊ የእስላም አገርና መንግሥት እንደነበር አልተገለጸም።

በመጨረሻ በ1285 ገደማ ጥንታዊ የሸዋ ሱልጣኔት አገር በሁለቱ አዳዲስ የይፋትና የአማራ ተፃራሪ ሥርወ መንግሥታትና መንግሥታት መካከል በምዕራብና በምስራቅ በሁለት የፖለቲካ ክልሎች ተከፈለ።[187] የምዕራቡ አጋማሽ ሸዋ፣ በ1531 ከመላው ደቡብ ኢትዮጵያ በኢማም አሕመድ ግራኝ አመጽ ተሸንፈው እስኪባረሩ ድረስ፣ ለሁለት ምዕተ ዓመታት ተኩል (1285-1531) በአካባቢው የሙስሊም ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ ለክርስቲያን የአማራ ነገሥታት ዋናው የፖለቲካና የእስትራቴጂ መሠረትና ማዕከል ይሆናል።

[187] Huntingford, Amda Seyon, pp. 16, 22, 57.

## የኢትዮጵያ የ1855 – 1900 ታላቁ ምዕከልና ታሪክ ካርታ




ምንጭ ላጌድ ፡ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።





# ክፍል አምስት

# የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ረጅም የስያሜ ታሪክ

## የሀበሻና የአጋዓዚያን ነገዶች ጥያቄ በኢትዮጵያ ታሪክ

### የሀበሻ ታሪካዊ መነሻና ትርጉም በአረቡ ዓለም

በጦቢያ መጽሔት ቅጽ 5 ቁጥር 4፣ 1989 «ሐበሻ ማነው? ማንስ ነው ያልሆነው?» በሚል ጥያቄ በቀረበው ጽሑፍ፣ በኢትዮጵያውያን ዘንድ በልምድ ከታወቁ ብዙ ውስብስብና ተዛማጅ የኋላ ቀርነት ማለትም የእውቀት፣ የትምህርት፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና አጠቃላይ ማኀበራዊ የዕድገት ደረጃ ችግሮች ጎን ያለው አንድ መሠረታዊ የኅብረ ተሰብ፣ የታሪክና የማንነት ግንዛቤ ችግር እንደሚከተለው ይነበባል። በመጽሔቱ አቀራረብ፣

*ከሁለት ዓመት በፊት ገደማ እንደገና በአዲስ መልክ ከተዋቀረው የአቢሲኒያ ባንክ መሥራች አባላት መካከል የተወሰኑ ራሳቸውን ከባንኩ ባለድርሻነት ማግለላቸውን አስታወቁ። ዜና ሆኖ ያነጋገረው ራሳቸውን ማግለላቸው ሳይሆን ለድርጊታቸው የሰጡት ምክንያት ነበር። አቢሲኒያ (ሐበሻ) የሚለው ስያሜ በአረቦች ዘንድ አሉታዊ ትርጓሜ ስለሚሰጠው የባንኩ ስም ካልተቀየረ የለንበትም የሚል አቀራረብ ነበር ይፋ የወጣው።*

*ሐበሻ ማን ነው? በሚለው ጥያቄ ላይ እንድቆዝም ምክንያት የሆነኝ የባንኩ ባለአክሲዮኖች አባባል ብቻም አልነበረም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ይህ የቆየ የአገሪቷና የሕዝቧ አጠራር በተለያዩ ወገኖች፣ በተለያዩ አጋጣሚዎች ተዘውትሯል። የኦሮሞ ብሔርተኞች አቢሲኒያና ሐበሻ የሚለውን አጠራር ለተወሰኑ የአገሪቷ ብሔረሰቦችና ክፍሎች ስያሜ አድርገው ይጠቀሙበታል። በኡርጂና ሰይፈ ነበልባል የሚወጡትን ጽሑፎች ማየቱ በቂ ይመስለኛል። በአውሮፓ መዲናዎች አዲስ የተፈጠረችው የጎረቤት አገር ኤርትራ ተወላጆችም የኢትዮጵያ ዜጎችን በአንድነት ለመጥራት ሀበሻ የሚለውን ቃል በጥቅም ላይ እያዋሉ ነው። «ወንድም ኢትዮጵያዊ ነህ ኤርትራዊ ባለማሰት ተፈርቶ» ሐበሻ ነህ ወይ? የሚል ጥያቄ መልካም የማምለጫ ዘዴ ሆኖ ቀርቧል።*

*ለመሆኑ ሐበሻ ማነው? የሚለው ጥያቄ ለጦቢያ መጽሔት አንባቢያን ማቅረብ እፈልጋለሁ። ብዙ ጥያቄዎች አሉኝ። እንደተባለው ስሙ በአረቦች ዘንድ ጺያፍ ይዘት አለው? ቢኖረውስ አጠራሩ የራሱ መታወቂያ ነው የሚል ወገን ካለ በሌላኛው አሉታዊ አመለካከት ምክንያት አድርጎ ስሙን የመሰለ ነገር እርግፍ*

አድርጎ ይተዋል? ይህ ስም ለአገሪቷ መጠሪያ፥ ለሕዝቧ መታወቂያ ሆኖ ለብዙ ዘመናት መገልገሉ እየታወቀ ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ የተመረጠበትን ምክንያት የሚያስረዱን ባለሙያዎች ከመካከላችን እንደሚጠይፉ እርግጠኛ ነኝ። የጠንኩ ባለአክሰዮኖች ዓይነት ምክንያት እንደማይሰጠኝ ተስፋ አደርጋለሁ። ሌሎች ጥያቄዎችም ሊነሱ ይችላሉ። ይህ የቆየ ስያሜ እንደገና ነፍስ እንዲዘራና እንዲያንሰራራ የሚፈልጉ ወይም የሚገፉ ወገኖች አሉ? ለየትኛው ፖለቲካዊ ዓላማቸው? የሚል ጥያቄ የግድ ያስከትላል።

አረቦች «አልሐበሻ» የሚለው ስም ለአገራችን መቼ መጠቀም እንደጀመሩ በእርግጠኝነት መናገር ቢያዳግትም አሊያየሙ የቆየ መሆኑ አያጠያይቅም። እነሱ «አልጃሃሊያ» የድንቁርና ዘመን በሚሉት ቅድመ እስልምና ወቅት ላይ የዛሬይቱ ኢትዮጵያን «አልሐበሻ» ብለው እንደሚጠሯት ብዙ ዋቢ መጥቀስ የሚያስ ፈልግ አይመስለኝም። ኢትዮጵያ በዚያ ጊዜ ገናና ከነበሩት ሮም፥ ፋርስ፥ ሕንድ ጎን ለጎን ደጋግማ የምትጠቀስ አገር ነች። አብርሃ የተባለው የአጼ ካሌብ የጦር አበጋዝና እንደራሴ በካዕባ የነበሩትን የዓረቦች ቅድመ እስልምና ማምለኪያ ቅዱሳን ሰፈሮች ለማፈራረስ በ571 ዓም ገደማ ያስማራው በዝሆኖች የተጠናከረ ዘመቻ በዓረቦች ታሪክ እውቅ የጊዜ መለያ ታሪክ መጋጠሚያ ነው። ዓመቱ የዝሆኖች ዓመት ይባላል። ባለዝሆኖቹ ደግሞ አብርሃ አልሐበሻ (የሐበሻው አብርሃ) ይባላሉ።

ከሁሉ በላይ ግን ሐበሻ የሚለው ስም ከዓረቦች ሆነ በኋላ እስልምና ከተቀበሉ የአካባቢ ሕዝቦች ልቦና ጋር ያቆራኘው የመጀመሪያው ሙስሊሞች የሐበሻ አገር ፍልሰትና መስደድ ነበር። ነቢዩ ሙሐመድ 'ራሳችንን ለመከላከል አቅሙ ብርታቱን እስኪሰጠን ድረስ ወደ ሐበሻ አገር ሄዳችሁ እዚያው ቆዩ። የሐቀኞችና የፃድቃን አገር ናት። ንጉሡም ፍርድና ፍትሕ አዋቂና እስተዋይ ስለሆነ በእርሱ ዘንድ ማንም አይበደልምና እትትስጉ' በማለት የሰጡትን መመሪያ በመቀበል የመጡት ስደተኞች ናቸው ለዚች አገር እንግዳ ተቀባይነት፥ ለሕዝቧ ጨዋነት ምስክርነት የሰጡት። በዚህ መሠረት ነው ነቢዩ 'ሐበሻን አትንኩ፥ ሐበሻ ላይ በግድ የማስለም ዘመቻ አታውጁ' ብለዋል የሚባለው። በዓረቦች ዘንድ 'ሐበሻ' የሚለው ስም በታላቅ አክብሮትና ባለውለታነት እንጂ በአሉታዊ አመለካከት የተንጸባረቀበት ጊዜ የለም።

ዓረቦች ሌሎች ሕዝቦችን ዝቅ አድርገው የሚመለከቱበት አንዱ መመዘኛ ከሰማያት የወረዱ የሚሉዋቸው ሦስቱን ባለመጽሐፍ ሃይማኖቶች ከመቀበልና ባለመቀበል ላይ የተመሠረተ ነው። 'ሓመጅ' በማለት እንደአሕዛብ የሚያንቋሽሿቸው ተራ ውስጥ «ሐበሻ» አልነበረችም። ምክንያቱም ግልፅ ነው። ከእነሱ በፊት አይሁዳዊነትን፥ ክርስትናንና እስልምናን የተቀበለ ሕዝብ አገር ናትና። እስልምናም ቢሆን መዲና ከመግባቱ በፊት አክሱም ላይ ተሰብኳል።

አቢሲኒያ የሚለው የሐበሻ የፈረንጅኛ አጠራር ዘዬው ምንጩ ይህ የዓረብኛ ቃል መሆኑ የሚያጠያይቅ አይመስለኝም። ፈረንጆች አገራችንን በዚህ ስያሜ አማካኝነት ለቀረው ዓለም አስተዋውቀዋታል። አሁንም 'ሀበሻ' የሚለውን ስም ዓረቦች ከየት አመጡ የሚለው ጥያቄ መልስ አላገኘም። ለቃሉ አመጣጥ ብዙ መላ ምቶች ቢሰጡም ሁለቱን ብቻ እንመለከታለን። አንደኛው ሐበሻ የሚለው ቃል መሠረቱ 'ሐቢሽ' ከሚለው የዓረብኛ ቃል ተገኘ የሚለው ነው። «ሀቢሽ» ትርጉሙ ቅይጥ ወይም የተደበላለቀ ማለት ነው።





ብዙ ሕዝቦች በአንድነት ተቀይጠው ስለሰፈሩባት ስያሜው ተሰጣት የሚል ማብራሪያ እናገኛለን።

ሌላው ደግሞ 'ሐበሻ' የሚለው ቃል ከደቡብ ዓረቢያ ፈልሰው በደጋው ኢትዮጵያ ክፍል ከሰፈሩት ዋና ዓረብ ነገዶች አንዱ ከነበረው «ሐበሻ» ጋር ያቆራኙታል። ሁለተኛ ደግሞ 'አግዓዚ' የሚባል እንደነበረ በኢትዮጵያ የታሪክ ማስተማሪያ መጻሕፍት ስንማረው የነበረው ነው። አጋዓዚያን ለግዕዝ ቋንቋ ስማቸውን ሲያበረክቱ 'ሐበሻ' ደግሞ ለዚህ ለቆመው የአገሪቱ መጠሪያ ምንጭ ነበረ ወደሚለው ድምዳሜ መድረሱ ያስኬድ ይሆን? የታሪክ ባለሙያዎቻችን ምን ይላሉ?

በማለት መፅሔቱ ሊመለስ የሚገባ ጥያቄ ሰንዝሯል።

## በኢትዮጵያ ታሪክ የሀበሻና የአጋዓዚያን ጥያቄ ማብራሪያ

ከሁሉ በፊት በዚህ ጥናት ከላይ በዝርዝር እንደተመለከተው «ሀበሻ» የተሰኘ ስም በኢትዮጵያ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በሰነድ ተጽፎ የተገኘው በዘመነ ክርስትና በ183[188] በደቡብ አረቢያ በጥንታዊ የማሪብ ከተማ በሳባ ቋንቋና ፊደል በተጻፈው በአንድ የአረብ መስፍን ረጅም ዜና መዋዕል «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት»[189] ተብሎ በአንቀጽ 13፥ 20፥ 28፥ 32 በሰፈረው ታሪክ ነው። «ግዕዝ» የተሰኘ የሕዝብና የአገር ስም ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ በታሪክ ሰነድ ተጽፎ የተገኘው በ300 ዓመተ ምህረት አካባቢ በቀይ ባሕሩ የአዱሊስ ወደብ በግሪክ ቋንቋና ፊደል በተፃፈው በአንድ የአክሱም ንጉሥ ዜና መዋዕል «የጋዝ፥ የአጋሜ፥ የአገው፥ የአድዋ፥ የሰሜን፥ የቤጃ ሕዝቦች»[190] ተብሎ በቀረበው ታሪክ ነው።

ሁለተኛ፥ የግዕዝ ቋንቋና ፊደል ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ የተገኘበት ዘመን ደግሞ በዘመነ ክርስትና በ2ኛው ምዕተ ዓመት አካባቢ ተጽፎ በቅርቡ በ1950ዎቹ በአርኪኦሎጂ ጥናት ከትግራይ በተገኘውና «የአክሱማውያን ንጉሥ ገደር» በሚለው አጭር ታሪካዊ ዜና መዋዕል[191] ነው። በተጨማሪም፥ ከላይ እንደተመለከተው፥ ለግዕዙ ቋንቋ፥ ፊደልና ጽሕፈት ግዕዝ፥ ካዕብ፥ ሳልስ፥ ራዕብ፥ ሐምስ፥ ሳድስና ሳብዕ የተሰኘው የድምፅ፥ የንግግር፥ የጽሕፈትና የንባብ ሕግና ሥርዓት የተቀረጸለት በአጼ ኢዛና ዘመነ መንግሥት (320-344) ነው።[192]

---

[188] Kobishchanov, Axum, p. 50.

[189] S. Hablesellasie, History, p. 76.

[190] Cosmas, Christian Topography, pp. 60-61; Kammerer, Essai Sur L'Histoire, p. 90.

[191] Coquote et Drewes, "Les Monuments", p. 37.

[192] Littman, DAT, TV, Inscriptions, Nos. 9-11.

ይህ ሁሉ ከሆነና ከታወቀ በኋላ ኢጣሊያዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ ሙሴ ካርሎ ኮንቲ ሮሲኒ (1872-1949) *በጆርናል አሲአቲክ* ቁጥር 18 ጁላይ/ሴፕቴምበር 1921 «የሐበሻት ዘመቻዎችና ግዛቶች በአረቢያ» «*Expeditions et Possessions Des Habashat En Arabie» Journal Asiatique, Ser. 18, 1921)* በሚል ርዕስ ባሳተመው ጽሑፍ ከላይ ከቀረቡ ሁለት ታሪካዊ ሰነዶች ማለትም ከማሪቡ የ183 የሳባ ቋንቋ ዜና መዋዕል «ሀበሻት» የተሰኘውን ስም በመውሰድ ከአዱሊስ የ300 የግሪክ ቋንቋ ዜና መዋዕል «ጋዛ» ከተባለው ስም ጋር አቀናጅቶ በዓመተ ዓለም በግምት ከ7ኛው ምዕተ ዓመት ጀምሮ «በኋላቀሩ» የአፍሪካ ዓለም የኢትዮጵያን ጥንታዊ የአክሱማውያን መንግሥትና ሥልጣኔ የፈጠሩ ኃይሎች ናቸው በማለት «ሀበሻ» እና «አጋዓዚያን» የሚላቸውን ሁለት «ምርጥ» ሴማዊ የአረብ ነገዶች ፈጥሮ ለዓለምና ለትውልድ ተረቱን በድፍረት አሳወቀ።[193]

ለማንም የሚገርመው ጉዳይ ግን በተጠቀሰው ጽሑፍ፣ ሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያ ስድስት ምዕተ ዓመታት በአረቢያና በኢትዮጵያ አጎራባች አገሮች በጥንታዊ የሳባ፣ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች በተጻፉና ከላይ በቀረቡ የማሪብ፣ የአዱሊስ፣ የአጼ ኢዛና፣ የአጼ ካሌብና የንጉሥ አብርሃ ታሪካዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች መሠረት፣ የተለያዩ የአክሱም ነገሥታት ከኢትዮጵያ ቀይ ባሕርን ተሻግረው በአረቢያ ቢያንስ በአራት ልዩ ልዩ ክፍለ ዘመናት ያካሄዱዋቸውን ወታደራዊ የእስትራቴጂ፣ የግዛትና የገበያ ዘመቻ ዎችን በትክክል ካስቀመጣቸው በኋላ ከጥናቱ ተጨባጭ ሰነዳዊ መረጃዎችና ግኝቶች ውጭ የኢትዮጵያን አገር በቀል ባህል፣ ታሪክና ሥልጣኔ የሚያፈርስ ዘረኛ አስተያየቱን እንደሚከተለው ሰነዘረ።

በኢጣሊያኑ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ በሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ ብርቱ እምነትና ትምህርት መሠረት፣ በዘመነ ክርስትና በመጀመሪያው ስድስት ምዕተ ዓመታት ከኢትዮጵያ ተነስተው ከላይ የቀረቡትን የእስትራቴጂ፣ የግዛትና የገበያ ዘመቻዎች ያካሄዱ ኢትዮጵያውያን ነባርና ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦች ሳይሆኑ አስቀድሞ በግምት ከ1000 ዓመታት በፊት ገደማ ማለትም በ700-500 ዓመተ ዓለም አካባቢ ከምድረ አረቢያ ቀይ ባሕርን በባቤልመንደብ ሰርጥ ተሻግረው ለመጀመሪያ ጊዜ «ኋላቀሩ» በተባለው የአፍሪካ ምድር በነበሩ ኩሻዊ ሕዝብ ላይ በኋላ «ለምርጥ» ሴማዊ የአክሱሙ መንግሥትና ሥልጣኔ መሠረትና መነሻ የሚሆነውን ሴማዊ አገርና ኅብረተሰብ በየሀ

[193] Conti Rossini, "Expeditions et Possessions", pp. 5-36.





ደጋ አምባ ላይ የቆረቆሩና «ሀበሻት» እና «አጋዓዚያን»[194] የተሰኙ ሁለት ወራሪ የአረብ ነገዶችና ተወላጆች ናቸው።

ባጭሩ፣ ሙሴ ኮንቲ ሮሲኒና ተባባሪዎቹ የጀርመን፣ የኢጣሊያ እና የይሁዲ ሴሚቲስት የቋንቋና የታሪክ ምሁራን ለምሳሌ አውጉስት ዲልማን (1823-1894)፣ ኢኞሲዮ ጉይዲ (1844-1935)፣ ኢኖ ሊትማን (1875-1958)፣ በኋላም ኤድዋርድ ኡለንዶርፍ፣ ዎልፍ ሌስላውና ብዙ ሌሎችም ከተማሪዎቻቸውና ከተከታዮቻቸው ጋር የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥትና ሥልጣኔ ፈጣሪ ባለቤቶች «ሀበሻት» እና «አጋዓዚያን» የተሰኙ ሁለት ሴማዊ የአረብ ነገዶች ናቸው የሚል ተረታቸውን በስመ ሳይንስ ለማሳመን «የሳባ ፊደል» ነው የሚሉትን የኢትዮጵያን አገር ወለድ የጽሕፈት ሥርዓትና «ሴማዊ» የተሰኙ ስምንት የግዕዝ፣ የትግረ፣ የትግሬ፣ የአማራ፣ የአርጎባ፣ የሐረሪ፣ የጉራጌና የጋፋት ቋንቋ ማኅበረሰቦችን እንደዋና መረጃዎች አድርገው ያቀርባሉ።[195]

ነገር ግን፣ ከ1950ዎቹ ጀምሮ ባለፉት አምሳ ዓመታት ውስጥ በከፍተኛ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምር በተገኙ ዘመናዊ የአርኪኦሎጂና የሊንጉዊስቲክስ ማለትም የሥነልሳን መረጃዎችና ግኝቶች መሠረት፣ አንደኛ፣ የኢትዮጵያ ጥንታዊ የግዕዝ ቋንቋ፣ ፊደልና ጽሕፈት የተገኘው፣ የኢጣሊያን፣ የጀርመንና የይሁዲ ሴሚቲስት የቋንቋና የታሪክ ምሁራን እንደገመቱት፣ በአረቢያ ዛሬ ከገጸምድር ከጠፋው የሳባ ቋንቋ፣ ፊደልና ጽሕፈት ሳይሆን ከራሱ ከኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአማት ቋንቋ፣ ፊደልና ጽሕፈት ነው።[196] ሁለተኛ፣ በጥንቱ ዓለም ሴማዊ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦች በአረቢያና በመካከለኛው ምስራቅ አገሮች ከአፍሪካ በፍለሳና በሰፈራ እንቅስቃሴ ከመገኘታቸው በፊት ቢያንስ ለ8,000-10,000 ዓመታት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ይኖሩ እንደነበር አሁንም የቋንቋ ሳይንቲስቶች ያስተምራሉ።[197]

[194] Ibid., pp. 6-20.

[195] Littmann, DAT, IV, Inscriptions; E. Ullendorff, The Semitic Languages of Ethiopia (1955); W. Leslau, "South-East Semitic: Ethiopic and south Abrbic", "South-East SemiticAmerican Oriental Society, Vol. 63 (1943), pp. 4-14; Budge, History, pp. 551-553,557.

[196] Drewes, Inscriptions; Schneider, "Deux Inscriptions".
________, " Histoire".
________, "Evolution of the Ethiopian Writing".
________, " Daamatite State, Kings, and Gods".

[197] Murtonen, Early Semitic: A Diachronical Inquiry into the Relationship of Ethiopia to the Other so-called South-East Semitic Languages, (Leiden: Brill, 1967):
___, G. Hudson, "Language Classification and the Semitic Prehistory of Ethiopia", Folia Orientalia, Vol. 18 (1977), pp. 119-166.

ስለሆነም የኢትዮጵያ ጥንታዊ መንግሥት፣ ሥልጣኔና ታሪክ ከአረቢያ «ሀበሻ» እና «አጋዓዚያን» የተሰኙ ሴማዊ የአረብ ነገዶች ሥራ ነው የሚለው የእነኮንቲ ሮሲኒ ቲዮሪ በተጨባጭ የታሪክ መረጃ ላይ ያልተመሠረተ ተረት ነው። በሌላ በኩል ሀበሻ የተሰኘው ስም ግን አጎራባቹ አረቦች ለሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ጥቁር ሕዝቦች በሙሉ የሰጡት የመጠሪያ ስም ነው። በመሆኑም ስሙ የኢትዮጵያ ሕዝብና ታሪክ አንድ ሕያው አካልና መግለጫ ነው ለማለት ግን ይቻላል።

## የአረቦቹ የአፍሪካውያን ግንዛቤና ስያሜ

የአፍሪካ ምድር ሕዝቦች ጥንታዊ ስያሜዎች ከሞላ ጎደል ሁሉም ከሦስቱ የይሁዲዊ፣ የግሪክና የአረብ ሕዝቦች የተሰጡ የሕዝብና የአገር መጠሪያ ስሞች ናቸው። ለምሳሌ በቅደም ተከተል በታችኛው የዓባይ ሸለቆ፣ በላይኛው የዓባይ ሸለቆና በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የካም-ኩሽ ልጆችና ዘሮች ናቸው ተብለው የተጠቀሱት ሦስቱ የጥቁር አፍሪካ የመጀመሪያ ሕዝቦችና መንግ ሥታት ግብፅ፣ ኩሽና ፑንት በዓለም ሥልጣኔ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በጽሑፍ የታወቁት ከዛሬ 3500 ዓመታት በፊት በነቢዩ ሙሴ ተጻፈ በሚባለው በይሁዳውያኑ የፍጥረት ታሪክ መጽሐፍ ማለትም በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ 10 ነው።

እንዲሁም በጊዜና በታሪክ ከሴማዊ ይሁዳውያኑ በኋላ የተነሱት ግሪኮች ኩሽ/ኑቢያን ጨምሮ ከምድረ ግብፅ በታች ለሚኖሩ መላ የጥቁር አፍሪካ ነባር ሕዝቦች «ኢትዮጵያ» የተሰኘ አንድ የወል ስም ሰጡ። የስሙም ገላጭ ትርጉም ጥቁር ሕዝብ/ሕዝቦች ማለት ነው። አረቦች ደግሞ በዘመናቸውና በቋንቋቸው፤

1) በአጠገባቸው በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለሚኖሩ ጥቁር ሕዝቦች «ሀበሻ» የተሰኘ የወል ስያሜ፤
2) በጥንታዊ የግሪክ፣ የሮማውያንና የአረብ ሰነዳዊ መረጃዎች መሠረት፣ በግምት ከ100 ዓመተ ዓለም እስከ 1400 ዓመተ ምህረት ገደማ ድረስ ለ1500 ዓመታት በአፍሪካ ቀንድ ምሥራቃዊ ጠረፍ ማለትም በሕንድ ውቅያኖስ ዳርቻ በሰሜን ከጉአርዳፋይ ጫፍ አንስቶ በደቡብ ምስራቅ እስከ ዛንዚባርና ሞዛምቢክ ድረስ በሚገኘው ረጅም ክፍለ አህጉር ሰነበሩና አዛኒያ ተብለው ለሚታወቁ ጥቁር የባንቱ አፍሪካውያን «ዘንጅ»[198] የተሰኘ የወል ስያሜ፤
3) ኩሽ/ኑቢያን ጨምሮ በማዕከላዊና በምዕራብ አፍሪካ ክፍላተ አህጉር ለሚኖሩ ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦች ደግሞ «ሱዳን» የተሰኘ የወል ስያሜ ማለትም በሦስት በተለያዩ ክፍላተ አህጉር ለተሰራጩ አፍሪካውያን ሦስት ልዩ ልዩ የወል ስሞች እንደሰጡ ከታሪክ መረጃና ትምህርት ይታወቃል። በአረቦቹ ዘንድና እንደበት የሦስቱም ስያሜዎች ገላጭና ማዕከላዊ ትርጉም አረብ ያልሆነ ጥቁር ሰው ጥቁር ሕዝብ እንደማለት ነው።

በመሆኑም «ሀበሻ» አረቦች ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦችን ከሚጠሩባቸው ሦስት የወል ስሞች አንዱና የመጀመሪያ ስያሜ ነው። ነገር ግን «ሀበሻ» «ሀቢሽ» ከሚለው የአረብ ቅጽል የወጣ ቅይጥ፣ ድብልቅ ማለት ነው የሚለው ተረትና ትውፊት በዚህ ጥናት ከላይ ከቀረበው ከስሙ ውስብስብና ረጅም ታሪክ ጋር አብሮ የማይሄድ ኢ-ታሪካዊ ትረካ ነው። ምክንያቱም ጥቁር ሰው ማለት ቅይጥ ወይም ድብልቅ ዕቃ፣ ነገር ነው ማለት አይደለምና።

## የኢትዮጵያ የአገርና የመንግሥት ስያሜ ረጅም ታሪክ

ከጊዜና ከታሪክ አኳያ የአረቦቹ «ሀበሻ» የሚለው ገላጭ የሕዝብና የአገር ስም በኢትዮጵያ ምድር፣ ቤተ መንግሥትና ታሪክ ከኦፊሴላዊ ፕሮቶኮል አንፃር ለመጀመሪያም ለመጨረሻም ጊዜ በሰነድ ተጽፎ የተገኘው አረቢያ የኢትዮጵያ የባሕር ማዶ ግዛት በነበረበት ዘመን በሦስቱ የግሪክ፣ የሳባና የግዕዝ ቋንቋዎች የፀሬኔ ጦርነት አስመልክቶ በድንጋይ ላይ በተቀረፀው በአጼ ኢዛና ዜና መዋዕል በሁለቱ የሳባና የግዕዝ ቋንቋ ቅጅዎች «ኢዛና የአክሱም፣ የሕሜር፣ የረይዳን፣ የሐበሠት፣ የሳባ፣ የሰልሔን፣ የፅያሞ፣ የካሱ፣ የቤጃ፣ ንጉሠ ነገሥት የድል አድራጊው መሕርም ልጅ»[199] ተብሎ በተገለፀው ታሪክ ነው። ከዚያ በፊትና በኋላ ኢትዮጵያውያን «ሀበሻ» የሚለውን ስም የአገራቸውና የመንግሥታቸው ኦፊሴላዊ ስያሜና መግለጫ አድርገው የተጠቀሙበት ሥፍራና ጊዜ መኖሩ እስከ ዛሬ ድረስ ከታሪክ መረጃና ትምህርት አይታወቅም።[200]

በመሆኑም ከላይ በጦቢያ መጽሔት በቀረበው ጽሑፍ ሀበሻ የተባለው «ስም ለአገሪቱ መጠሪያ፣ ለሕዝብ መታወቂያ ሆኖ ለብዙ

___, "Geolinguistic Evidence for Ethiopian Semitic Prehistory", Abbay, Vol. (1978), pp. 71-85; Bernal, Black Athena, pp. XXIV-XXVI, 11-12.

[198] Doresse, Histoire Sommaire, pp. 116-134.

[199] Littmann, DAT, Vol. 4, Inscriptions, Nos. 6, 7, pp. 10-12.

[200] Schneider, "Histoire", p. 49.

ዘመናት ማገልገሉ እየታወቀ» ኢትዮጵያ የሚለው ስያሜ የተመረጠበትን ምክንያት አስመልክቶ የተነሳውን ትምህርታዊ የግንዛቤ ጥያቄ በሚመለከት፣ ከታሪክ አኳያ ከሁሉ በፊት «ኢትዮጵያ» የሚለው የግሪክ ስም በግምት ከ1500 ዓመተ ዓለም እስከ 63 ዓመተ ምህረት ድረስ በ1563 ዓመታት ውስጥ በ13 ልዩ ልዩ ደራሲያን በተፃፉ በ15 ልዩ ልዩ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በአርባ በሚቆጠሩ ሥፍራዎችና ጊዜያት ማለትም፤

*በኦሪት ዘፍጥረት 2:13፣ በኦሪት ዘሁልቁ 12:1፣ 8:9፣ በመጽሐፈ ነገሥት ካልዕ 19:9፣ በመጽሐፈ ዜና መዋዕል ካልዕ 14:9፣ 16:8፣ 21:16፣ በመጽሐፈ አስቴር 1:1፣ 8:9፣ በመጽሐፈ ኢዮብ 28:19፣ በመዝሙረ ዳዊት 68:31፣ 87:4፣ በትንቢተ ኢሳያስ 11:11፣ 18:1፣ 20:3-5፣ 37:9፣ 43:3፣ 45:14፣ በትንቢተ ኤርምያስ 13:23፣ 38:7፣ 10፣ 12፣ 39:16፣ 46:9፣ በትንቢተ ሕዝቅኤል 29:10፣ 30:4:5:9፣ 38:5፣ በትንቢተ ዳንኤል 11:43፣ በትንቢተ አሞፅ 9:7፣ በትንቢተ ናሆም 319፣ በትንቢተ ሶፎንያስ 2:12፣ 3:10፣ በሐዋሪያት ሥራ 8:27፤* በተሰኙ ምዕራፎችና ቁጥሮች በላይኛው የዓባይ ሸለቆ በዘመኑ በግብፃውያኑ «ኑቢያ»፣ በይሁዳውያኑ ደግሞ «ኩሽ» ተብሎ ከላይ የቀረበ ያንድ ጥንታዊ የጥቁር አፍሪካ የሕዝብና የአገር ስም ትርጉም ነው።

የይሁድውያኑ ብሉይ ኪዳን (መጽሐፍ ቅዱስ) በ280-150 ዓመተ ዓለም በግብፁ የእስክንድሪያ ከተማ ከይሁዳውያኑ ቋንቋ ወደ ግሪክ በተተረጎመ ጊዜ በመጽሐፉ ኩሽ የተሰኘው የሕዝብና የአገር ስም «ኢትዮጵያ» ተብሎ ተተካ። እንዲሁም ከስምንት ምዕተ ዓመታት በኋላ በዘመነ ክርስትና በ5ኛው ምዕተ ዓመት በአክሱም ከተማ መጽሐፍ ቅዱስ ከግሪክ ቋንቋ ወደ ግዕዝ በተተረጎመ ጊዜ አሁንም «ኢትዮጵያ» ተብሎ ተገለበጠ።

በመጽሐፍ ቅዱስ በይሁዳውያኑ «ኩሽ» በኋላ በግሪኮች «ኢትዮጵያ» የተሰኘው የዚህ የአንድ የጥቁር አፍሪካ ጥንታዊ የሕዝብ፣ የአገርና የመንግሥት ስም ታሪካዊ መነሻና መጨረሻ አስመልክቶ ይህ ጸሐፊ *የኢትዮጵያ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ* በተሰኘው ጥናቱ አሳጥሮ እንዳስቀመጠው፤

በጥንትና በመካከለኛ ዘመናት የዓለም ታሪክ *ኩሽ፣ ኑቢያ፣ ኢትዮጵያ፣ ናፓታ፣ ሚሮዌ፣ ናበዳ፣ መኩሪያ፣ አልዋና ፉንጅ* ተብለው በብዙ ተከታታይ ስሞች በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የሚታወቁ ማኅበረሰቦች፣ ሕዝቦችና አገሮች በግምት ከ3000 ዓመተ ዓለም እስከ 1820 ዓመተ ምህረት ድረስ በ4820 ዓመታት ውስጥ በላይኛው የዓባይ





ሸለቆ በሰሜን ከዛሬው የአስዋን ግድብ አጠገብ፣ ከዓባይ ወንዝ የመጀመሪያው ፏፏቴ አንስቶ በደቡብና በምስራቅ እስከ አክሱማውያኑ ያልተወሰነ ጠረፍ ክልል ድረስ ባለው ምድር በየጊዜው በፈረቃ የተነሱ ተዛማጅ የጥቁር አፍሪካ ጥንታዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ናቸው።

ከእነዚህ ስሞች ኩሽ፣ ኑቢያና ናፓታ ለተጠቀሱት ተዛማጅ ሕዝቦችና አገሮች የጥንታዊ ግብፃውያንና የሴማውያን ስያሜዎች ናቸው። ግሪኮች ግን የተጠቀሱትን ሕዝቦችና አገሮች ጨምሮ ከግብፅ በታች የሚገኙ ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦችንና አገሮችን በሙሉ የጎሳ፣ የቋንቋ፣ የባህል፣ የሥፍራና የጊዜ ምርጫና ልዩነት ሳያደርጉ በጥቁር የቆዳ መስፈርት ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን በሚል የወል ስያሜ ይጠሩ እንደነበር ተገልጿል። ሚሮዌ ለጥንታዊው ኑቢያ በኋላ የግሪኮች፣ የሮማውያንና የአክሱማውያን ስም ነው። ናበዳ፣ መኩሪያ፣ አልዋና ፉንጅ ደግሞ በዘመነ ክርስትና በክልሉ የተነሱ አናሳ መንግሥታት ናቸው። የእነዚህ ጥንታዊ የላይኛው ዓባይ ሸለቆ ሕዝቦችና መንግሥታት ሥልጣኔና ቋንቋ እስከ ዛሬ ድረስ ሳይገለፅና ሳይታወቅ በከርሰ ምድር ተቀብሮ ይኖራል።

ከጊዜ በኋላ በጦርነት፣ በሃይማኖትና በንግድ መንገዶችና ምክንያቶች ከ640ዎቹ ጀምሮ በአካባቢው የተስፋፉ አረቦች የተጠቀሱ ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦችንና አገሮችን «ሱዳን» በሚል የአረቦች ስም መጥራት ጀመሩ። ከላይ እንደተባለው፣ «ሱዳን» (ቢላድ አል-ሱዳን) የሚለው ስም ራሱ ለጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦች የአረቦቹ የወል ስያሜ ነው። ለምሣሌ ነቢዩ ሙሐመድ ኢትዮጵያውያን ወዳጆቹን «ሀበሾች» እና «ሱዳኖች»[201] እያለ በተለዋዋጭ ስሞች ይጠራቸው ነበር። ባጭሩ ኢትዮጵያ፣ ሱዳን፣ ሀበሻና ዝንጅ የተሰኙ ስያሜዎች ሁሉ ከነጭ ግሪኮችና አረቦች ለጥቁር አፍሪካውያን የተሰጡ ገላጭ የሕዝብና የአገር ስሞች ናቸው።

ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ጥንት በላይኛው ዓባይ ሸለቆ በመጽሐፍ ቅዱስና በዓለም ታሪክ በይሁዳውያኑ «ኩሽ»፣ በግብፃውያኑ «ኑቢያ»፣ በግሪኮቹ «ኢትዮጵያ»፣ በአረቦቹ «ሱዳን» የተሰኘው የጥቁር አፍሪካ ሕዝብና መንግሥት በዘመኑ ከሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ነባርና ሉአላዊ የፑንት፣ የደአማት፣ የአክሱም፣ የአገው፣ የሰሜን/ፈላሻ ተከታታይና ተዛማጅ ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር ብሎም ከዛሬው የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ኢትዮጵያውያን ጋር በሥፍራ፣ በጊዜ፣ በቋንቋ፣ በባህል፣ በሃይማኖት፣ በሥርዓትና በታሪክ ቀጥተኛ

[201] Norris, "The Himyaritic Tihama", pp. 108.

ግንኙነት መኖሩን በተጨባጭ መልክና መንገድ የሚያሳይ የሰነድ፣ የቋንቋ ወይም የአርኪኦሎጂ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ ገና አልተገኘም።

በተጨማሪም የጥንት ይሁዳውያንንና ፑንታውያንን ታሪካዊ ግንኙነት በሚመለከት፣ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ለዛሬ ኢትዮጵያውያን ከብዙ ሺህ ዓመታት በፊት አንድ ታሪካዊ መነሻና ምንጭ የሆነው የፑንት ሕዝብና መንግሥት በግምት ከ1500 እስከ 400 ዓመተ ዓለም ድረስ በ1000 ዓመታት ውስጥ በይሁዳውያኑ መጽሐፍ ቅዱስ *በአሪት ዘፍጥረት ም. 10 ቁ 6፣ በትንቢተ ኤርምያስ ም. 46 ቁ 9፣ በትንቢተ ሕዝቅኤል ም. 27 ቁ 10፣ ም. 30 ቁ 5፣ ም. 36 ቁ 5* በድምሩ በአምስት ልዩ ልዩ ሥፍራዎችና ጊዜያት ብቻ በጨረፍታ ተጠቅሷል።

በአጭርና በጥቅል አነጋገር፣ በዘመነ ክርስትና *በመጽሐፍ ቅዱስና በክብረ ነገሥት* ከመካከለኛው ምስራቅና ከግብፅ በግዕዝ ትርጉም ወደ ኢትዮጵያ ከመግባታቸው በፊት ኩሽ-ኑቢያውያንና ይሁዳውያን የተሰኙ ጥንታዊ ሕዝቦች ከጥንቱ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካውያን ጋር በንግድ፣ በሃይማኖት፣ በባህል የነበራቸውን ቀጥተኛ ግንኙነት የሚያሳይ ተጨባጭ የታሪክ መረጃና ትምህርት እስከ ዛሬ ድረስ ገና አልተገኘም።

በሌላ በኩል፣ በዚህ ጥናት ከላይ እንደተመለከተው፣ በዓመተ ዓለም በግምት ከ2800 እስከ 1000 ድረስ ለ1800 ዓመታት ገደማ በጥንታዊ የግብፅና የፑንት አገሮችና መንግሥታት መካከል በምድርና በባሕር መንገዶች በንግድ፣ በሃይማኖትና በባህል ረጅም የመስተጋብርና የመወራረስ ዘመናትና እንቅስቃሴዎች እንደነበሩ ከግብፃውያኑ የሃይሮግላፊክስ ዘገባዎችና ግኝቶች አሁን በሥፍራ፣ በጊዜና በታሪክ መስፈርት በትክክል ታውቋል።

ይህ በጥንታዊ የግብፅና የፑንት ሕዝቦች መካከል በንግድ፣ በሃይማኖትና በባህል የነበረው ረጅም ግንኙነት በብዙ የውስጥና የውጭ ግፊቶችና ምክንያቶች በ1000 ዓመተ ዓለም አካባቢ ከተቋረጠ በኋላ በሚቀጥሉት 1640 ዓመታት ውስጥ፤

አንደኛ፣ በ700-100 ዓመተ ዓለም አካባቢ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በሰሜኑ ደጋ ክፍል የኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአማትና የአክሱም ሉአላዊ መንግሥታት በተከታታይ ተነሱ።

ሁለተኛ፣ በተመሳሳይ ዘመን እንዲሁም በአጎራባቹ ደቡብ አረቢያ በዕጣን፣ በሙጫ፣ በከርቤና በቀረፋ ቅመማቅመም ምርትና ንግድ የተሰማሩ የሚና፣ የሳባ፣ የቀጣባን፣ የሂሚያርና የሃድራማዊ እናሳ መንግሥታት ተከሰቱ።





ሦስተኛ፣ በዓመተ ዓለም በ6ኛው ምዕተ ዓመት በላይኛው የዓባይ ሸለቆ የሚሮዌ[202] መንግሥት ተነሳ።

አራተኛ፣ ጥንታዊው የግብፅ መንግሥት በ525-404 በፋርሳውያን፣ በ332-30 በግሪኮች እጅ ወደቀ። ከ30 ዓመተ ዓለም እስከ 642 ዓመተ ምህረት ድረስ በሮማውያን ተገዛ። በ642 በጦር ተይዞ የአረቦች አገር ሆነ።

ባጭሩ እነዚህ የዘመኑ ታላላቅ የሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር፣ የዓባይ ሸለቆ፣ የቀይ ባሕር፣ የአረቢያና የመካከለኛው ምስራቅ ሕዝቦችና አገሮች የጂኦ-ፖለቲካ ክስተቶች፣ ኃይሎች፣ ለውጦችና እንቅስቃሴዎች ናቸው በተጠቀሰው ረጅም ዘመን በንግድ፣ በሃይማኖት፣ በቋንቋ፣ በባህልና በስትራቴጂ ጉዳዮች፣ መስኮችና መንገዶች በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር ኢትዮጵያውያንን ከነባር የቀይ ባሕር፣ የአረቢያ፣ የዓባይ ሸለቆ፣ የመካከለኛው ምስራቅና የሜዲትራኒያን ጥንታዊ ሕዝቦች፣ መንግሥታትና ሥልጣኔዎች ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ በልዩ ልዩ መንገዶችና ደረጃዎች በቅርብ ያገናኙዋቸው። ለምሳሌ በዚሁ ዘመን ነበር ከውጭ ግሪኮች «ኢትዮጵያ» አረቦች ደግሞ «ሀበሻ» የተሰኙ የወል ስያሜዎችን ለሕዝቡና ለአገሩ የሰጡት።

ከሁሉም በላይ በዚሁ በተጠቀሰው ዘመንና መንገድ ነበር በአገሩ ነባርና ሉአላዊ የደአማት-አክሱም አዋማዊ ኅብረተሰብና መንግሥት የኢኮኖሚ ታህታይና የፖለቲካ ላዕላይ መሠረቶችና መዋቅሮች ላይ የተጠቀሱት የውጭ ኃይሎች የተለያዩ የንግድ፣ የባህል፣ የትምህርት፣ የፖለቲካና የእምነት ግፊቶች ከሦስቱ መለኮታዊና አሀዳዊ የክርስትና፣ የኦሪትና የእስልምና ሃይማኖቶች ጋር ለኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች ኅብረተሰብ፣ መንግሥትና ታሪክ ክስተትና ዕድገት ሁሉም አንፃራዊ አስተዋፃኦ ያደረጉት።

የዚህን የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ባህሎችና ሃይማኖቶች ኅብረተሰብና መንግሥት ስያሜ በሚመለከት፣ ከታሪክ ትምህርትና ተግባራዊ ልምድ እንደሚታወቀው፣ በጥንት ዘመን በየትኛውም ክፍለ ዓለም የሕዝቡና የአገር ስም ጥያቄ የሚነሳው በአመዛኙ ከአገር መሪ፣ መንግሥት ወይም ከተማ ጋር በተያያዘ መንገድና መልክ ነው። ከዚህ አኳያ ለምሳሌ፣

1. በዓመተ ዓለም በ4ኛው ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ በሳባ ፊደልና ቋንቋ የተፃፈ የአንድ የደአማት ንጉሥ የረበህ ልጅ ለመነ ዜና

[202] P. L. Shinnie, Meroe: A Civilization of the Sudan, (1967), p. 33.

መዋዕል የንጉሡን ስም ከአገሩ ስም ጋር አጣምሮ «ሰመነ የረበሀ ልጅ የደአማታውያን፣ የሳባውያን፣ የአበራውያን፣ የቀዮችና የጥቁሮች ንጉሥ» ይላል።

2. በዘመነ ክርስትና በ183 በምድረ አረቢያ በሳባ ቋንቋና ፊደል በተጻፈ ዜና መዋዕል የዘመኑ የኢትዮጵያ ንጉሥ ስም «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» ተብሎ ተጽፏል።
3. በአረቢያ በሳባ ዜና መዋዕል «የሀበሾችና የአክሱማውያን ንጉሥ ገደረት» በዚያው ዘመን በኢትዮጵያ በግዕዝ ቋንቋና ፊደል በተጻፈ ዜና መዋዕል «የአክሱማውያን ንጉሥ ገደር» ተብሎ ቀርቧል።
4. በ4ኛው ምዕተ ዓመት በኢትዮጵያ በሦስቱ የግዕዝ፣ የግሪክና የሳባ ቋንቋዎች የተጻፈው የአጼ ኢዛና ዜና መዋዕል «ኢዛና የአልአሜዳ ልጅ የነገደ ሐሌን፣ የአክሱም፣ የሀሜር፣ የረይዳን፣ የኢትዮጵያ፣ የሐበሡት፣ የሳባ፣ የሰልሔን፣ የጽያሞ፣ የካሱ፣ የቤጃ ንጉሠ ነገሥት» ይላል።
5. በ6ኛው ምዕተ ዓመት በአረቢያ በግዕዝ ቋንቋ የተጻፈው የአጼ ካሌብ ዜና መዋዕል ደግሞ «ካሌብ የኢዛና ልጅ የአክሱም፣ የካሱ፣ የረይዳን፣ የሳባ፣ የሰልሔን፣ የትአሞ፣ የቲሃማት፣ የራባም፣ የኖባ፣ የአራባት፣ ንጉሥ» ብሎ ከንጉሡ ስም ጋር የብዙ ሕዝቦችንና አገሮችን ስም ይጠራል።
6. በ6ኛው ምዕተ ዓመት በሳባ ቋንቋና ፊደል የተጻፈው በአረቢያ የኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ አብርሃ ዜና መዋዕል «የሳባ፣ የዲሁረይዳን፣ የሃድራማዊ፣ የየመን፣ የቲሃማት፣ የደጋና ቆላ አረቦች ንጉሥ አብርሃ የነገደ ግዕዝ ተወላጅ» ይላል።

እነዚህ የኢትዮጵያ ታሪክ ቁልፍና ወሳኝ የሆኑ የሰነድ መረጃዎች የተጻፉት በግምት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በአንድ ሚሊኒየም ዘመን ውስጥ ነው። በዚህ ረገድና ተግባር ከላይ በሠንጠረዥ 4 - 5 በቀረቡ መረጃዎች እንደተመለከተው፣ በአንድ በኩል እነዚህን ልዩ ዜና መዋዕሎች ጨምሮ ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በአንድ ሺህ ዓመታት ዘመን ውስጥ በኢትዮጵያ፣ በአረቢያ፣ በሱዳንና በግብፅ በአምሳ በተለያዩ ታሪካዊ ቦታዎች በአራቱ ጥንታዊ የደአማት፣ የሳባ፣ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎችና ፊደሎች በድንጋይ ላይ የተፃፉና በ500 የሚቆጠሩ ጽሑፎች በ1804-1981 ሰላሳ በሚሆኑ ተመራማሪ ምሁራን ጥናት ተገልጸው ለዓለምና ለትውልድ ለመጀመሪያ ጊዜ ታውቋል።





በሌላ በኩል ደግሞ፣ ከላይ እንደተጠቆመው፣ በ550-1300 'ጨለማ' ዘመን በኢትዮጵያ ምድርና ቤተ መንግሥት በድንጋይ ላይ ሆነ በብራና የተፃፈ አንድም የጽሑፍ ሰነድ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም።[203] በመሆኑም በ550-1300 'ጨለማ' ዘመን ውስጥ የአክሱም ሥልጣኔ ውድቀት በሚመለከትም ሆነ የአገው መንግሥት ክስተትና ፍጻሜ ወይም የአገሩንና የመንግሥቱን ስያሜ በሚመለከት ምንም ተጨባጭ የታሪክ መረጃና ትምህርት እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም። ይህን አስመልክቶ የእንግሊዙ ታዋቂ የኢትዮጵያ ታሪክ ተመራማሪና ጸሐፊ ምሁር ዶክተር ዋሊስ ባጅ እንዳስቀመጠው፣

> ***The truth is that Abyssinians know nothing about the true history of their country in pre-Christian times. They have always had a passionate desire to be considered a very ancient nation, and the vivid imagination of their scribes has borrowed the traditions of historical facts preserved by the Semites, i.e. Yamanites, Himyarites, Hebrews, etc., and modified them to suit the aspiration of their fellow-countrymen ... The first "King of the Kings of Ethiopia" known to us is Yekuno-Amlak (A. D. 1270-1285), who brought the whole country under his rule.***[204]
>
> ***The history of Abyssinia during the Christian Era, as presented by chroniclers and scribes, until we come to the second half of the 13th century, is incomplete and, in some respects, is wholly untrustworthy ... It is the sad fact that no Ethiopic manuscript older than the 14th century is known to exist.***[205]
>
> ***Contradictions, anacronisms and confounding of the names of persons and places are common in works dealing with history and chronology, and prove that their authors and copyists lacked the ability to write history as we understand it. Much confusion has been caused by the mistakes made in copying by ignorant and sleepy and careless scribes,***[206]

ይህ ሁሉ ከሆነና ከተባለ በኋላ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር አጎራባች አረቦች «ሀበሻ» ብለው ለሚጠሩት ለአንድ የጥቁር አፍሪካ ጥንታዊ ሕዝብና አገር «ኢትዮጵያ» የተሰኘው የግሪኮች ስያሜ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ የተሰጠው፣ ከላይ እንደተመለከተው፣ በ14ኛው ምዕተ ዓመት በአጼ አምደጽዮን ዘመነ መንግሥት (1314- 1344) በ1320 ገደማ[207] በአክሱም ቤተ ክርስቲያን መነኩሴት ከአረብኛ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ...

[203] Budge, History, p. XI.
[204] Ibid., p. X.
[205] Ibid., XI.
[206] Ibid., p. XII.
[207] Donald N. Levin, Greater Ethiopia: The Evolution of a Multiethnic Society, (1974), p. 100.

በተተረጎመው የክብረ ነገሥት መጽሐፍ ነው።[208] የሰነዱ የአረብኛው ረቂቅ የተጻፈው «ሀበሻ» በሚል ስም ነው። በኋላ በ17ኛው ምዕተ ዓመት በሃይማኖት ትምህርት ልዩነትና ግጭት ተሸንፈው ከኢትዮጵያ የተባረሩ የካቶሊክ ሚሲዮናውያን «ሀበሻ» የተሰኘውን የአረብ ስያሜ «አቢሲኒያ» በሚል ላቲናዊ ትርጉም በምዕራቡ ዓለም እስከ ሀያኛው ምዕተ ዓመት መጀመሪያ ድረስ በጽሑፍ አሰራጩ።

በሌላ በኩል በአገር ውስጥ በ1931 በአጼ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ሕገ መንግሥት «ኢትዮጵያ» የሚለው የግሪኮች ስም በመጨረሻ የሕዝቡ የአገሩና የመንግሥቱ ሕገ መንግሥታዊ ስያሜ ተደርጎ ተደነገገ። በቀጣይ ሦስት የኢትዮጵያ የ1955+ የ1987 እና የ1994 ሕግጋተ መንግሥትም እንዲሁ ተደነገገ። ይህ ሁሉ ሲሆንና ሲባል ሁለቱም የአረቡ «ሀበሻ» እና የግሪኩ «ኢትዮጵያ» ነባር የጥቁር አፍሪካ ሕዝቦች የወል ስያሜዎች ናቸው።

[208] Budge, Queen of Sheba, p. 228.





# መደምደሚያ

## የውጭ አገር አስተማሪዎች ትምህርት ተጽዕኖ በኢትዮጵያ ታሪክ ላይ

የኢትዮጵያ የ1974 ሕዝባዊ አብዮት የቀድሞ ዘውዳዊ ሥርዓትን ከጉልተኛው የገዥ መደብ ጋር በማስወገድ የአገሪቱን በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች+ ቋንቋዎች+ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ባዲስና ሁለአቀፍ የጥናት ዘዴ (ሜቶዶሎጂ) ከስልተ ምርትና ከሥርዓተ ማህበር አኳያ+ ከአዳዲስ የመረጃ ምንጮች አኳያ+ ከአዲስ የኢትዮጵያ በሀውርታዊ ኅብረተሰብ ግምባታ አኳያ ለማጥናትና ለማወቅ ብዙ አስፈላጊና ምቹ የሆኑ ቅድመ ሁኔታዎችን+ ምክንያቶችንና መንገዶችን ፈጥሯል። ስለሆነም በዚህ ወቅትና ሁኔታ ከሁሉ በፊት የኢትዮጵያ የሕዝብና የመንግሥት ታሪካዊ መነሻና ማንነት በሚመለከት ባገር ውስጥ ባለፉት 2500 ዓመታትI

1) በግምት ከ500 ዓመተ ዓለም እስከ 550 ዓመተ ምህረት ድረስ በ1000 ዓመታት በአራቱ ጥንታዊ የደአማት+ የሳባ+ የግዕዝና የግሪክ ቋንቋዎች በድንጋይ ላይ ተጽፈው ባለፉት 200 ዓመታት ከከርሰ ምድር የተገኙ ጥንታዊ ሰነዶችI
2) በዘመነ ክርስትና በግምት ከ1270 እስከ 1855 ድረስ በ585 ዓመታት በግዕዝ ቋንቋ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊዎች የተጻፉ የነገሥታት ዜና መዋዕሎች+ የካህናት ገድለ ቅዱሳንና ገድለ ሰማዕታትI
3) ከ1855 እስከ 1974 ድረስ በ120 ዓመታት በአማርኛ ቋንቋ በቤተ መንግሥት ባለሟሎች የተጻፉ የነገሥታት ዜና መዋዕሎች+ ገድለ ካህናትና የመሥሪያ ቤት መዛግብት እስከ 1974 ሕዝባዊ አብዮት ድረስ የተለያዩና ቁልፍ የሆኑ የታሪክ መረጃ ዓይነቶችና ምንጮች ናቸው።

በመጀመሪያው ክፍል የተጠቀሱና በድንጋይ ላይ የተጻፉ ጥንታዊ ሰነዶች የኢትዮጵያን የኅብረተሰብ+ የመንግሥትና የታሪክ መነሻ በሚመለከት ቁልፍና ወሳኝ የሆኑ የመረጃ ምንጮች ናቸው። በመሆኑም ይህ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ጥናት በአመዛኙ የተመሠረተው በተጠቀሱ ጥንታዊ ቁልፍ ጽሑፎች ላይ ነው።

በሌላ በኩል በዘመነ ክርስትና በግምት ከ550 እስከ 1300 ድረስ ለስምንት ምዕተ ዓመታት በኢትዮጵያ የክርስቲያን ቤተ መንግሥትና ምድር በድንጋይ ላይ ሆነ በብራና የተጻፈ አንድም ሰነዳዊ የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም። በዚህ ረጅም የታሪክ መረጃ ባልተገኘበት የጨለማ ዘመን በኢትዮጵያ ከአክሱም ቀጥሎ የተነሳው የአገው የክርስቲያን መንግሥት (1100-1270) ባለሥልጣኖች የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ከግብፁ ቤተ ክርስቲያን ረጅም ግዛት ነፃ ለማውጣት ለመጀመሪያ ጊዜ ያልተሳካ የፖለቲካ እርምጃ እንደወሰዱ ተረጋግጧል።

ነገር ግን ይህንን የአገው መንግሥት የገጠት ፖሊሲና እንቅስቃሴ ለማጥፋት እስከዚያ ድረስ በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን ላይ ለ1000 ዓመታት የነበራትን ከፍተኛ የሥልጣን መብትና የኢኮኖሚ ጥቅም የበለጠ ለማጠናከርና ለማስፋፋት የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በአንድ በኩል በአገር ውስጥ፣ በራሱ በአገው ሥርወ መንግሥትና መንግሥት ላይ ተፃራሪ የፖለቲካ ኃይሎችን በወኪል አቡኖቹዋ አማካይነት አደራጅታ በተሳካ የፖለቲካ ሴራ ከኮላ አሰለፈች።[1] በሌላ በኩል ደግሞ ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት በአስገባቻቸውና ክብረ ነገሥት እና ፍትሐ ነገሥት በተሰኙ ባሕረ መዛግብት[2] የኢትዮጵያን ታሪክ ወደ ሰለሞናዊ የአይሁድ ተረት ቀየረች።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ የግብፅ ቤተ ክርስቲያን በክብረ ነገሥት ሰነድ የኢትዮጵያን ጥንታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በ1000 ዓመተ ዓለም በሙሴው የኦሪት ሕግና ሃይማኖት ትምህርት የመሠረቱ ከኢየሩሳሌም የመጡ የአይሁድ መሳፍንትና ካህናት ናቸው ብላ በይፋ አወጀች።[3] በ1300ዎቹ በተጻፈው የፍትሐ ነገሥት ሰነድ ደግሞ ከ1000 ዓመታት በፊት በ325 ዓመተ ምህረት በኒቅያ ጉባኤ የተቀመጡ 318 የዓለም አህዳዊ ቤተ ክርስቲያን መሪዎችና መምህራን (ማለትም ክርስትና ገና በ330 ዓመተ ምህረት ወደ ኢትዮጵያ ከመግባቱ በፊት) ከግብፃዊው ወኪል አቡን በስተቀር ማንም ኢትዮጵያዊ ተወላጅ በምንም ጊዜና መንገድ የአገሩ የኢትዮጵያ ቤተ

[1] ተክለጻድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ ከአጼ ይኩኖ አምላክ እስከ አጼ ልብነድንግል (1951)፣ ምዕ 4 ፣ Tadesse Tamrat "The Abbots of Debre Hayq 1248-1535", Journal of Ethiopian Studies, Vol. 8, No. 1 (1970), pp. 89-90.

[2] E. A. W. Budge, tr. and ed; The Queen of Sheba and Her only Son Menyelek (1929); Paulos Tzadau, tr. The Fetha Nagest: The Law of the Kings (1918).

[3] Ibid., The Queen of Sheba, pp. 51-84.





ክርስቲያን የበላይ መሪና አስተማሪ እንዳይሆን ወስነዋል[4] በማለት በኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የዘረኝነት መርዛማ ትምህርት በመለኮታዊው የክርስትና ሃይማኖት ስም መሠረተች።

ባጭሩ የኢትዮጵያን የሕዝብ፣ የመንግሥትና የታሪክ መነሻና ማንነት በሚመለከት ጉዳይ ላይ የተጠቀሱ የክብረ ነገሥት እና የፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሕግጋት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን የቀረበው የዘረኝነት አስተምህሮ (ማለትም እምነትና ትምህርት) ከ1270 እስከ 1974 ድረስ ለ700 ዓመታት፣ በኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብ፣ መንግሥት እና ታሪክ ላይ ሁለአቀፍ የፖለቲካ፣ የእምነት፣ የትምህርት፣ የባህል፣ የኢኮኖሚ፣ የሰላም፣ የዕድገትና የልማት ችግሮችን ያስከትላል። የጦርነትና የጥፋት መዘዝና መዓት ያደርሳል።

ከ1270 እስከ 1855 ድረስ በኢትዮጵያ የቤተ መንግሥት ታሪክ ጸሐፊዎች በግዕዝ ቋንቋ በብራና የተፃፉ ዜና መዋዕሎች፣ ገድለ ቅዱሳንና ገድለ ሰማዕታት ከግብፅ ቤተ ክርስቲያን በክብረ ነገሥት እና በፍትሐ ነገሥት ባሕረ ሕግጋት በገባ የፖለቲካ አስተምህሮ የሚመራው የኢትዮጵያ ኅብረተሰብና መንግሥት የፖለቲካ፣ የሃይማኖትና የጦርነት ዘገባዎች ናቸው።

ዘገባዎቹ የሚገልፁት ሁኔታዎችና ነገሮች በተጠቀሰው የጦርነት ዘመን ራሳቸውን ሰለሞናውያን ነን ብለው የሰየሙ የኢትዮጵያ ነገሥታት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር አዋማዊ፣ እስላማዊና አሪታዊ ሕዝቦችንና መንግሥታትን ለመግዛት ለረጅም ዘመን ያካሄዱዋቸውን ወታደራዊና ወንጌላዊ ዘመቻዎችን ነው።

በተጠቀሱ የመንግሥትና የሃይማኖት ሰነዶች የክፍለ አህጉሩ አሪታዊ፣ እስላማዊና አዋማዊ ሕዝቦችና መንግሥታት፣ ለምሳሌ የአገው፣ የሰሜን/ፈላሻ፣ የይፋት፣ የሀዲያ፣ የዳሞት፣ የአዳል፣ የሶማሌ፣ የኦሮሞ... ሕዝቦች በሙሉ የኢትዮጵያ የክርስቲያን ሕዝብ፣ መንግሥትና ሃይማኖት ደመኛ ጠላቶች ናቸው ተብለው ተፈርጀዋል። የተጠቀሱ ሕዝቦች በአገራቸውና በመሬታቸው «ወራሪ» ጠላቶች ተብለው ለቅጣትና ለጥፋት ጦርኞት ተመድበዋል።

በመሆኑም የክፍለ አህጉሩ አዋማዊ፣ እስላማዊና አሪታዊ 'ጠላት' የተባሉ ሕዝቦችና መንግሥታት በተጠቀሱ የክርስቲያን ኃይሎች እና ሰነዶች ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ተደርገው አልተወሰዱም። ምክንያቱም የክርስትና ሃይማኖት፣ በተጠቀሱ ኃይሎች ዘንድ፣

[4] Paulos Tzadau, The Fetha Nagest, pp. 17-18.

የኢትዮጵያዊነት ብቸኛው መነሻና ቅድመ ሁኔታ፥ ማተብና ማህተም እንደሆን ተደርጎ ተወስዷልና።

በቅርቡም በ1855-1974 በአማርኛ ቋንቋ የተጻፉ የኢትዮጵያ የአጼው መንግሥት ሰነዶች የአገሪቱን አምሣዊ፥ እስላማዊና አረታዊ ሕዝቦች፥ መንግሥታትና ሃይማኖቶች በሚመለከት በ1270-1855 የግዕዝ ብራና ከተጻፉ መዛግብት በይዘትና በዓይነት የሚለዩ አይደሉም። ከዚህ አንፃር እንዲያውም በዘመኑ የተነሱ አጼ ነገሥታት ቴዎድሮስ፥ ዮሐንስ፥ ምኒልክና ኃይለ ሥላሴ በከፍለ አህጉሩ እስላማዊና አምሣዊ ሕዝቦች ላይ የክርስትያን መንግሥትና ኅብረተሰብ ለመገንባት ለቀየሱትና ለተከተሉት ወታደራዊና ወንጌላዊ ፖሊሲና ፕሮግራም ታሪካዊ ሞዴልና መሠረት ተደርጎ የተወሰደው የጥንቱ ሰለሞናውያን ነገሥታት ይኩኖአምላክ፥ አምደፅዮን፥ ዳዊት፥ ይስሐቅ፥ ዘርዓ ያዕቆብ፥ ልብነ ድንግልና ገላውዴዎስ ... በከፍለ አህጉሩ ነባር እስላማዊና አረታዊ ሕዝቦች ላይ በጠንካራ የክርስቲያን ሃይማኖትና ጦር የተማከለ ዘውዳዊ መንግሥትና ሥርዓት ለመገንባት የተጠቀሙት ወታደራዊና ወንጌላዊ ፖሊሲና ፕሮግራም ነው።

ከ1855 እስከ 1935 ድረስ ለ80 ዓመታት የተጠቀሉ አጼዎችና ባለሥልጣኖቻቸው በተለይ በኢትዮጵያ እስላማዊና አምሣዊ ሕዝቦችና መንግሥታት ላይ በሰፋሪ የጦር አበጋዞች፥ ወታደሮችና ቄሶች አማካይነት አጼያዊ የክርስቲያን መንግሥት፥ ሃይማኖት፥ ሥርዓትና ባህል እንደመሠረቱ ሕዝቡንም እንደባዕድ ጠላት በአገሩና በመሬቱ ላይ ሰብዓዊ የምርጫና የእንቅስቃሴ መብትና ነፃነት የሌለው የመንግሥትና የሰፋሪ ኃይሎች ቋሚ ገባርና ባሪያ አድርገው፥ በጦርና በፈረስ ኃይል የተሸነፈው ሰው የአሸናፊው ባሪያና ገባር ነው በሚለው የፍትሐ ነገሥት አረታዊ ሕግና ሥርዓት መሠረት፥ እንደገዙት የታሪክ መረጃና ትምህርት ያስተምራል።

ይህ ሁሉ ከሆነና ከተደረገ በኋላ በመጨረሻ በ1936 ዘውዳዊና አረታዊ የነፍጠኛ፥ የባሪያና የገባር ሥርዓቶች በኢጣሊያ ወራሪ ኃይል ተደመሰሱ። በዚህ ወቅትና ሁኔታ መሳፍንታዊ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች ከአጼው ጋር ከአገር ተሰደዱ። በመሆኑም የኢትዮጵያ የሰለሞናውያኑ ባሮችና ገባሮች አርነት ወጡ።

በ1941 በእንግሊዝ ጦርና በኢትዮጵያ አርበኞች ኅብረት የኢጣሊያ ወራሪ ፋሽስቶች ከአገር ተባረሩ። የተሰደዱ አጼ ኃይለ ሥላሴ ከተከታዮቻቸው ጋር ተመልሰው እንደገና የመንግሥት ሥልጣን ባለቤት ሆኑ። የኢትዮጵያ ሕዝብም ተመልሶ ለሚቀጥሉት 33 ዓመታት ወደ ዘውዳዊ ቀምበር ሥር ገባ።





በዚህ ወቅት ከ1941 እስከ 1974 ድረስ የምርጥ መሳፍንቶች፥ መኳንንቶች፥ ካህናት፥ ሚኒስትሮች፥ አገረገዥዎች፥ የጦርና የፖሊስ መኮንኖች፥ ጉልተኞችና የከተማ ከበርቴዎች ኅብረት መንግሥት በአጼው መሪነትና አዝማችነት በኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገርና ኅብረተሰብ ላይ በአንድ በኩል የገዥውን መደብ ሃይማኖትና ቋንቋ ብሔራዊ ሃይማኖትና ቋንቋ አደረገ። በሌላ በኩል ደግሞ የአገሪቱን የተቀሩ ቋንቋዎችን ከእስልምና ሃይማኖት ጋር ለማጥፋት የሚያስችል የኢኮኖሚ፥ የትምህርት፥ የባህልና የሃይማኖት ፖሊሲና ሥርዓት ቀይሶ ተግባራዊ በማድረግ ለኢትዮጵያ የ1974 ሕዝባዊ አብዮት ፍንዳታ የራሱን የጎላ አስተዋፅኦ አደረገ።

ከዚህ አኳያ፥ አንደኛ፥ በ1940ዎቹ፥ በ1950ዎቹና በ1960ዎቹ በ19ኛው ምዕተ ዓመት በደቡብ ኢትዮጵያ በመንግሥት ስምና ሥር የተያዘው የአገርና የሕዝብ መሬት በአጼው ፈቃድና ትእዛዝ ከላይ ለተጠቀሱ የገዥው መደብ መሪዎችና አባሎች በስፋት በግል ይዞታ ተሰጠ። በዚህ አዲስ የመሬት ፖሊሲ ጉዳይ፥ በ1941-1974፥ «ለገዥው መደብ አባሎች በድምሩ 4,828,560 ሄክታር ማለትም ስፋቱ 4,636,716 ሄክታር ከሆነው ከቀድሞ የኢሉባቦር ክፍለ ሀገር የሚበልጥ ለም መሬት በአጼው ትእዛዝና ስጦታ በርስትነት እንደተሰጣቸው በሰነድ ተመልክቷል።»[5]

ይህ የአጼው የመሬት ፖሊሲና ተግባር በአብዮቱ ዋዜማ በአገሪቱ ውስጥ በአንድ በኩል በመንግሥቱ ላይ የገጠር አርሶ አደሮችንና ብሔረሰቦችን በየአካባቢያቸው በአመፅ አስነሳ። በሌላ በኩል ደግሞ በአዲሱ ጉልተኞች ከመሬታቸው የተፈናቀሉ አርሶ አደሮች ከገጠር ወደ ከተማና ኢንዱስትሪ አካባቢዎችና ማዕከላት እየተሰደዱ ለከተማና ለወዛደሩ መደብ ዕድገት አንዱና ዋናው ምንጭና ምክንያት ሆኑ። ባጭሩ በድህረ ጦርነት የኢትዮጵያ የዘውዳዊ መንግሥት የመሬት ፖሊሲና ተግባር የገጠሩን አርሶ አደር ወደ ከተሜነት፥ ወዛደርነት፥ ነጋዴነት፥ ወታደርነት፥ ተማሪነት፥ ቦዘኔነት፥ አሽከርነትና ኩሊነት ለወጠው። በተጨማሪም በገጠር ለብሔረሰብና ለአርሶአደር እንዲሁም በከተማ ለወዛደር፥ ለተማሪ፥ ለአስተማሪ፥ ለነጋዴ፥ ለቦዘኔ ፀረ መንግሥት አመፅ መነገድና ምክንያት ፈጠረ። በሌላ ቃል፥ በራሱ በኢትዮጵያ በሀውርታዊ ኅብረ ተሰብና መንግሥት ውስጥ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት ታሪካዊ መነሻ፥ ሂደትና ዘመን ተከሰቱ። በኢምፔሪያሊዝም ግፊት፥ በኢትዮጵያ ጥንታ

---

[5] ዓጽሶ ጌ ድሌቦ፥ የኢትዮጵያ የገበር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም (1983)፥ ገፅ 222።

ዊና ኋለቀር «ምሥራቃዊ» ሥልተምርትና ሥርዓተማኅበር ለአብዮታዊ የሥርዓት ለውጥ የውስጥና የውጭ ሁኔታዎች፣ ኃይሎች እና ግፊቶች ተከሰቱ።

ሁለተኛ፣ በነሐሴ 1944 በንጉሡ ሁለአቀፍ የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የትምህርትና የባህል ፖሊሲ ድንጋጌ ቁጥር 3 በአገሪቱ ከአንዱ የገዥው መደብ ቋንቋ በስተቀር የተቀሩ ቋንቋዎች በሙሉ የጽሕፈት፣ የትምህርትና የሥራ መሣሪዎች ሆነው እንዳያድጉ በሕግ ተወሰነ።[6] የድንጋጌው መሠረታዊ ዓላማና ተግባር፣ የኢትዮጵያን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገርና ኅብረተሰብ የአንድ ሕዝብ፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ባህል፣ ንጉሥ፣ መንግሥትና ሥርዓት አገር ማድረግ ነው።

ሦስተኛ፣ በጥቅምት 1955 በተሻሻለው ሕገ መንግሥት፣ በአንድ በኩል በአንቀጽ 38 እና 40 በይፋ ኢትዮጵያውያን በሙሉ በሕግ ፊት የእኩልነት መብትና የሃይማኖት ነፃነት አላቸው ተባለ። ይሁን እንጂ በሌላ በኩል ደግሞ በአንቀጽ 125 እና 126 ሁለቱ የገዥው መደብ ቋንቋና ሃይማኖት ምርጥ ያገርና የመንግሥት መሣሪያዎችና መግለጫዎች ናቸው ተብለው ተደነገጉ።[7]

አራተኛ፣ በጥር 1956 በንጉሡ ትእዛዝና በጽሕፈት ሚኒስቴር ማለትም በንጉሡ ልዩ ጽሕፈት ቤት ጥብቅ ቁጥጥር ስር «የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር» በተቋቋመበትና በቅርቡ በመጋቢት 1993 ለሕዝብና ለታሪክ ይፋ በሆነ የምሥጢር ሰነድ[8] በአንድ በኩል የገዥ መደቡን ቋንቋና ሃይማኖት ምርጥ ያገርና የመንግሥት ብቸኛ ቋንቋና ሃይማኖት አድርጎ ለማሳደግ፣ በሌላ በኩል ግን የአገሪቱን የተቀሩ ቋንቋዎች በሙሉ ከእስልምና ሃይማኖት ጋር በመንግሥታዊ ፖሊሲ እና አሠራር ለመጨቆን እስከ 1974ቱ አብዮት ድረስ በተግባር ላይ የሚቆይ የፖለቲካ ውሳኔና እርምጃ ተወሰደ።

ይህ ሁሉ ከሆነና ከታወቀ በኋላ፣ ከ1855-1974 ድረስ ለ120 ዓመታት የኢትዮጵያ አጼ ነገሥታት በኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች አገርና ኅብረተሰብ ላይ አህዳዊና ወንጌላዊ የዘውድ መንግሥትና ሥርዓት ለመገንባት

---

6 የሚሲዮናውያን የማኅበር አቋቋም፣ ነጋሪት ጋዜጣ፣ ድንጋጌ ቁጥር 3 (ነሐሴ 21 ቀን 1936)።

7 የኢትዮጵያ የተሻሻለው ሕገ መንግሥት (ጥቅምት 24 ቀን 1948) አንቀጽ 38፣ 40፣ 125፣ 156።

8 የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር፣ ቤተ መዛግብት ቁጥር 146 (48) ሚያዝያ 8 ቀን 1948)፣ "የኢትዮጵያና የኢትዮጵያዊነት ጸር የሆነው መንግሥታዊ ሰነድ፣ ጧሰኝ፣ ቁጥር 3 (መጋቢት 1985)።





በተከታታይ ያካሄዱት የምዕከልና ፖሊሲና ፖለቲካ የዮካቲት 1974 የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮት በፈነዳ ጊዜ ፈረሰ።

የኢትዮጵያና የኢትዮያውያን ታሪካዊ መነሻና ማንነትን በሚመለከት በሰኔ 11 ቀን 1987 (1995) ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባደረግኩት ቃለምልልስ፣ «የትኛውም የኢትዮጵያ ዘር መጤ አይደለም፣ ያገራችንን ፖለቲካ ያበላሸው የታሪካችን መበላሸት ነው» በሚል ቲሲስ ያቀረብኩትን ትንታኔ የዚህ ተዛማጅና ቀጣይ ጥናት መደምደሚያ ላደርገው እወዳለሁ።

በዚህ ጥናት ይዘትና ሂደት በስፋትና በጥልቀት እንደተብራራው፣ ታሪክ ማለት የሰው ልጅ ያለፈው ዘመን ሥራ፣ ሕይወት፣ ድርጅት፣ ምርት፣ ባህል፣ እምነትና ትምህርት ድምር መግለጫ ነው። ካለፈው ዘመን፣ ሥራና ልምድ በጥናትና ምርምር የሚገኝ እውቀትና ትምህርት ነው። የሰው ልጅ በየዘመኑና በየትውልዱ የያለፈውን ዘመን ባህላዊ ቅርስና ውርስ ማለትም ተጨባጭ የሥራ መረጃና ልምድ በጥናትና ምርምር በሥፍራ፣ በጊዜና በተግባር መስፈርትና ሚዛን መርምሮና አገናዝቦ የሚያገኘው ማኅበራዊ ልምድ፣ እውቀት፣ ትምህርት ነው። በሌላው ትርጉሙ ደግሞ፣ ታሪክ የማህበራዊ እውቀትና ትምህርት የሚገኝበት ሜቴዶሎጂ ማለትም ስልተ ጥናት ነው። ከተግባር አኳያ ደግሞ ታሪክ የሰው ልጅ ካለፈው ዘመን ልምዳዊ እውቀትና ትምህርት ተነስቶ የሚመጣውን ዘመን፣ ትውልድ፣ ኅብረተሰብ ከሁለቱም ከትላንትና ከዛሬው የተሻለና የበለጠ አድርጎ ለመገንባት የሚችልበት መንገድና መሣሪያ ነው። በዚህ የታሪክ ትርጉምና ትምህርት መሠረት፣ የታሪክ መነሻ ከሰው ልጅ ሥራና ልምድ በተወሰነ ሥፍራና ጊዜ የሚገኝ የታሪክ መረጃ ነው። በመሆኑም የታሪክ መረጃ በሌለበት ሥፍራና ጊዜ የታሪክ ሜቴዶሎጂም እውቀትም አይኖርም ማለት ነው።

በዚህ ረገድና ተግባር፣ የኢትዮጵያን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ መነሻ፣ ይዘት፣ ጥናትና ትምህርት በሚመለከት ባለፉት 700 ዓመታት (1270-1974) ውስጥ ከአገር ውጭ የግብፅና የአውሮፓ ክርስቲያን አስተማሪዎችና ጸሐፊዎች የተረትና የዘረኝነት ተፅእና በማሳደራቸው በአገራችን እስከ ዛሬ ድረስ ሳይንሳዊ የታሪክ ሜቴዶሎጂና ትምህርት ገና አልዳበረም።

ከዚህ አኳያ፣ አንደኛ ከ330 እስከ 1950 ድረስ ለ1620 ዓመታት በ110 ወኪል አቡኖቿዋ አማካይነት የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን ስትመራ የኖረችው የግብፅ ቤተ ክርስቲያን የአገሪቱን ጥንታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ በ1000 ዓመተ ዓለም በአረት ሕግና

ሃይማኖት ምህረት የፈጠሩ ከኢየሩሳሌም ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ምርጥ የአይሁድ መሳፍንትና ካህናት ናቸው ብላ በክብረ ነገሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተማረች። ሕዝቡም ራሱንና ታሪኩን ረስቶ ምርጥ የአይሁድ ዘር ነኝ ማለት ጀመረ። በዚህ የተረት እምነትና ትምህርት መሠረትም እንደአገውና እንደኦሮሞ ያሉ የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ዜጎች የአይሁድ ዘር አይደላችሁም ተብለው በአገሪቱ መንበረ-ሥልጣን ላይ እንዳይቀመጡ ተደረጉ። ለምሳሌ በዚህ መንገድ እና ምክንያት፥ በ1270 የአገው ተወላጅ አጼ ይትባረክ፥ እንዲሁም በ1916 የኦሮሞ ተወላጅ ልጅ ኢያሱ፥ ሁለቱም በግብፅ ቤተ ክርስቲያን ከተወገዙ በኋላ፥ በጦር ኃይል ከመንበረ ሥልጣን ተባረሩ። እንደእንስሳትም በስለት ታረዱ።

ሁለተኛ፥ ባለፉት ሦስት ምዕተ ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያን የግዕዝ ፊደል ከስምንቱ ሴማዊ የግዕዝ፥ የትግረ፥ የትግርኛ፥ የአርጎብኛ፥ የአማርኛ፥ የጉራግኛ፥ የሐረሪኛና የጋፋትኛ ቋንቋዎች ጋር አይተው የአውሮፓ ክርስቲያን የሃይማኖት፥ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ምሁራን በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር በነባር ኩሻዊና ናይሎቲካዊ ጥቁር የአፍሪካ ሕዝቦች ላይ ከ500 ዓመተ ዓለም ጀምሮ የኢትዮጵያን ጥንታዊ የአክሱም መንግሥትና ሥልጣኔ የፈጠሩ ከአረቢያ ቀይ ባሕር ተሻግረው የገቡ «ሀበሻ» እና «እጋዓዚያን» የተባሉ ሁለት ሴማዊ ነጭና ምርጥ የአረብ ነገዶች ናቸው በማለት መላምት ፈጥረው በሳይንስና በታሪክ ስም ለኢትዮጵያውያንም ለዓለምም በስፋትና በዝርዝር አስተምረዋል።[9]

በእነዚህ የአውሮፓ ምሁራን እምነትና ትምህርት መሠረት፥ የኢትዮጵያ ነባር ኩሻዊና ናይሎቲካዊ ሕዝቦች የመንግሥትና የሥልጣኔ ሥርዓቶችን መገንባት የማይችሉ ኋላቀር ጥቁር ዘሮችና ሕዝቦች ናቸው። መጤ ነጭ ሴማውያን የተባሉ ሕዝቦች ደግሞ «ምርጥ» የሥልጣኔ ሐዋርያት ናቸው። በመሆኑም መጤ ሴማውያን የተባሉ ኃይሎች በኢትዮጵያ ነባር ጥቁር ሕዝቦች ላይ ገዥዎችና ጌቶች ለመሆን በቅተዋል። በሌላ በኩል ደግሞ ኋላቀር ናቸው የተባሉ የኢትዮጵያ ጥቁር ሕዝቦች በቁጥር በመብዛታቸው ምክንያት በአናሳ መጤና «ምርጥ» ሴማውያን ቋንቋና ባህል ላይ ከባድ የብክለትና

[9] Job Ludolf, A New History of Ethiopia (1681); E. Littmann, tr. and ed., Saba sche, Greichische und Altabessinische Inschriften Book IV, Deusche Aksum-Expedition (DAT) (Berlin, 1913); Conti Rossini, "Expedition et Possessions des Habashat en Arabie", Journal Asiatique, Vol. 18 (1921); E. Ullendorf, The Semitic Languages of Ethiopia (1955); Ibid., The Ethiopians (1966).





የብልሽት ተፅዕኖ እንዳስከተሉ በተጠቀሱ ምሁራን ተገልጿል። በሴማውያኑ ምርጥ ቋንቋና የሥልጣኔ ባህል ላይ የተባለውን ብክለትና ብልሽት አድርሰዋል ተብለው ከተከሰሱ ነባር ኢትዮጵያውያን መካከል የቤጃ፥ የአገውና የኦሮሞ ኩሻዊ ሕዝቦች በመጀመሪያ ደረጃ ተወንጅለዋል።

ይህን የኢትዮጵያ በሀውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፥ ቋንቋዎች፥ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብ፥ መንግሥትና ታሪክ በሁለት የኩሽና የሴም «ጠላት» ዘሮችና ሕዝቦች መካከል የሚከፍለውን ትምህርት በእንግሊዘኛ ቋንቋ (1) *The Semitic Languages of Ethiopia (1955)* እና (2) *The Ethiopians (1966)* በተሰኙ መጽሐፎቹ በጊዜያችን በዓለም ላይ በዓይነትና በብዛት ያሰራጨው የእንግሊዙ ይሁዳዊ የቋንቋና የሥነ ጽሑፍ ምሁር ፕሮፌሰር ኤድዋርድ ኡለንዶርፍ (Edward Ullendorf) ነው። ፕሮፌሰር ኡለንዶርፍ (The Ethiopians) «ኢትዮጵያንስ» በተሰኘው መጽሐፉ በግልፅና በደፋ እንዳስቀመጠው፥

*1. "A glance at any linguistic map of Ethiopia will show almost dramatically, the small, yet compact, Semitic island stretching from northern Eritrea to Addis Ababa into the south surrounded on all sides by a vast Cushitic sea, with some Nilotic currents in the west and two tiny Semetic islets in the east (Harari) and the south (Gurage).*

*"For the reasons which already have been stated in previous chapters, we shall mainly confine ourselves in this survey to the Semitic languages of Ethiopia, since they express that "real" Abyssinia as we know it and are the virtually exclusive carriers of Ethiopian civilization, literature and intellectual prestige ... the impact of the Cushitic languages on their Semitic superstrata has in some cases been considerable, especially in the field of syntax, and will to that extent be touched upon in the following pages. The position has been well summed up by M. M. Moreno in the form of a general "law": the socially superior minority imposes its language by virtue of its prestige while the majority "deforms" that language by virtue of its large numbers."*[10]

*2."The Gallas had nothing to contribute to the civilization of Ethiopia; they possesed no material or intellectual culture, and their social organization was at a far lower stage of development than that of the population among whom they settled. They were not the only cause of the depressed state into which the country now sank, but they helped to perpetuate a situation from which even a physically and spiritually exhausted*

[10] Ibid., The Ethiopians, pp. 116-117.

*Ethiopia might otherwise have been able to recover far more quickly.*"[11]

ከኢትዮጵያ ጥንታዊ የደአማትና የአክሱም የድንጋይ ላይ ጽሑፎችና የአካባቢው ጥንታዊ የአረብ ጹሑፎች ኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያንን በሚመለከት ከጻፉ ግንቢ ሰነዶች በስተቀር፣ ከ1270 እስከ 1974 ድረስ በኢትዮጵያውያንና በአውሮፓውያን ስለኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን የተጻፉ ሰነዶችና መጻሕፍት በሙሉ፣ በ1972 በሁለት የኢትዮጵያ ዘመናዊ የታሪክ ቀዳሚ ምሁራን ማለትም በዶክተር ሰርጉ ሀብለሥላሴና በፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት በቅደም ተከተል *(Ancient and Medieval History of Ethiopia to 1270* እና *Church and State in Ethiopia 1270-1527)* በተሰኙ ርዕሶች የተጻፉትን መጻሕፍት ጨምሮ፣ ከላይ የተጠቀሱ የግብፅና የአውሮፓ ዘረኛ አስተማሪዎች፣ ምሁራንና ጸሐፊዎች እምነትና ትምህርት ነጸብራቆች፣ መገለጫዎች ማስተፉፊያዎች ብቻ ናቸው ለማለት ይቻላል።

ለምሳሌ በታዋቂ የኢትዮጵያ የቤተ መንግሥትና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ምሁርና ጸሐፊ በፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት እምነትና ትምህርት መሠረት፣ ባለፉት 2500 ዓመታት በኢትዮጵያ ምድርና ታሪክ፣ ከአጎራባቹ አረቢያ ምድር በፍልሰት የገቡ «ምርጥ» እና «ሰልጡን» ሴማዊ ሕዝቦች ነባርና «ኋላቀር» ኩሻዊ ሕዝቦችን በሚከተሉት አምስት ልዩ ልዩ ዘመናት ገዝተዋቸዋል። በፕሮፌሰሩ ቃልና ትምህርት በግልፅና በይፋ እንደተባለው፣

*1. "The ultimate origins of the Ethiopian State lie in the remote past, when Sabean settlements were established in northern Ethiopia."*[12]

*2. "South Arabian immigrants began to settle in the hinterland of Adulis as far inland as the surroundings of Aksum before the fifth century B.C."*[13]

*3. "From then on, their settlements became the spearhead of a long process of Semitization of the Ethiopian region."*[14]

*4. "The extensive area of north-east Africa, between the Red Sea and the Nile as far north as the First Cataract and including the whole of the Ethiopian region, is still predominantly inhabited by a large family of people known to anthropologists and linguists as the Kushites."*[15]

*5. "It is precisely in this characteristic pattern of a few South Arabian or Sabeanized individuals moving far into the*

[11] Ibid., p. 76.

[12] Tadesse Tamrat, Church and state in Ethiopia 1270-1527, (1972), p. 5.

[13] Ibid.,

[14] Ibid.,

[15] Ibid.,





*interior and assuming political and cultural leadership among the Kushitic people of the Ethiopian region that one can best envisage the origin and the eventual expansion of the embryonic state organization long established in northern Ethiopia."*[16]

*6. "Thus both for its cultural inspiration and its economic development the Ethiopian region depended entirely on South Arabia."*[17]

*7. "As has already been suggested above, the slow penetration of social and cultural influences into these southern areas must have started in the pre-Aksumite period."*[18]

*8. "It is in fact apparent that the Aksumite conquests were only a second major wave of "Semitic" expansion into the interior of the Ethiopian highlands."*[19]

*9. "With the introduction of the Church into Aksum, this process of expansion got yet another dimension, and it continued throughout the early and the late medieval period."*[20]

*10. "One of the most characteristic aspects of the process of expansion was the establishment of military colonies in the newly conquered territories. It has been said above that the Agaw were the native inhabitants of the Ethiopian plateau north of the river Jama. The immigrants from South Arabia settled in the Northen part of this region and lived among the Agaw population, who gradually adopted the language of the settlers. These linguistically Semitized natives later constituted the dominant section of the peoples of Aksum. As the Kingdom acquired additional territories, large groups of these people were apparently recruited and settled in distant frontier stations. Here they intermarried with the local people and formed yet another Semitized zone in the interior of the Agaw country, which was gradually passing into the sphere of Aksumite political influence. It is apparent that all the Semitic linguistic groups South of the Tigre region had a similar origin. The Amhara tribal group is the most northerly of these communities and was probably the earliest to be established as such.*

*Traditional material on the Amhara is lacking and it is impossible here to give any specific dates for their origin."*[21]

*11. "Ethiopian history has a particular tendency to repeat itself. The military exploits of King Amda-Seyon strongly remind one of the great achievements of the Aksumite Kings Ezana and Kaleb on whom he seems to have modeled himself. More recently, in the nineteenth century, the extensive conquests and*

[16] Ibid., p. 12.

[17] Ibid., p. 15.

[18] Ibid., p. 19.

[19] Ibid.,

[20] Ibid.,

[21] Ibid., p. 37.

*expansion of Amda-Seyon were dramatically re-enacted by Emperor Minilik, who, just like his fourteenth-century predecessor, had the Shawan plateau as the centre of his military activities. It remains to be seen, however, whether Minilik and his successors have been more successful than their medieval counterparts in the essential task of building an Ethiopian nation."*[22]

ሁለት ልዩ የኩሽና የሴም ተፃራሪ ዘሮችና ሕዝቦች ናቸው «የተባሉ» ኃይሎች ላለፉት 2500 ዓመታት በኢትዮጵያ ምድር ላይ በመሬትና በሰፈራ ምክንያቶች በሥፍራና በጊዜ በማያቋርጥ ግጭትና ጦርነት ላይ እንደኖሩ ተደርጎ የቀረበው ይህ የፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት የኢትዮጵያ በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ ትርጉም በሁለንትናው የተወሰደው ከኢጣሊያዊ ጸሐፊ ከሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ መላምትና ከላይ ከተመለ ከተው ከፕሮፌሰር ኡለንዶርፍ ሐተታ ነው።[23]

አሁን እጭርና ዋናው ነገር፣ የሙሴ ኮንቲ ሮሲኒ የኢትዮጵያ ታሪክ መላምት ሆነ የፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ተዛማጅና ቀጣይ ትምህርት፣ ከመነሻውም ሆነ ከመረጃና ከይዘት ወይም ከታሪካዊ ዕድገትና ሂደት አኳያ፣ የአገሪቱን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ኅብረተሰብ፣ መንግሥትና ታሪክ ከተጨባጭ ሳይንሳዊ መረጃና ሥልተ ጥናት በትክክል አልገለፀም። ሊገለፅም አይችልም። ምክንያቱም በእነኮንቲ ሮሲኒ እንደተባለው የኢትዮጵያ ታሪክ የነባር ኩሻውያንና የወራሪ ሴማውያን ጦርነት መግለጫ መሆኑን በሥፍራና በጊዜ መስፈርትና ሚዛን የሚያሳይ የታሪክ መረጃ እስከ ዛሬ ድረስ አልተገኘም። የታሪክ መረጃ ሳይኖር ታሪክም ሆነ የታሪክ ባለሙያ እንደማይኖር የታወቀ ነው።

በመሆኑም አሁን የኢትዮጵያን በህውርታዊ የብዙ ሕዝቦች፣ ቋንቋዎች፣ ሃይማኖቶችና ባህሎች ታሪክ በአዲስ ሜቶዶሎጂ፣ መስፈርትና ሚዛን እንደገና ማጥናትና ለሁሉም የአገሪቱ ዜጎች በሚገባና በሚጠቅም መንገድና ቋንቋ መግለፅና ማስተማር አማራጭ የሌለው የእውነትና የእውቀት ግዴታ ነው።

---

[22] Ibid., p. 302.
[23] Ibid., pp. 1-12.





# የመረጃ ምንጮች
## Bibliography


1. Alvarez, F. The Prester John of Indies. 2 Vols., trs and ed., C. F. Beckingham and G. W. B. Huntingford (1966).
2. Anfray, F., "Recherches Archaelogique en Ethiopie", Academic des Inscriptions et Belles-Lettres (Paris, 1978).
3. Anfray, F. "Les Steles du Sud Shoa et Sidamo", Annales D'Ethiopie. No. 12 (1982).
4. Arabfaqih, Histoire de la Conquete de L'Abyssinie, tr. and ed., R. Basset, (1897).
5. Aren, Evangelical Pioneers in Ethiopia: Origins of the Evangelical Church Mekane Yesus (1978).
6. Bahrey, History of the Galla, C. F. Beckingham and G. W. B. Huntingford, trs. and eds., Some Records of Ethiopia 1593-1646, (London: 1954).
7. Beckingham C. F., "A Note on the Topography of Ahmed Gragn's Campaign in 1542", Journal of Semitic Studies, Vol. 4 (1955).
8. Beckingham, C. F. and G. W. B. Huntingford (1966). trs. and eds., Some Records of Ethiopia 1593-1646 (1954).
9. Beke, C. T., The French and English in the Red Sea, (1862).
10. Bent, J. T., The Sacred City of The Ethiopians, (1896).
11. Bernal, M., Black Athena: The Afrosiatic Roots of Classical Civilization, Volume I: The Fabrication of Ancient Greece 1785-1985 (1997). Volume II: The Archaeological and Documentary Evidence (1991).
12. Bernand, E. A., Drewes, A. J., Schneider, R. et Anfray, F., trs. and eds., Recueil des Inscriptions de L'Ethiopie Periods Pre-Axoumite et Axoumite, (Forthcoming).
13. Braukamper, U., "Islamic Principalities in South- Eastern Ethiopia between the 13th and 15th Centuries", Part I and II, Ethiopianist Notes, No. 1 (1977).
14. Braukamper, U. Geschichte der Hadiya Sud-Athiopiens, (1980).
15. Bruce, J. Travels To Discover the Source of the Nile, 5 Vols., (1790).
16. Budge, E. A. W., A History of Ethiopia, (1966).
17. Budge, E. A. W., The Queen of Sheba and Her Only Son Menyelek, (1922).
18. Coquote A. et Drewes, A. J., "Les Monuments Recueillis a Maqale", Annales D'Ethiopie, No. 1 (1955).
19. Cerulli, E., Ethiopia's Relations with the Muslim World, UNESCO, History of Africa, Vol. III (1988).

20. Christides, Vassilios, "The Himyarite-Ethiopian War and the Ethiopian Occupation of South Arabia in the Acts of Gregentius, Ca. 530 A. D." AE. Vol. 9 (1972).
21. Conti Rossini, Historia Regis Sarsa Dengil, (1907).
22. Conti Rossini, "Expeditions et Possessions des Habashat en Arabie", Journal Asiatique, Ser. 18 (1921).
23. Conzelman, W. E. (tr. and ed.), Chronique de Galawdewos, Roi d' Ethiopie, (1895).
24. Cosmas, Christian Topography of Cosmas, tr. and ed. J. W. McCrimble (1897).
25. Crawford, O. G. S., Ethiopián Itineraries, Circa 1400-1524, (1958).
26. Crummey, D., Priests and Politicians: Protestants and Catholics Missions in Orthodox Ethiopia, 1830-1868 (1972).
27. Cuoq, J., L'Islam en Ethiopie des Origines Au XVI Siecle, (1981).
28. Drewes, A. J., Inscriptions de L'Ethiopie Antique (1962).
29. Doresse, J., Histoire Sommaire de la Corne Orientale de L'Afrique, (1971).
30. Erlich, H., Ethiopia and The Middle East, (1994).
31. The Fetha Nagast: The Law of The Kings, tr. and ed., Paulos Tzadau, (1968).
32. Getahun Delibo, (Lapiso Dilebo) "Early Portuguese Imperialism in Ethiopia, 1490-1632: Origins, Responses, and Consequences", MA. Thesis (Howard University, Wash. D. C., 1971).
33. Getahun Delibo, (Lapiso Dilebo), "Emperor Menelik's Ethiopia, 1865-1916: National Unification OR Amhara Communal Domination", Ph.D. Dissertation (Howard University, Wash. DC, 1974).
34. Getahun Delibo, (Lapiso Dilebo), "Historical Origins and Development of the Eritrean Problem 1889-1962", A Current Bibliography on African Affairs, Vol. 7, No. 3, (1974).
35. Getahun Delibo, (Lapiso Dilebo), History and Historical Maps, National Atlas of Ethiopia, (1988).
36. Getahun Delibo, (Lapiso Dilebo), Ethiopia: A Cradle of History, (1989).
37. Gobalt, S., Journal of a Three years' Residence in Abyssinia (1850).
38. Greenberg, J. H., African Linguistic Classification, UNESCO, African History, Vol. 1, (1981).
39. Hess, Robert, "Chapter 4: Toward A History of the Falasha", Deneil F. McCaall, ed., Eastern African History, (1969).
40. Hess, Robert, "An Outline of Falasha History", Proceeding of the 3rd International Conference of Ethiopian Studies, (1966).
41. Hudson, G., "Language Classification and the Semitic Pre-History of Ethiopia", Folia Orientalia, Vol. 18, (1977).





42. Hudson, G., "Geolinguistic Evidence for Ethiopian Semitic Prehistory", Abbay, Vol. 9, (1918).
43. Huntingford, G. W. B., tr. and ed., The Glorious Victories of Amda Seyon King of Ethiopia, (1965).
44. Huntingford, G. W. B., tr. and ed., The Periplus of the Erythrean Sea (1980).
45. Ibn Fadl A. Umari, Masalik El Absar Fi Amalik El Masar, tr. and ed., G. Demombynes, (1927).
46. Isenberg C. W., and Krapf, J. L., Journals of Isenberg and Krapf (1843).
47. Jamme, W. F., tr. and ed., Sabaean Inscriptions from Mahram Bilqis (Marib), (1962).
48. Jones A. H. M., and Monroe, E., A History of Ethiopia, (1966).
49. Joussaume, R., Le Megalithisme En Ethiopie: Monuments Funeraries Protohistorique Du Harar (1974).
50. Kammerer, A., Essai sur L'Histoire Antique D'Abyssinie: Le Royaume D'Aksum Et Ses Voisins D'Arabe Et De Meroe, (1926).
51. Krapf, J. L., Travels and Researches in East Africa. (1860).
52. Kobishchanov, Y. M., Axum, (1979).
53. Lange, W., History of the Southern Conga: SouthwesternEthiopia, (1982).
54. Lapiso G. Dilebo, The Italo-Ethiopian War of 1887-1896 From Dogali to Adwa, (1996).
55. Leclant, J., "L'Exploration Des Cote Da Mer Rouge : A La Quete De Pount Et Des Secretes De Mer Erythree", AE, No. 11, (1978).
56. Leslau, W., "South-East Semitic: Ethiopic and South Arabic', Journal of the American Oriental Society, Vol. 63, (1943).
57. Leslau, W., Falasha Anthology: The Black Jews of Ethiopia, (1951).
58. Levin, D. N., Greater Ethiopia: The Evolution of a Multiethnic Society, (1974).
59. Littmann, E. tr. and ed., Sabaische Griechische, und Altabessinische Inschriften, Deutsche Aksum Expedition Book IV (DAE) Book IV (1913).
60. Ludolf, Job, A New History of Ethiopia (1681).
61. Maqrizi, The Book of the True Knowledge of the History of the Moslem Kings in Abyssinia, Tr. by G. W. B. Huntingford, (Typescript, 1955).
62. Murtonen, A., Early Semetic: A diachronical Inquiry into the Relationship of Ethiopic to the Other so-called South-East Semetic Languages, (Leiden: Brill, 1967).
63. "Negash: The Second Mecca", Tigrai Culture, Tourism and Information Bureau (Mekelle, 1997).
64. Norris, H. T., "The Himyaritic Tihama: Evidence for a Multi-Racial Society in Pre-Islamic and Early Islamic Arabia," Abbay, No. 9 (1978).


65. Pankhurst, R. An Introduction to the Economic History of Ethiopia, (1961).
66. Perruchon J., tr. and ed., Les Chroniques de Zara Yaeqob et de Baeada Mariam, (1893).
67. Perruchon, J. tr. and ed., "Histoires des Guerres d'Amba Syon, Roi D'Ethiopie", Journal Asiatique, Ser. 8, Vol. 14 (1889).
68. Rubenson, S., The Survival of Ethiopian Independence (1976).
69. Salibi, Kamal, The Bible Came from Arabia, (1985).
70. Sauneron, Serge, The Priests of Ancient Egypt, (1960).
71. Schneider, M., "Steles Funeraires Arabes de Quiha", Annales D'Ethiopie, Vol. 7 (1967).
72. Schneider, R. "Deux Inscriptions Sudaribique du Tigre", Biblothetica Orientalist, vol. 30, Nos. 516 (1973).
73. Schneider, R. "Les Debuts de L'Histoire Ethiopienne" Documents Histoire Civilisation Ehiopienne, RCP. 230, CNRS, FASC. 7 (1976).
74. Schneider, R., "On the Evolution of the Ethiopian Writing", Lecture Text (Addis Ababa, 1982).
75. Schneider, R., "On the Daamatite State, Kings, and Gods", Written note to the author (Addis Ababa, 1982).
76. Schneider, R., "L'Inscription Chretienne d'Ezana en Ecriture Sudarabie", AE, Vol. 10 (1976).
77. Taddesse Tamrat, "The Abbots of Dabra-Hayq", 1248-1535", Journal of Ethiopian Studies, Vol. 8, No. 1 (1970).
78. Tadesse Tamerat, Church and State in Ethiopia 1270-1527, (1972).
79. Tadeschi, S. "Note Storiche Salle Isole Dahlack," Proceedings of The Third International Conference of Ethiopia Studies. 3 Vols., (Addis Ababa, 1966).
80. Sergew Habte Sellassie, Ancient and Medieval History of Ethiopia to 1270 (Addis Ababa, 1972).
81. Sergeant, R. A., "South Arabia and Ethiopia: African Elements in the South Arabian population", Proceedings of the Third International Conference of Ethiopian Studies, 3 Vols. (Addis Ababa: HSIU, 1966).
82. Shinnie, P. L., Meroe: A Civilization of the Sudan, (1967).
83. Trimingham, J. S., Islam in Ethiopia, (1966).
84. Ullendorff, E., The Semitic Languages of Ethiopia (1955).
85. Watt, W. A., Muhammad et Mecca, (1952).
86. Watt, Muhammad at Medina, (1956).
87. UNESCO, General History of Africa I; Methedology and African Prehistory, (1981).
88. Unger, M. F., The New Unger's Bible Handbook, (Chicago: Moody Press, 1984).






89. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፣ ረጅም የሕዝብና የመንግሥት ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት 1982)።
90. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፣ የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም (1983)።
91. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፣ የቀይ ባሕርና የዓባይ ሸለቆ ሚና በኢትዮጵያ ታሪክ (1974)።
92. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፣ የምርትና የባህል ዕድገት በከምባታና ሀዲያ (1975)።
93. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፣ የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ (1985)።
94. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፣ «ብሄራዊ ስሜት ብቻውን የታሪክ ምሁር አያደርግም»፣ እፎይታ ቅ6 ቁ2 (1990)።
95. ላጵሶ ጌ. ድሌቦ፣ «ኢትዮጵያዊነት ትላንትና ዛሬ»፣ እፎይታ ቅ7 ቁ1 (1991)።
96. አጥመ ጊዮርጊስ፣ የጋላ ታሪክ (ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ በሁለት ቅጾች) (1907)።
97. ገበረ ሥላሴ፣ ታሪክ ዘመን ዘዳግማዊ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ 1959።
98. ገብረ እግዚአብሔር ኤልያስ፣ የታሪክ ማስታወሻ፣ 1901-1922 (ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ። የልጅ እያሱና የንግሥት ዘውዲቱ ዘመናት ዜና መዋዕል)።
99. ተክለ ሥላሴ (ጸሐፊ ተዕዛዝ)፣ የአጼ ሱስንዮስ ታሪክ 1605-1632 (ያልታተመ የእጅ ጽሑፍ)።
100. ማኅተመ ሥላሴ ወ/መ፣ ዝክረ ነገር፣ (1962)።
101. ገድለ ተክለ ሃይማኖት (1973)።
102. ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ፣ አክሱም ዛጉዬ (1966)።
103. አለቃ ታዬ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ፣ (1958)።
104. ቅዱስ ቁርአን ያማርኛ ትርጉም (1961)።
105. «አንድነት»፣ ብርሃንና ሰላም (ታኅሣሥ 19 ቀን 1926)
106. «ስለሚሲዮናውያን ማህበር አቋቋም የወጣ ድንጋጌ» ነጋሪት ጋዜጣ ቅ.3 ቁ.3 (ነሐሴ 21 ቀን 1936)።
107. «የልጅ ኢያሱ ምሥጢራዊ አገዳደል» እፎይታ፣ ቅ.2 ቁ.5/6 (ሐምሌ ነሐሴ 1985)።
108. የ1948 የሕዝባዊ ኑሮ ዕድገት ሚኒስቴር ምሥጢራዊ የብሔረሰብና የሃይማኖት ሰነድ የመዝገብ ቁጥር 140/48 በ8/10/48 የተመዘገበ።

## የውጭ ኃይሎች ግፊት፣ የኢትዮጵያ የትግልና የድል ካርታ



ምንጭ ላጌድ ፡ ኢትዮጵያ የታሪክ መነሻ (1990) ።



ይህ <u>የኢትዮጵያዊነት ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች</u> በሰነድ፣ በትውፊት፣ በአርኪኦሎጂ፣ በሊንጉዊስቲክስና በፓሌኦንቶሎጂ መረጃዎች ላይ በዘመናዊ የጥናት ሜቶዶሎጂ በአገርኛ ቋንቋ የተካሄደና ባለፉት አምስትና ስድስት ሺህ ዓመታት በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ ክፍለ አህጉር የተከሰተውን የኢትዮጵያውያን የመነሻና የማንነት ታሪክ የሚገልጽ የአገሪቱ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶች ጥናት ነው። ቋንቋዎቹና ሃይማኖቶቹ የኢትዮጵያውያን የጋራ ህልውናና ማንነት ህያው መግለጫዎችና ማስረጃዎች ናቸው።

በመጽሐፉ እንደተገለደውና በተባበሩት መንግሥታት የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል ድርጅት እንደተረጋገጠው ክፍለ አህጉሩ ከብዙ ሚሊዮን ዓመታት በፊት የሰው ልጅ ለመጀመሪያ ጊዜ የተከሰተበት ብሎም ከዛሬ ዘጠኝና አሥር ሺህ ዓመታት በፊት ጀምሮ ለዛሬ የዓለም ሕዝቦችና ቋንቋዎች የፍለሳና የስርጭት እንቅስቅሴ መነሻ የሆነው ምድር ነው። በሊንጉዊስቲክስ መረጃና ትምህርት መሠረት የኢትዮጵያ አራቱ ኩሻዊ፣ ሴማዊ፣ ኦሞአዊና ናይሎቲካዊ የቋንቋ ቤተሰቦችና ማህበረሰቦች ሁሉም የክፍለ አህጉሩ ነባር ሕዝቦች ናቸው።

ባለፉት አምስትና ስድስት ሺህ ዓመታት የአካባቢው ነባር ሕዝቦችና መንግሥታት በአፍሪካ፣ በእስያና በአውሮፓ አጎራባች አህጉራት በተነሱ ጥንታዊ የግብፅ፣ የሚሮዌ፣ የሳባ፣ የግሪክ፣ የሮምና የአረብ አገሮች ሕዝቦችና መንግሥታት ጋር በጂኦ-ፖለቲካ፣ በሃይማኖትና በባህል የቀረበ መስተጋብርና መወራረስ እንደነበራቸው ከታሪክ መረጃና ትምህርት ተረጋግጧል። በተጠቀሱት የመስተጋብርና የመወራረስ ምክንያቶች፣ መንገዶችና ሥርዓቶች ከመካከለኛው ምሥራቅና ከአረቢያ የገቡ የክርስትናና የእስላምና ሃይማኖቶች ከአገሪቱ ነባር አዋማዊ ሃይማኖቶችና ባህሎች ጋር ተዋህደው ለኢትዮጵያ የክርስቲያንና የእስላም መንግሥታትና ሥልጣኔዎች ድርጅታዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች ለመሆን እንዴት እንደበቁ መጽሐፉ በታሪካዊ መረጃና ትምህርት በዝርዝር ያሳያል።

ንግድ ማተሚያ ድርጅት

[redacted]